# ሕብረተሰብ ሳይንስ

# 7ኛ ክፍል

# የመምህር መምሪያ

አዘጋጅ፡-

መኩሪያ ፈለቀ

አርታኢ፡-

ወንዱ ተክለመድህን

ገምጋሚዎች፡-

ዘላለም አሳጋው

ዘሪሁን ጌታቸው

ይታገሱ አጥናፉ

AL GHURAIR
Printing and Publishing LLC

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

ትምህርት ሚኒስቴር

**ምስጋና**

የዚህ መጽሐፍ ዲዛይን ህትመትና ስርጭት ማከናወኛ ገንዘብ የተገኘው በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ኘሮጀክት (GEQIP) አማካኝነት ነው:: የኘ ሮጀክቱ ዋና ዓላማ በአገሪቱ በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከ1ኛ-12ኛ ክፍሎች የሚሰጠውን የትምህርት ጥራት ማሻሻል ነው::

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ለGEQIP የዋለውን ገንዘብ ያገኘው በብድር/በእርዳታ ሲሆን ብድሩን/ እርዳታውን የሰጡት ዓለምአቀፍ የልማት ማህበራት (IDA)፣ ፋስት ትራክ ኢንሼትቭ ካታሊቲክ ፈንድ (FTI CF) እና ሌሎችም የልማት አጋሮች ማለት የፊንላንድ፣ የኢጣሊያ የልማት ማህበር፣ የኔዘርላንድና የታላቋ ብሪታኒያ የእርዳታ ድርጅት አለምአቀፍ የልማት ዋና ክፍል (DFID) ናቸው::

ሁሉንም በዝርዝር መጥቀስ የማይቻል በርካታ ግለሰቦችና ድርጅቶች ይህ የመምህር መምሪያና የተማሪ መጽሀፍ እውን እንዲሆኑ ያልተቆጠበ ድጋፍቸውን ሰጥተዋል:: በዚህም ትምህርት ሚኒስቴር ምስጋናውን ያቀርባል::

© በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር

1ኛ እትም፣ 2004 ዓ.ም

ISBN 978-99944-2-087-2

**የአል-ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት**
**የፖ.ሳ.ቁጥር 5613**
**ዱባይ፣**
**የተባበሩት የአረብ ኤሚሬት**

**ከኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር**
**የፖ.ሳ.ቁጥር 100767**
**አዲስ አበባ**
**ኢትዮጵያ**

ጋር በመተባበር ይህን መጽሐፍ ለኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር አዘጋጅተው አትመው፣ አሰራጭተዋል::

ሁሉም የህትመት መብቶች ተከብረዋል::
የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም እንደማይቻል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዲራል ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 410/2004 የኮፒራይትና የተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ 10ኛ አመት ቁጥር 55 አዲስ አበባ ጁላይ 19, 2004 ይከለክላል::

የስዕሎችን የኮፒ ራይት መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል:: ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን::

# መቅድም

ትምህርት እና ልማት እጅግ የተቆራኙና አስፈላጊ ነገሮች ናቸው:: ለዚህም ነው ትምህርት በኢትዮጵያ ልማት ውስጥ ዋንኛውና ቁልፍ መሳሪያ ነው ተብሎ የሚነገረው:: በዚህ ፈጣን ዓለም አቀፋዊነት በሚታይባት ዓለማችን ውስጥ ለመኖር አዲስ እውቀት፣ ክህሎት፣ አመለካከቶች እና እሴቶችን እያንዳንዱ ሰው ማዳበር ይጠበቅበታል:: እንግዲህ በዚህ ዓላማ መሰረት ነው የአንድ ሃገር የትምህርት ሂደት ነፀብራቅ የሆነው ስርዓተ ትምህርት ለለውጥ ምላሽ በሚሰጥ መልኩ መቀረፅ ያለበት::

ሃገራችን ኢትዮጵያ አዲስ የትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲ አዘጋጅታ መተግበር ከጀመረች ከአስራ አምስት አመታት በላይ ሆኗታል:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ተደራሽ፣ ፍትሃዊ እና ተገቢነት ያለው  እመርታ በትምህርቱ መስክ አስመዝግባለች:: የትምህርትንም ጥራት ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ  የቆየ ሲሆን ጥረቱ ወደፊትም ይቀጥላል::

ይህን ሂደት ለመቀጠልም የትምህርት ሚኒስቴር የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ማዕቀፍ አዘጋጅቷል:: ማዕቀፉም ሁሉንም  የትምህርት ደረጃ፤ የአፀደ ህፃናት፣ የመጀመሪያ ደረጃ ፣አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ እና የመሰናዶ ክፍሎች ትምህርቶችን ያጠቃልላል:: የማዕቀፉም አላማዎች  የሚያተኩሩት በትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲዎች ላይ ያሉትን መሰረታዊ ሐሳቦችና መርሆዎች ለማጠናከር፤ እንዲሁም ወደፊት ለሚዘጋጁት፣ የስርዓተ ትምህርት መጻሕፍት፣ ለዚህ የመምህር መምሪያና ለተማሪ መጽህፍት አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴንና የመማር ብቃት አቀራረብን ያቀፉ ሆነው እንዲዘጋጁ ማስቻል ነው::

አዲስ ማዕቀፍ ማዘጋጀት እንዲሁም፣ የተከለሱና የተሻሻሉ የመምህር መምሪያና የተማሪ መጻሕፍት ማዘጋጀት የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል በየትኛውም ሀገር ቢሆን ብቸኛ መፍትሔ አይደሉም:: ነገር ግን ቀጣይነት ያለው ማሻሻያ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ይጠበቃል:: የመምህራን ሚናም ከገለፃ ሰጭነት  እስከ አነቃቂነት፣ መሪነት እና አመቻችነት ዘላቂ እንዲሆን  ያስፈልጋል:: ይህንንም ለማገዝ በማዕቀፉ ላይ እና በመምህር መምሪያው ላይ የተቀመጡትን ማስተማሪያ ዘዴዎች በተመለከተ መምህራን ስልጠና የተሰጣቸው ሲሆን ወደፊትም ስልጠናው መሰጠቱ ይቀጥላል::

መምህራን ይህን መምሪያ በጥንቃቄ እንዲያነቡ እና የተቀመጡትን የማስተማሪያ ዘዴዎች በመተግበር ተማሪዎቻቸውን መደገፍ ይጠበቅባቸዋል::

በተማሪ መጽሐፍ በየምዕራፉ መጨረሻ ለተቀመጡት የማጠቃለያ ጥያቄዎች መልሶቻቸው በመምህር በመምሪያ ውስጥ የተቀመጡ ቢሆንም፣ ይህ ተማሪዎችን አማራጭ መልሶችን ከመፈለግ ሊያግዳቸው አይገባም:: ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት መጽሐፋቸውን አንብበው አማራጭ መልሶችን እንዲያገኙ ማስቻልም ይጠበቃል::

# ማውጫ


ገፅ

*መግቢያ* ........................................ i

**ምዕራፍ አንድ፡- በአፍሪካ ውስጥ መኖር**

1.1 የአፍሪካ የቆዳ ስፋት፣ ቅርጽና መገኛ ........................ 2

1.2 ኬንትሮስና ኬክሮስ ........................ 4

1.3 የአፍሪካ ዋና ዋና ቋንቋዎች ቤተሰቦች እና ሥርጭታቸው ........ 8

1.4 ጥንታዊ የአፍሪካ ሥልጣኔ በግብጽና በካርቴጅ ........................ 10

1.5 የቅድመ ቅኝ ግዛት ዘመን ሀገሮች ........................ 13

1.6 የሲራራ ንግድ የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ለማገናኘት
የነበረው ፋይዳ ........................ 16

1.7 የህዝብ ስርጭትና አሰፋፈር ........................ 19

1.8 የአፍሪካ ሕዝብ አኗኗር ........................ 22

1.9 የሕዝብ ሥርጭትን፣ አሠፋፈርንና አኗኗርን
የሚወስኑ ነገሮች ........................ 25

**የምዕራፍ አንድ የክለሳ ጥያቄዎች መልስ ........................ 28**

**ምዕራፍ ሁለት፡- የመሬት አወቃቀር**

2.1 ከካርታ ላይ መረጃ መፈለግና መጠቀም ........................ 29

2.2 የመሬት ንጣፍ ........................ 33

2.3 የአለት ዓይነቶችና አፈጣጠር ........................ 36

**የምዕራፍ ሁለት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ ........................ 40**

**ምዕራፍ ሦስት፡- ሥርዓተ-ምህዳር እና ተጽእና የሚያሳድሩበት ነገሮች**

**3.1** የተፈጥሮ ሀብቶች ........................................................................41

**3.1.1** የተፈጥሮ እጽዋትና የዱር እንስሳት .................................... 41

**3.1.2** ውሃ፣ አፈርና አየር ............................................................... 47

**3.3** የተፈጥሮ ሀብትን ለመንከባከብ
የሚወሰዱ እርምጃዎች ...........................................................51

**የምዕራፍ ሦስት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ .............................................56**

**ምዕራፍ አራት፡- ሕዝባዊ ጉዳዮች**

4.1 ሕዝብ ነክ ጉዳዮች ......................................................................59

4.2 የመብትና የደኅንነት ጉዳይ ........................................................64

4.3 የአጋርነት መር ሐ ግብር .........................................................70

**የምዕራፍ አራት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ** ................................................75

**ዋቢ መጻሕፍት** ............................................................................................77

**አጥጋቢ የመማር ብቃት .....................................................................78**

**መርሀ ትምህርት ...............................................................................82**

# መግቢያ

የመምህር መምሪያ የትምህርት ርዕሶችንና ከእነዚሁ ጋር ተጎዳኝተው የሚሄዱትን የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶችን፣ የክፍለ ጊዜ ሥርጭትን፣ የትምህርት አቀራረብ ዘዴዎችንና የተከታታይ ምዘና ስልቶችን ያካተተ በመሆኑ ለመምህር በጣም ጠቃሚ መሣሪያ ነው፡፡ መምህር ከተመደበው ጊዜ ጋር አገናዝቦ ለሚያዘጋጀው የትምህርት እቅድ ተሟልቶ የቀረበ የጽሑፍ ማስረጃ ነው ማለትም ይቻላል፡፡

ስለዚህ የ7ኛ ክፍል የኅብረተሰብ ሳይንስ መምህር መምሪያ አራት ምዕራፎችን ያካትታል፡፡ እያንዳንዱ ምዕራፍ በንዑሳን ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው፡፡ እያንዳንዱ ንዑስ ምዕራፍ ደግሞ ለማስተማሩ ሥራ ምቹ የሆኑ የትምህርት ርዕሶች አሉት፡፡ እያንዳንዱ ንዑስ ምዕራፍ ደግሞ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች፣ ዝርዝር ይዘቶች፣ የትምህርቱ አጭር መግለጫዎች፣ ለትምህርቱ አቀራረብ የሚጠቅሙ ዘዴዎች፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎች፣ የትምህርቱ ቅድመ ዝግጅቶች አቀራረብና የምዘና ስልቶች ያጠቃለለ ነው፡፡ ከእነዚህ ዝርዝር መረጃዎች አኳያ የትምህርቱ አሰጣጥ ተማሪ ተኮር ስለመሆኑ መምህራን ሊገነዘቡ ይገባል፡፡ ስለዚህ የእርስዎ ዋነኛ ተግባር ለተማሪዎች መመሪያ መስጠት፣ አሠራሩን ማሳየትና ያላሰለሰ ክትትል ማድረግ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የተማሪው ተግባር “እየሠሩ መማር” ከሚለው መርህ አንፃር በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ነው፡፡ የምዘና ስልቶችም እየሠሩ መማር የሚለውን መርህ ከሚያካትቱት አሳታፊ ዘዴዎች ጋር የተገናዘቡ ናቸው፡፡

መምህር በማስተማር ሥራ ላይ ተሠማርተው እንደተገነዘቡት ሁሉ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ተለዋዋጭ ናቸው፡፡ የተመረጠው የትምህርት ርዕስ በዚህ መመሪያ ውስጥ ከተጠቆሙት የመማር ማስተማር ዘዴዎች በአንዱ፣ በሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑት

ሊቀርብ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ የሚጠቀሙበት የመማር ማስተማር ዘዴ ወይም ዘዴዎች አሳታፊ የትምህርት አቀራረብ ስልትን የሚያጎለብቱ መሆናቸውን በአግባቡ መገንዘብ ይገባዎታል፡፡ የምዘና ስልቶቹም በእነዚሁ ዘዴዎች ላይ የተመሠረቱ መሆን አለባቸው፡፡ አሳታፊ ዘዴዎችን ለምን እንጠቀማለን? ምክንያቱም እነዚህ ዘዴዎች በየንዑስ ርዕሱ መጨረሻ በተማሪው ላይ እንዲያመጣ የተተለመውን የባህርይ ለውጥ የሚያጎለብቱ በመሆናቸው ነው፡፡

ከላይ ከቀረበው ዝርዝር ሃሳብ አንፃር የኅብረተሰብ ሳይንስን በመጀመሪያ ደረጃ በምን እንደምናስተምር የሚገልጹትን ጠቅላላ ዓላማዎችና አጥጋቢ የመማር ብቃቶች ማወቅ ይኖርቦታል፡፡ ከዚህም በላይ በ7ኛ ክፍል ኅብረተሰብ ሳይንስን በማስተማር መገኘት ያለበትን ውጤት፣ የተከታታይ ምዘናንና በየርዕሱ ማጠቃለያ ላይ መሰጠት ያለበትን ሙከራ(ቴስት) ትርጉም መገንዘብ አለብዎት፡፡

**የኅብረተሰብ ሳይንስ አጠቃላይ ዓላማዎች**

የኅብረተሰብ ሳይንስ ትምህርት በኢትዮጵያ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሁለተኛው እርከን ከሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች አንዱ ነው፡፡

- የኅብረተሰብ ሳይንስ ተማሪዎች ስለአገራቸው፣ ስለአኅጉራቸው ከዚያም አልፎ ስለ ዓለም ምጣኔ ሀብት፣ ፖለቲካዊና ሕጋዊ ሥራዓቶችና ተቋማት እንዲያውቁ ያደርጋል፡፡
- ተማሪዎች ኃላፊነት ተሰምቷቸው በማኅበረሰብ ሕይወት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ እኩልነትን፣ ፍትህን እንዲያከብሩ፣ መቻቻልንና አርበኝነትን እንዲያጎለብቱ፣ ለአገራቸው ታማኝ ሆነው የአገር ፍቅር ስሜት እንዲኖራቸው የአመለካከት ባህርይ ለውጥን ያዳብራል፡፡
- ተማሪዎች የምንኖርባትን መሬት፣ ጥንታዊ መንግሥታትን፣ ገፀ-ምድርን የሚለውጡ ኃይሎችንና ሕዝባዊ ጉዳዮችን እንዲያውቁና እንዲረዱ ያደርጋል፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

የመማር ማስተማር ዘዴዎች መምህር የሚያስተምሩትን ትምህርት ወደ ተማሪዎች ለማስተላላፍ ወይም ተማሪዎች በመሳተፍ እንዲማሩ የሚደረጉባቸው ዘዴዎች ናቸው፡፡ በመሠረቱ የመማር ማስተማር ዘዴዎች መምህራን የሚያቀርቡትን ትምህርት ከሚያዘጋጁበት፣ የትምህርቱን ግቦች ለመምታት ከሚጠቀሙባቸው ስልቶች ወይም ክህሎት፣ የትምህርት ዓይነት፣ የመስተማሪያ መሣሪያዎች ወይም ከማንኛውም የትምህርቱን ግብ ሊያንፀባርቁ ከሚችሉ አግባብ ካላቸው ጠቃሚ ነገሮች ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ ዘዴዎች ለማስተማር የሚያስፈልጉ አጠቃላይ ዓላማዎችንና ግቦችን፣ የትምህርት ርዕስ መረጣን፣ ግቦችን ለማስፈጸም የሚረዱ የትምህርት ርዕሶችንና የተግባር ቅደም ተከተሎችን፣ የመማር ተግባር ስኬትን፣ የስኬቱ ግብ መምታትን ወይም አለመምታትን መገምገምን ያጠቃልላሉ፡፡

## የማስተማር መማር ዘዴዎች ጠንካራና ደካማ ጎኖች መግለጫ ሠንጠረዥ

| ዘዴ | ጠንካራ ጎን | ደካማ ጎን |
|---|---|---|
| ጥያቄና መልስ (Question & Answer) | - የሚከተሉትን የሚያጠቃልሉ ልዩ ልዩ ዓይነት ጥያቄዎች ለመጠቀም ይረዳል፡፡ እነሱም፡-<br>• ጠቅላላ ጥያቄዎች(general questions)<br>• ከተለያዩ አማራጭ መልሶች አሰጣጥ ጋር የተጎዳኙ ጥያቄዎች(DIvergent questions)<br>• ከማነፃጸር ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች(Probing questions)<br>• ከምክንያታዊነት ጋር የተገናዘቡ ጥያቄዎች<br>- ጥያቄዎቹ ትምህርት ከመጀመሩ በፊትና ትምህርቱ ቀርቦ ከተገባደደ በኂላ በአግባቡ ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ | - መምህራን ከበቂ በላይ በጥያቄዎች መጠቀም መቻላቸው<br>- በእውቀት፣ በግንዛቤና በመሳሰሉት ላይ የሚመሠረቱት ጥያቄዎች ውስን አለመሆናቸው<br>- ጥያቄዎቹን መመለስ የሚያቅታቸው ተማሪዎች ቅር መሰኘት ወይም መሸማቀቅ |
| ገለፃ (explanation) | - የትምህርት ርዕሱን የሚገልጹ በቂ ቃላት መጠቀም ያስችላል፡፡<br>- ተማሪዎች ትኩረት በተሰጠው የትምህርት ርዕስ ላይ አስፈላጊውን መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡፡ | - ሁልጊዜ ተማሪዎች ከመምህር መረጃ እንዲጠብቁ ማድረጉ<br>- ተማሪዎች በአብዛኛው አዳማጮች እንዲሆኑ ማድረጉ፡፡ |
| ውይይት (discussion) | - የሀሳብ ልውውጥ እንዲኖር ያደርጋል፡፡<br>- እያንዳንዱ ተማሪ በንቃት እንዲሳተፍ እድል ይሰጣል<br>- ተማሪዎች የማገናዘብና ምክንያታዊ የመሆን አቅም እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡<br>- ማስተማር የሁለትዮሽ ግንኙት መሆኑን ያረጋግጣል | - ደካማ ተማሪዎች ላይ ትኩረት አለማድረጉ<br>- በጣም ጥቂት ፈጣን ተማሪዎች ውይይቱን መቆጣጠራቸው<br>- ደከም ያሉት ተማሪዎች |

| ዘዴ | ጠንካራ ጎን | ደካማ ጎን |
|---|---|---|
| | | በመምህር ካልተጎተጎቱ በስተቀር መዳከማቸውና መፍዘዛቸው |
| ምልከታ (demonstration) | - የሚቀርበው ትምህርት ተጨባጭ እንዲሆን ይረዳል<br>- የተመረጠና ለእይታ የሚበቃ መረጃ ላይ በመመሥረት የትምህርቱን ርዕስ በቀላሉ ለማቅረብ ያስችላል፡፡ | - የትምህርቱ ርዕስ የሚያጠቃልላቸውን በሙሉ አለማካተቱ<br>- ተማሪዎች ለእይታ በቀረበው ማቴሪያል ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ማድረጉ |
| እውነትን ፈልጎ የማግኘት ዘዴ (Inquiry teaching learning method) | - በመማር ማስተማሩ ወስጥ ተዋናይ የሆኑትን ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ እንዲሳተፉ ያደርጋል<br>- እንደሳይንሳዊ ዘዴ ግትር ባይሆንም በስልት መልስ ለማግኘት ጥረት የሚያደርግ ዘዴ ነው፡፡ ይኸውም ተማሪዎች ለጥያቄዎች ወዲያውኑ መልስ ከመስጠት ይልቅ ሌሎች ጥያቄዎች በማንሳት የበለጠ እንዲመራመሩ ያደርጋል፡፡ ተማሪዎች ወድያውኑ እውነት ነው ብለው ከሚያረጋግጡ ይልቅ እውነትን ፈልገው ማግኘቱ ላይ እንዲያተኩሩ መንገድ ይከፍታል፡፡<br>- ተማሪዎችን ችግርን ለመፍታት የተለያዩና በርካታ አማራጮችን እንዲጠቀሙ ነፃ ያደርጋቸዋል፡፡<br>- ተማሪዎች ከፍተኛ የውስጥ መነሳሳት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ትምህርትን እየተደሰቱና እየጓጉ እነዲቀስሙ በር ይከፈታል፡፡ | - ተማሪዎችን ከእውነታው ጋር ለማገናኘት ያለው ብቃት አዝጋሚ መሆኑ<br>- በተወሰነ ጊዜ ሊሸፈን የተያዘ የትምህርት ርዕስ እንዳይሸፈን ማገቱ<br>- ዘዴው ለየት ያለ እውቀት መጠየቁ፣ ይኸውም የመመራመር፣ የመተንተን፣ የማጠቃለልና የመዘገብ ክህሎት እንዲኖር መፈለጉ |

| ዘዴ | ጠንካራ ጎን | ደካማ ጎን |
|---|---|---|
| ችግር ፈቺ የማስተማር ዘዴ (Discovery teaching method) | - ከፍተኛ የተማሪዎች ተሳትፎ ይታይበታል<br>- ሰፊ ጽንሰ ሃሳቦችንና መርሆችን ለመገንዘብ ከማበረታታቱም በላይ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር አብሮ የመሥራት ችሎታን ያጎለብታል፡፡<br>- ችግር ፈቺ የማስተማር ዘዴ የመምህሩን ድጋፍ የሚፈልግ ሲሆን ተማሪዎች አብሮ የመሥራትና ችግር የመፍታት ዘዴን እንዲለማመዱ ያደርጋል | - ሰፊ የትምህርት ርዕስ ለመሸፈን ያለው ብቃት ደካማ መሆኑ<br>- የመወዳደር ስሜትን ስለሚቀንስ ተማሪዎች ፍዝ እነዲሆኑ ማድረጉ<br>- አብሮ ከመሥራት ባሻገር በተማሪዎች መካከል የውድድር ወይም የመፎካከር ስሜት አለመፍጠሩ |
| የቡድን ኘሮጀክት ዘዴ(የመተባበርና የመፎካከር የማስተማር ዘዴ) (Group project method) | - ለቡድን ሥራ መነሳሳትንና መሳተፍን ያበረታታል ወይም ሁኔታዎችን ያመቻቻል<br>- በተማሪዎች መካከል የመደጋገፍ መንፈስን ያጠናክራል<br>- ተማሪዎች የሥራቸውን የመጨረሻ ውጤት ለማወቅ የበለጠ ጥረት እንዲያደርጉ ያበረታታል፡፡ | - ጊዜ መፍጀቱ<br>- የገንዘብ ወጪ መጠየቁ<br>- እጅግ አስተማማኝ የክፍል አመራር ከሌለ በርካታ የሥነ ምግባር ጉድለት መፍጠሩ |

## ተከታታይ ምዝናና መኩራ

### ተከታታይ ምዘና

ተከታታይ ምዘና ስለተማሪዎች እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ከተለያዩና ከበርካታ ምንጮች መረጃ የመሰብሰብና የመተንተን ሂደት ነው፡፡ ተከታታይ ምዘና የሚከናወነው ተማሪዎች የሚያውቁትን፣ በአንድ ነገር ላይ ያላቸውን ጥልቅ ግንዛቤና ከቀሰሙት እውቀት አንፃር ሊተገበሩ የሚችሉትን ለማወቅና ለማጎልበት ነው፡፡ ተከታታይ ምዘና ግቡን የሚመታው የተከታታይ ምዘናው ውጤቶች የትምህርቱን ሂደት ማሻሻል

ሲያስችሉ ነው፡፡ ስለዚህ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎች የመማር ሂደት አካል ሲሆን የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- ስለተማሪዎች የትምህርት ክትትል መረጃ ይሰጣል
- የማስተማር መማሩን ሂደት ለማሻሻልና ለማረጋገጥ ትችሉ ዘንድ መረጃዎችን በመተንተን ላይ እንድታተኩሩ ያደርጋል፡፡
- ተማሪዎች የሚጠበቁባቸውን ግቦች ማሳካታቸውን መረጃ ይሰጣል፡፡
- ትምህርታዊና ተቋማዊ መሻሻል እንዲደረግ ፍንጭ ይሰጣል
- የተደረጉት ለውጦች በተማሪዎች የመማር አቅም ላይ ያመጡትን መሻሻል መገምገም ያስችላል፤

በአጠቃላይ የመማር ሂደት የተማሪ ተኮር ሥነ ዘዴ የመጨረሻ ትኩረትና ግብ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ተከታታይ ምዘና ተማሪ ተኮር የትምህርት ሥነ ዘዴ እንዲዳብር ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡

የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሲከታተሉ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ማተኮር አለብዎት፡-

- ተማሪዎች ምን ተምረዋል፣ ከተማሩት ውስጥ ምን ያህል አውቀዋል? ምን ክህሎትን አዳብረዋል? ምንስ ያህል የአስተሳሰብ ወይም የአመለካከት ለውጥ አምጥተዋል?
- አስተምሬ ለመድረስ ያሰብኩበትን ግብ ከመምታት አኳያ ምን ያህል ተሳክቶልኛል?

በርካታ ዓይነት ተከታታይ ምዘናዎች ቢኖሩም አሁን የምናተኩረው በተማሪ ተከታታይ ምዘና ላይ ነው፡፡ የተማሪ ተከታታይ ምዘና የሚከተሉትን ለማወቅ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

- ተማሪዎች ምን ያህል እውቀት እንደቀሰሙ፡፡
- የተማሪዎች ክህሎት ምን ያህል መሻሻሉንና መጎልበቱን፡፡

- ተማሪዎች ሥራ ለመሥራት ስላላቸው አቅምና በአቅማቸው ምን ያህል መጠቀም እንደሚችሉ፡፡
- ተማሪዎች ስለሥራ ትጋታቸው ያላቸው ስሜት ወይም ተነሳሽነት ወይም በአጠቃላይ ስላሳዩት የአመለካከት ለውጥ፡፡

**የተከታታይ ምዘና ተግባራት ምን ምን ናቸው?**

- ለተማሪዎች ምን ያህል መማር እንዳለባቸው ማሳወቅ
- ተማሪዎች ምን ያህል ጠንክሮ በመሥራት ላይ ስለመሆናቸው ማስገንዘብ
- በትምህርቱ ምዕራፍ መገባደጃ ላይ ተማሪዎች ጠንክረው ስለመሥራታቸው ማመልከት
- የተማሪዎች ክህሎትና የአመለካከት ለውጥ የደረሰበትን ደረጃ መጠቆም

**እርስዎ የትምህርቱን ሂደት እንዴት መከታተል ይችላሉ?**

- ዕለት በዕለት በሚያደርጉት ምልከታ
- ተከታታይና ዱብዳ ሙከራዎች(ቴስቶች) በመስጠት
- የፕሮጀክት ሥራና የመሳሰሉትን በማዘጋጀት ተማሪዎች በቡድን ሆነው እንዲሠሩ በማድረግና ያገኙትን ውጤት በመገምገም

**በተከታታይ ምዘና እነማን መሳተፍ አለባቸው?**

- መምህራን
- ተማሪዎች
- ወላጆች
- የትምህርት ባለሙያዎች

**ሙከራ/ፈተና**

ከትምህርት አንፃር ሙከራ ሥርዓት ባለው መንገድ የአንድን ሰው እውቀት፣ ክህሎት፣ አመለካከትና ሌሎች ተጓዳኝ የባህርይ ለውጦችን የመለካት ሂደት ማለት ነው፡፡ በርካታ የሙከራ ዓይነቶች አሉ፡፡

መምህራን የተማሪዎቻቸውን የመማር ችሎታ ለመቃኘት ሙከራዎች ይሰጣሉ፡፡ ከዚህም በላይ ተማሪዎች አንዱን የትምህርት ርዕስ ምን ያህል በብቃት ተምረው መገንዘባቸውን ለማወቅ ሙከራዎች እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

**ደረጃቸውን የጠበቁ ሙከራዎች/ፈተናዎች**

አብዛኞቹ በጽሑፍ የሚቀርቡና ተማሪዎች የሚወስዷቸው ሙከራዎች ደረጃቸውን የጠበቁ ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ አንድ ሙከራ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ ተከልሶና በድጋሚ ጥቅም ላይ ውሎ ተመሳሳይ ውጤት ሲያስመዘግብ እንዲሁም የወሰዱት ተማሪዎች ተመሳሳይ አማካይ ውጤት ሲያስመዘግቡ ሙከራው ደረጃውን የጠበቀ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የአንድ ሙከራ ጥራት በሦስት ዋና ዋና ደረጃዎች ይወሰናል፡፡ እነሱም፡-

- ሙከራው የትምህርቱን ግብ የመምታት አቅሙ(Validity)
- ተአማኒነቱ(reliabiligy)
- ተፈጻሚነቱ(practicality) ናቸው

**የትምህርቱን ግብ የመምታት አቅሙ፡-** አንድ ሙከራ ሊለካው የተገመተውን ግብ መለካት ሲችል

**ተአማኒነት፡-** በሙከራው ላይ የተገኘው ተከታታይ ውጤት ተመጣጣኝ ሲሆን ተአማኒነትን ለማረጋገጥ አንድ ሙከራ ለአንድ ቡድን በተደጋጋሚ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በተሰጠበት ጊዜ ሁሉ በጣም የተቀራረቡ ውጤቶች ሊመዘገቡ ከቻሉ ሙከራው በጣም ተአማኒ ወይም አስተማማኝ ነው ማለት ይቻላል፡፡

**ተፈጻሚነት፡-** ሙከራው የሚጠይቀው ወጪ ከአቅም ጋር መገናዘብንና የሚሰጥበት አካባቢን ምቹነት ይመለከታል፡፡ በአንፃሩ ሙከራው ከፍተኛ ወጪና ትጋት የማይጠይቅ ከሆነ ተፈጻሚነቱ ከፍተኛ ይሆናል፡፡ ሙከራውን ለማዘጋጀት ብዙ ወጪና ትጋት የሚጠይቅ ከሆነ ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም፡፡ የሚመዘገበው ውጤትም

ለመተንተን አስቸጋሪ ከሆነ የሙከራው ተፈጻሚነት አስተማማኝ አልነበረም ማለት ይቻላል፡፡

**የሙከራ ዓይነቶች**

አብዛኞቹ ሙከራዎች አንድ ወይም ከአንድ በላይ ባህሪያት እንዲለኩ ተደርገው ይዘጋጃሉ፡፡ እነዚህ ባህሪያት የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡፡

- የመማር ችሎታ
- የትምህርት ውጤት
- ዝንባሌና ፍላጎት

**በመማር ሂደት ላይ የተመሠረቱ ሙከራዎች፡-** በአቅም ላይ የተመሠረቱ ሙከራዎች ሲሆኑ አንድ ተማሪ የማወቅ ብቃቱን ተጠቅሞ ወደፊት ምን ያህል መሥራት እንደሚችል የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ እነዚህ ሙከራዎች አንዳንድ ጊዜ የብስለት ሙከራዎች፣ የአእምሮ ችሎታ ሙከራዎች፣ የአከዳሚክ ዝንባሌ ሙከራዎች በመባል ይታወቃሉ፡፡

**የመማር ብቃት ሙከራ፡-** ይህ ዓይነቱ ሙከራ ደረጃቸውን በጠበቁ ተግባራት ወይም ጥያቄዎች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ተማሪው በሕይወት ዘመኑ በመደበኛ ትምህርት ወይም ከመደበኛ ትምህርት ውጭ ያገኘውን እውቀትና ክህሎት እንዲያሳይ ይረዳል፡፡

**ውጤት ላይ ያተኮረ ሙከራ፡-** አንድ ተማሪ ካለው ጠቅላላ እውቀት ይልቅ አንድ የትምህርት ርዕስ በክፍል ውስጥ ተምሮ ምን ያህል እውቀት እንዳገኘ ይለካል፡፡ ከሌላው የሙከራ ዓይነት በበለጠ ትምህርት ቤቶች ውጤት ላይ ባተኮረ ሙከራ ይጠቀማሉ፡፡
አብዛኞቹ በአንደኛ ደረጃም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ ወይም በኮሌጅ የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪዎችን የትምህርት ክትትል ለማወቅ ውጤት ላይ ያተኮሩ ሙከራዎች ይሰጣሉ፡፡

# የትምህርት እቅድ ናሙና

የትምህርት ቤት ስም ____________________ ቀን ____________________

የመምህር ስም ____________________

የትምህርት ዓይነት ____________________ ክፍል 7ኛ የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ 45 ደቂቃዎች

ምዕራፍ 1 ንዑስ ክፍል ________ የክፍለ ጊዜ ብዛት 1

## የትምህርቱ ርዕስ፡- የአፍሪካ የቆዳ ስፋትና መገኛ

*ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ*

- *የአፍሪካ አኅጉር ቅርጽና ስፋት ከሌሎች አኅጉራት ጋር ያወዳድሩ::*
- *የአፍሪካን ፍፁማዊ መገኛ ይለያሉ::*

| ቀን | የሚወስደው ጊዜ | የትምህርቱ ርዕስ ወይም ይዘት | የመምህር ተግባር | የተማሪ ተግባር | የማስተማሪያ መሣሪያዎች | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሰኞ | *10 ደቂቃዎች* | *የአፍሪካ የቆዳ ስፋት ቅርጽና መገኛ* | • ፍፁማዊ መገኛን በተመለከተ በሚከተሉት ዓይነት ጥያቄዎች ይጠየቃሉ:- ፍፁማዊ መገኛ ማለት ምን ማለት ነው?<br>• ተማሪዎች መልሶቻቸውን ጥቁር ሠሌዳ ላይ እንዲጽፉ ያበረታታሉ:: | • ጥያቄውን ለመመለስ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ::<br>• ስለጥያቄው ነፃ አስተሳሰባቸውን ያቀርባሉ::<br>• በውይይቱ ላይ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ:: | • የአፍሪካ የግርግዳ ካርታ<br>• የአፍሪካ ንድፍ ካርታ | ከገጽ___ እስከ ገጽ____ |

| ቀን | የሚወስደው ጊዜ | የትምህርቱ ርዕስ ወይም ይዘት | የመምህር ተግባር | የተማሪ ተግባር | የማስተማሪያ መሣሪያዎች | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | **20 ደቂቃዎች** | | • በተማሪዎች መልሶች ላይ ውይይት መክፈት::<br>• የአፍሪካን ካርታ በመጠቀም የአፍሪካን ፍፁማዊ መገኛ ማመልከት:: | • ያልገባቸውን ይጠይቃሉ::<br>• የአፍሪካን ፍፁማዊ መገኛ በካርታ ላይ ያመለክታሉ፤ በቀለም ይረልደሉ:: | | |
| | **10 ደቂቃዎች** | | • የዕለቱን ትምህርት በማሰባሰብና ምሳሌዎችን በመስጠት ማጠቃለል:: | • ካርታን በደብተራቸው ላይ ይሥላሉ:: ማስታወሻ ይጽፋሉ:: | | |
| | **5 ደቂቃዎች** | | • በተማሪ መጽሐፍት የተቀመጡ ጥያቄዎችን በክፍልና በቤት እንዲሠሩ መስጠት:: | • የተሰጣቸውን የክፍል ሥራ በቡድንና በግል ይሰራሉ:: | | |

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# ትምህርት ሚኒስቴር

# ህብረተሰብ ሣይንስ በመማር ከየክፍል ደረጃው የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት ደረጃ
# 7ኛ ክፍል

# የህብረተሰብ ሣይንስ የ7ኛ ክፍል አጥጋቢ የመማር ብቃት

| | 7ኛ ክፍል |
|---|---|
| ህዝብ | • የአፍሪካን መገኛ፣ መጠን እና ቅርፅ መግለፅ |
| | • የአፍሪካ ህዝቦችን ታሪክ፣ቋንቋ እና ሐይማኖት ማብራራት፤ |
| | • ስለ አፍሪካ ጥንታዊ ሥልጣኔ፣ቅርስ እና ባህል ፅብረቃ ማድረግ፤<br>• በኢትዮጵያ የሲራራ ንግድ ህዝቦችን በማስተሳሰር የነበረውን አስተዋፅኦ ማድነቅ፤ |
| | • በአፍሪካ አህጉር ለህዝቦች አሰፋፈር፣ አኗኗር እና ሥርጭት ልዩነት ምክንያት የሆኑ እንደ መሬት ገፅታ፣ የተፈጥሮ ሃብትና የአየር ንብረት ወዘተ መለየት፤ |
| | • የካርታን አቅጣጫ በመጠቀም ከሌላ ህዝብ ጋር ግንኙነት መፍጠር፤ |

| | 7ኛ ክፍል | |
|---|---|---|
| ሥነ ምህዳር እና ተግዳሮቶቹ (ፈታኝ ሁኔታዎች) | ሥነ ምህዳር እና ተግዳሮቶቹ | • በአፍሪካ የሚገኙ አበይት ዕፅዋትን እና እንስሳትን መለየት፤ |
| | | • በአፍሪካ የውሃ ሃብት፤አየር የተፈጥሮ ዕፅዋት፣የድር እንስሳት እና አፈር ላይ ተፅዕኖ የሚሳድሩ ዋና ዋና ችግሮችን መለየት |
| | | • በአፍሪካ ህዝብ ፣የተፈጥሮ ዕፅዋት እና የዱር እንስሳት መካከል ያለውን መስተጋብር ማብራራት፤ |
| ሥነ ምህዳር እና ተግዳሮቶቹ (ፈታኝ ሁኔታዎች) | | • በአፍሪካ ያለው ፈጣን የህዝብ ዕድገት በዕፅዋት፣በዱር እንስሳት እና በአፈር ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ መገንዘብ |
| | | • በአፍሪካ ያሉ ዋና ዋና የተፈጥሮ ዕፅዋት፣፣የዱር እንስሳት የውሃ፣የአየር እና አፈር ጥበቃ መንገዶችን መለየትና መዘርዘር፤<br>• በአካባቢያቸው ዛፎችን ለመትከል እና እንስሳትን ለመንከባከብ የሚያስችል ክህሎት ማዳበር፤<br>• የብዝሃ ህይወት መመናመን በህዝብ አኗኗር ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት መገንዘብ፤ |
| | | • በአፍሪካ ያሉ ዋና ዋና የተፈጥሮ ዕፅዋት፣ የዱር እንስሳት የውሃ፣ የአየር እና አፈር ጥበቃ መንገዶችን መለየትና መዘርዘር፤<br>• በአካባቢያቸው ዛፎችን ለመትከል እና እንስሳትን ለመንከባከብ የሚያስችል ክህሎት ማዳበር፤<br>• የብዝሃ ህይወት መመናመን በህዝብ አኗኗር ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት መገንዘብ፤ |

| | 7ኛ ክፍል | |
|---|---|---|
| ህዝባዊ ጉዳዮች | ሥነ ህዝብ ነክ ጉዳዮች | • የኤች አይቪ/ ኤድስ መስፋፋት በአፍሪካ ማህበረሰብ ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ መገንዘብ፤<br>• የኤች አይቪ/ ኤድስ በአፍሪካ የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ በዝርዝር መረዳት፤<br>• ፈጣን ህዝብ ዕድገት የሚያስከትለውን ተፅዕኖ መገምገም |
| | የደህንነትና የመብት ጉዳዩች | • የህፃናት መብት ጥሰት መከላከያ መንገዶች ተግባራዊ ማድረግ፤<br>• የመልካም አስተዳደር መለያ ባህሪያትን መተንተን፤<br>• በመልካም አስተዳደር እና መልካም አስተዳደር በሌለበት ሁኔታ የሚስተዋሉ ተግባራትን ማወዳደር፤<br>• ወደ መጥፎ ድረጊት የሚያመሩ ህገወጥ ባህሪያትን መለየት፤ |
| | አጋርነትን የማጠናከር ፕሮግራም | • የአፍሪካን ክፍለ አህጉራዊ ድርጅቶች እና የትብብር መድረኮች የማህበረ ኢኮኖሚ እና ፖለቲካዊ ግቦችን ማድነቅ፤ |

# የሕብረተሰብ ሣይንስ መርሃ ትምህርት
# 7ኛ ክፍል

## የሰባተኛ ክፍል ሕብረተሰብ ሣይንስ ትምህርት መማር ማስተማር ውጤቶች

1. **ግንዛቤና ዕውቀት ማዳበር**
   - የአፍካን የቆዳ ስፋት፣ ቅርፅና ከሌሎች አህጉራት ጋር ያላት አንድነትና ግንኙነት
   - የአፍሪካ ዋና ዋና ቋንቋዎች ዝርዝርና ስርጭት
   - ጥንታዊ ግብፅና ካርቴጅ የአፍሪካ ቀደምት ስልጣኔ ማዕከል ስለመሆናቸው
   - የጥንታዊ ግብፅና ካርቴጅ ስልጣኔ ለአፍሪካ ያበረከቱዋቸው አስተዋፅኦዎች
   - በቅድመ ቅኝ ግዛት ዘመን የማሊና ሩንጂ ግዛት የኢኮኖሚ መሰረት
   - የአፍሪካ ሕዝብ ስርጭት
   - ለአፍሪካ ሕዝብ ስርጭትና አኗኗር መሰረታዊ ተፅዕኖዎች
   - የካርታ ምንነትን፣ ኬክሮስና ኬንትሮስ  ከሜሪዲያንና ዋልቴ ጋር ያላቸው ግንኙነት
   - የመሬት ውስጣዊ ንብርብሮች
   - የላይኛው የመሬት ክፍል ቅራፎ ይዘቶች
   - የአለት አይነቶችና አፈጣጠራቸው
   - የአለቶች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ
   - ዕፅዋትና የዕፅዋት ሥርጭት በአፍሪካ
   - የዱር እንስሳት ስርጭት በአፍሪካ
   - የዱር እንስሳት የዕፅዋት ትስስር/ግንኙነት
   - በዱር እንስሳት በዕፅዋት ላይ የሚደርሱ የሰው ልጅ አሉታዊ ተፅዕኖዎች
   - በተፈጥሮ ዕፅዋት ላይ  አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያመጡ ተፈጥሮአዊ ነገሮች
   - የሰው ልጅና ውሀ
   - የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትና ዕጥረት በአፍሪካ
   - የዕፅዋት እንክብካቤ በሌሎች ሀብቶች ላይ ያለው ጠቀሜታ
   - የውሀና አየር ብክለትን መቆጣጠር
   - የአፈር እንክብካቤ በአፍሪካ
   - በአፍሪካ የሕዝብ ቁጥር በፍጥነት መጨመር
   - የመልካም አስተዳደር አለመኖር /ዕጥረት/ መገለጫዎች በአፍሪካ

- የሕፃናት መብት ስምምነት ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ደጋፊ መረጃዎች
- የሕፃናት መብት ጥሰት
- ወንጀል ምንድን ነው?
- ክልላዊ ድርጅቶች በአፍሪካ
- የአፍሪካ ክልላዊ ድርጅቶች አባል ሀገሮች
- የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አመሰራረትና ወደ አፍሪካ ሕብረት መሸጋገር

## 2. ክህሎትና ችሎታን ማዳበር

- የአፍሪካን ካርታ በመሳል የሕዳግ መረጃ (Marginal Information) ምንነትና ጠቀሜታን ማሳየት
- በአካባቢያቸው ፈጣን የሕዝብ ዕድገት የሚያመጣቸውን ችግሮች አስመልክቶ ዘገባ አዘጋጅቶ ማቅረብ
- በአካባቢያቸው የመልካም አስተዳደር እጦት /እጥረት/ መገለጫዎች ላይ ዘገባ አዘጋጅቶ ማቅረብ
- ልጆች መብታቸው እንዳይጣስ እንዴት መከላከል እንደሚችሉ
- የወንጀል መገለጫዎችን ማስቀመጥ መቻል

## 3. አመለካከትና ዝንባሌ ማዳበር

- በቅድመ ቅኝ ግዛት ዘመን በዚምባቡዌ የነበረውን /የተሰራውን/ የዕደ ጥበብ ውጤት ማድነቅ
- የሲራራ ንግድ ሕዝብን ከሕዝብ በማገናኘት ያደረገውን አስተዋፅኦ ማድነቅ
- በአፍሪካ ያሉትን የተፈጥሮ ሀብትና የዱር አራዊት ጠቀሜታን መገንዘብ
- የንፁህ ውሀ አገልግሎትን ለማስፋፋት ንቁ የሕዝብ ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑን ማወቅና ለመሳተፍም ሙሉ ፈቃደኛ መሆን
- አፍሪካ ውስጥ ካሉ ክልላዊ ድርጅቶች ጋር አጋርነት/ወዳጅነት/ ለመፍጠር ፍላጎት ማሣየት

## ምዕራፍ አንድ፦ የአፍሪካ ሕዝብ አኗኗር *(23 ክፍለ ጊዜያት)*

***አጠቃላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፦*** ከዚህ ምዕራፍ ፍፃሜ በኋላ ተማሪዎች፦

- ስለ አፍሪካ ቅርፅ፣ መገኛና ዋና ዋና ቋንቋዎች ያብራራሉ፡፡
- ስለ አፍሪካ ጥንታዊ ስልጣኔ እና ስለ አፍሪካ ቅድመ ቅኝ ግዛት ዘመን ግዛቶች ይገነዘባሉ፡፡
- በአፍሪካ ሕዝቦች አሰፋፈር፣ ስርጭትና አኗኗር ላይ ተፅዕኖ ስላላቸው ነገሮች ያብራራሉ፡፡

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ፦*<br>• የአፍሪካን ቅርፅና ቆዳ ስፋት ከሌሎች አህጉራት ጋር ያወዳድራሉ፡፡<br>• የአፍሪካን ፍጹማዊ መገኛ ይለያሉ፡፡ | ***1. በአፍሪካ መኖር***<br>**1.1. የአፍሪካ የቆዳ ስፋት፣ ቅርፅና መገኛ** *(2 ክ/ጊዜ)*<br>• የአፍሪካ አቀማመጥና መገኛ<br>• የአፍሪካ የቆዳ ስፋትና ቅርፅ | • የአፍሪካን ካርታ ይዞ ወደ ክፍል በመግባት ተማሪዎች አፍሪካን እንዴት እንደሚረዱት እንዲናገሩ ማበረታታት በደረሱበት መነሻ ሀሳብ ላይ ተመርኩዘው ስለ አፍሪካ ቅርፅ፣ መገኛ እና ስፋት እንዲወያዩ ማድረግ<br>• ምንም ሀገሮች ያልተፃፈበት ባዶ የአፍሪካን ካርታ ከተማሪዎች ፊት ለፊት በማስቀመጥ ሀገሮቹን እንዲሞሉ ማድረግ፣ ተማሪዎች የሰጡትን መረጃ ማጠናከር፡፡<br>• ከሀገሮቹ ስም በተጨማሪ ወንዞቹንና፣ ዋና ከተሞቹንም በካርታቸው ላይ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡<br>• **ውስን ጥናት፦**ሁለት ከተሞችን ለምሳሌ አክራና ካምፓላን በመውሰድ በማወዳደር ውስን ጥናት እንዲያቀርቡ ማድረግ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
| --- | --- | --- |
| • የኬንትሮስና ኬክሮስን ምንነት ከቀዳማዊ ኬንትሮስ /ዋልቴ/ /ፕራይሜሪዲያን/ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ይገልጻሉ፡፡ | **1.2.ኬንትሮስና ኬክሮስ** *(3 ክ/ጊዜ)*<br>• የየካንሰርና የካፕሪኮርን የሀሩር መስመር እንዲሁም የምድር ወገብ<br>• የኬክሮስ ፣የኬንትሮስ መስመሮች እንዲሁም የግሪንዊች ሜሪዲያን<br>• የጊዜ አቆጣጠር | • ሀገሮችንና ዋና ከተማቸውን እንዲያዛምዱ ድንገተኛ ፈተና መስጠት<br>• **የክፍል ውይይት፡-**ስድስተኛ ክፍል የተማሩትን በማስታወስ የክፍል ውስጥ ውይይት እንዲያካሂዱ ማድረግ፡፡ ከዚያም በሰሌዳው ላይ ካፕሪኮርን፣ ካንሰር፣ ምድር ወገብንና የመሬት እንዝርትን እንዲስሉ ማድረግ<br>• በመቀጠል ሌሎች የኬክሮስ መስመሮችን ማስተዋወቅ ቀጥሎም ከዋልቴ በመነሳት ሌሎች ኬንትሮሶችን ማስተዋወቅ ፡፡<br>• ተማሪዎች ስእሎችን በደብተራቸው ላይ እንዲገለብጡ ማድረግ፡፡<br>• አንድ ሰዓት ወደ ምስራቅ ለመሄድ 15 ዲግሪ ኬንትሮስ መሄድ እንዳለብን መንገር እና ከፀሐይ መስመር ምህዋር ጋር ለማያያዝ/ ለማዛመድ የሳተላይት ቴሌቪዥንን ፕሮግራም መጠቀም፡፡ ለምሳሌ በናይልሳት የሚተላለፈውን የእግር ኳስ የቴሌቪዥን ፕሮግራም በዩናይትድ ኪንግዳም፣ በካይሮ፣ አዲስ አበባ፣ በሳውዲ አረቢያ፣ በአቡዳቢ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | በስንት ሰዓት እንደሚታተለፍ ማሣየት፡፡ ለምሳሌ ታላቋ ብሪታኒያ (0° ላይ) አንድ እግር ኳስ ጨዋታ በ14፡50 ሰዓት ላይ ቢጀመር በአዲስ አበባ ላይ ስንት ሰዓት ይሆናል? ብሎ ተማሪዎችን በመጠየቅ ማስተማር፡፡ |
| • የአፍሪካ ዋና ዋና ቋንቋዎችን ስም (የቋንቋ ግንድ ስም) ይዘረዝራሉ | **1.3. የአፍሪካ ዋና ዋና ቋንቋዎች ቤተሰቦችና ስርጭታቸው** *(2 ክ/ጊዜ)*<br>• ዋና ዋና የቋንቋ ቤተሰቦች | • የሚታወቁትን የማንኛውንም ቋንቋ ግንዶችን እንዲገልፁ ተማሪዎችን መጠየቅ በባዶ አፍሪካ ካርታ ላይ የተወሰኑ ቋንቋዎች መገኛን እንዲያሳዩ በማድረግ ማስተማር፡፡ ለምሳሌ የላንቲንና፣ የአረብን፣ የሰዳንን ቋንቋ ይመልከቱ<br>• ከ5 ደቂቃ ባልበለጠ ጊዜ በአፍሪካ ቋንቋ ግንዶች ዙሪያ ገለፃ እንዲያደርጉ መጋበዝ<br>• የሁለት ዋና ዋና ቋንቋ ተናጋሪዎችን እንደምሳሌ በመውሰድ የማወዳደር ውስን ጥናት ስራ እንዲሰሩ ማድረግ<br>• የቋንቋ ስርጭትን በሚሳይ ካርታ የቋንቋዎችን መገኛ እንዲያመለክቱ መጠየቅ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • የጥንታዊ አፍሪካ ስልጣኔ ማዕከል ከሆኑት የአፍሪካ ግዛቶች መካከል የግብፅንና የካርቴጅን መገኛ ያመለክታሉ፡፡<br>• የጥንታዊ ግብፅና የካርቴጅን ስልጣኔ ጠቀሜታ ያብራራሉ | **1.4. የጥንታዊ አፍሪካ ስልጣኔ በግብፅና በካርቴጅ** *(2 ክ/ጊዜ)*<br>• የጥንታዊ ግብፅ ስልጣኔ<br>▪ ጥንታዊ ፒራሚድ<br>▪ መካነ መቃብር<br>▪ ቤተ ፀሎትና ጥንታዊ የአምልኮ ስርዓት<br>▪ እርሻና ንግድ<br>• የጥንታዊ ኑቢያ ስልጣኔ መገለጫዎች<br>▪ የሂሮግላፊክስ አፃፃፍ<br>▪ እርሻ<br>• የጥንታዊ ካርቴጅ ስልጣኔ<br>▪ በፊንቄዎች የተመሠረተች ስለመሆኗ፣<br>▪ ንግድ | • በመጨረሻም ተማሪዎች የአንድ ቋንቋ ቡድን ተናጋሪዎችን በመውሰድ በሚችሉት መጠን እንዲዘረዝሩ ማድረግ<br><br>• ከተማሪዎች ጋር የጥንታዊ ግብፅን መገኛ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በተሳለ ካርታ ላይ እንዲያመላክቱ ማድረግ ከአሁኗ ግብፅ መገኛ ጋርም እንዲያወዳድሩ ማድረግ፡፡ ካርታውን እንደገለብጡ ማድረግ<br>• የሥነ ሕንፃ፣ የፈርኦንን፣ ቤተመንግስት እርሻን እና መገናኛ ሁኔታን በሚመለከት በካርታ ላይ እንዲያመለክቱ ማድረግና ከጥንታዊ አክሱም ጋር እንዲያወዳደሩ ማድረግ<br>• ሂሮግለይፊክስን አስመልክቶ፡- ለተማሪዎች ቁልፍ ነገሮችን ፊደሎቹ ምልክቶቹ በማሳወቅ ለማንበብ እንዲሞክሩ ማድረግና ስለ መግባቢያ ጥቅም እንዲያወያዩ ማድረግ<br>• ተማሪዎች ካርቴጂን በካርታ ላይ የት እንደምትገኝ ያመልክቱ<br>• ተማሪዎች በእርሻ፣ ንግድ (በሚዲቴሪኒያን) በሕዝብና በመገናኛ ላይ ውስን ጥናት አድርገው እንዲያቀርቡ ማድረግ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
| --- | --- | --- |
| • በቅድመ ቅኝ አገዛዝ ዘመን የጥንታዊ ማሊና ፍንጂ ግዛት የኢኮኖሚ መሰረት ይተነትናሉ፡፡<br>• በቅድመ ቅኝ አገዛዝ ዘመን የነበረውን የዝምባቡዌ የሥነ ሕንፃ ጥበብ ያደንቃሉ፡፡ | **1.5. የቅድመ ቅኝ ግዛት ዘመን ግዛቶች አፍሪካ**<br>*(3 ክ/ጊዜ)*<br>• ጥንታዊ ዝምባቡዌ<br>• ጥንታዊ ማሊ<br>• ጥንታዊ ፋንጂ | • ግብፅንና ጥንታዊ ፊንቄን ያወዳድሩ<br>• ተማሪዎች የእያንዳንዱ ስልጣኔ ለአሁኑ ዘመን ዕድገት ያለውን ጠቀሜታ እንዲወያዩ ማድረግ<br>• ተማሪዎች ስለ ጥንታዊ ስልጣኔና ስለ ቋንቋዎች ክለሳ ያድርጉ፣ የተማሩትን በክለሳ መልክ ያስታውሱ፡፡<br><br>• ከተማሪዎች ጋር በመሆን የጥንታዊ ዝምባቡዌን መገኛ በካርታ ላይ መለየት፡፡ ተማሪዎች ምን ያህል ስለ ግዛቷ እንደሚያውቁ እንዲወያዩ ማድረግ፡፡<br>• በቅድመ ቅኝ ግዛት ዘመን ስለ ዝምባቡዌ የግንብ ፍርስራሽ የተፃፈ ጽሁፍ መምህሩ በማቅረብ የተካሄደውን የተብራራ ውስን ጥናት መመልከት<br>• ስለ ጥንታዊ ማሊና ፎንጂ አስተዋውቆ በካርታ ላይ እንዲያሳዩ ተማሪዎችን መጠየቅ<br>• የማሊና ፎንጂ ግዛትን የሥነ ሕንፃ፣ እርሻ፣ ንግድ፣ ሕዝብ እና የኢኮኖሚ መሰረታቸውንና ጠቀሜታቸውን አስመልክቶ የተሰራ ውስን ጥናት ተማሪዎች እንዲመለከቱ ማድረግ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | • ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል የትኛውን ባህል በጣም እንደሚወዱ በመጠየቅ የተወሰነ ነገር እንዲፅፉ ማድረግ<br>• በቅድመ ቅኝ አገዛዝ ዘመን በነበሩ አፍሪካዊ ግዛቶች ላይ ድንገተኛ ሙከራ መስጠት<br>• የእነዚህን ግዛት የምስረታና የቆይታ ዘመን በማስቀመጥ ማስተማር |
| • የኢትዮጵያን ሕዝብ በማገናኘት በኩል የሲራራ ንግድ ያደረገውን አስተዋፅኦ ያደንቃሉ፡፡<br>• ሌሎች የንግድ መስመሮች እንዳሉ ያውቃሉ<br>• የንግድ መስመሮችን መነሻ ይለያሉ፡፡ | **1.6. የሲራራ ንግድ የኢትዮጵያ ሕዝቦችን በማስተሣሰር (በማገናኘት) በኩል የነበረው አስተዋፅኦ**<br>*(3 ክ/ጊዜ)*<br>• የሲራራ ንግድ በኢትዮጵያ | • ተማሪዎች በመወያየት የኢትዮጵያን ሲራራ ንግድ መስመሮችን እንዲስሉ ማድረግ፡፡ በመቀጠልም ምን አይነት የንግድ ዕቃዎችን ሲራራዎች ይነግዱ እንደነበር እንዲለዩ ማድረግ<br>• የሲራራ ንግድ በኢትዮጵያ ሕዝቦችን ከሕዝቦች ጋር በማገናኘት በኩል ያለውን አስተዋፅኦ እንዲወያዩ ማድረግ<br>• ከኢትዮጵያ ውጪ ያሉ የንግድ መስመሮች መነሻና መድረሻቸውን በካርታ በመታገዝ እንዲለዩ ማድረግ<br>• በሁለት ዘመናዊ እና ጥንታዊ ንግድ መስመሮች ላይ ውስን ጥናት በማድረግ የተመሰረቱበትንም ምክንያት እንዲወያዩ ማድረግ፡፡ ስለ ሲራራ ንግድ ከእድሜ ባለፀጎችና ከሚያውቁ ሰዎች ጠይቀው ዘገባ እንዲያዘጋጁ ማድረግ፡፡ |

| **የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች** | **ይዘቶች** | **ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች** |
|---|---|---|
| • በሕዝብ ስርጭት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮችን መግለፅና ማብራራት ይችላሉ፡፡<br>• እነዚህ ተፅዕኖዎች ከሕዝብ አሰፋፈር ጋር ያላቸውን ዝምድና እና በካርታ ላይ የሕዝብ አሰፋፈርን ይለያሉ፡፡ | **1.7. ሕዝብ**<br>**1.7.1. የሕዝብ ስርጭትና አሰፋፈር** *(3 ክ/ጊዜ)*<br>• በሕዝብ ስርጭት እና አሰፋፈር ከፍተኛ ተፅዕኖ ያላቸው ነገሮች (ዕፅዋት፣ አየርንብረት፣ የሕዝብ ግፊት)<br>• አየር ንብረት፡-<br>▪ የምድር ወገብ አካባቢ አየር ንብረት<br>▪ የዝቅተኛ አካባቢ አየር ንብረት<br>▪ የገሶ (ሳቫና) አየር ንብረት<br>▪ የምድር ወገብ ከፍተኛ ቦታዎች አየር ንብረት<br>▪ የበረሀማ አየር ንብረት | • ተማሪዎች በአፍሪካ መልክአምድራዊ ካርታ (Physical map) ላይ ያሉ ዕፅዋቶች ላይ እንዲወያዩ ማድረግ<br>• ካርታን በመመልከት ተማሪዎች ስለ አየር ንብረት ምን እንደሚሉ መጠየቅ፣ የትኛው አካባቢ ለምን አይነት እርሻ ምቹ እንደሆነ በመወያየት መለየት እንዲችሉ ማድረግ<br>• የተለያዩ አየር ንብረቶችን ሁኔታ የሚያሳይ ሰንጠረዥ በውስን ጥናት አማካይነት ማዘጋጀት<br>• የአፍሪካን የሕዝብ አሰፋፈር በካርታ ላይ በመመልከት ከሚማሩት አየር ንብረት ጋር እንዲያዛምዱ ማድረግ<br>• ለሕዝብ እንቅስቃሴ መንስኤ ስለሆኑ ሌሎች ነገሮች ለምሳሌ ጦርነት፣ ርሀብ፡ ድርቅ እንዲወያዩ ማድረግ |
| • የአፍሪካ ሕዝቦች መተዳደሪያ አይነቶችን ያብራራሉ፡፡<br>• እነዚህን የመተዳደሪያ አይነቶች ከአየር | **1.7.2. የአፍሪካ ሕዝቦች መተዳደሪያ** (3 ክ/ጊዜ)<br>• በስምጥ ሸለቆ አካባቢ የአሳ ማጥመድ ተግባር | • በተለያዩ ቦታዎች የሰፈሩ ሕዝቦች መተዳደሪያዎችን ለይተው እንዲያውቁና ምርቶቹም ከአየር ንብረትና ሀብት ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲገልፁ ተማሪዎችን መመደብ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| ንብረትና ዕፅዋት ጋር በማዛመድ አንድነታቸውን ይገልፃሉ፡፡ | • በምድር ወገብ አካባቢ ያሉ ዝቅተኛ ቦታዎችና ያላቸው ሀብት ለምሳሌ በናይጄሪያ /የተፈጥሮ ዘይት/ የኰኰነት ፓልም፣ አሳ ማጥመድ፣ የምግብ ፍራፍሬ ለምሳሌ ካሳቫ<br>• የከፍተኛ ሳቫና አካባቢ ሕዝብ፡- የሥጋ ከብት እርባታ ለምሳሌ /ኬንያ፣ ኢትዮጵያ/<br>• በምድር ወገብ አካባቢ ከፍተኛ ቦታዎች የሚመረቱ ጥራጥሬ፣ ሻይቅጠል፣ ቡና፣ አበባ፣ አትክልትና የወተት ውጤቶች | • በገጠር አካባቢ በተለይም በምድር ወገብ ዝቅተኛ ቦታዎች የሚከናወኑ ዋና ዋና የሕዝብ ተግባራትንና መተዳደሪያቸውን በተመለከተ እንዲለዩና ለምን ሊሆን እንደቻለ እንዲወያዩ ማድረግ<br>• በኢትዮጵያ የአሳ ማስገር ስራ ምን ያህልና በየትኛው ወንዝ ላይ እንደሚከናወን እነንዲመዘግቡና ውይይት እንዲካሄዱ ማድረግ<br>• የሥጋ ከብት እርባታን አስመልክቶ ውስን ጥናት እንዲካሄድ ማድረግ<br>• በአፍሪካ ያሉትን ቁልፍ መንገዶች /ባቡር ሀዲዶችን በካርታ ላይ ማመልከት፡፡ ጦርነትና ብጥብጥ በትራንስፖርትና መገናኛ መስመሮች ላይ ያለውን ተፅዕኖ ተማሪዎች እንዲወያዩ ማድረግ፡፡ |
| • በከተማ ባለው አሰፋፈር ምክንያቶች ላይ ይወያያሉ፡፡<br>• ምሳሌዎችን በመለየት ያስቀምጣሉ፡፡<br>• አቢይ/ቁልፍ መገናኛና ትራንስፖርት | 1.7.3. **የሕዝብ ስርጭትን፣ አሰፋፈርንና አኗኗርን የሚወስኑ ነገሮች** *(2 ክ/ጊዜ)*<br>• ለከተማ ሕዝብ አሰፋፈር ወሳኝ ምክንያቶች (ምሳሌ የአዲስ አበባ እና የሞምባስ ከተሞች አሰፋፈር) | • ተማሪዎች ካርታን በመመልከት ስለ ከተማ ሕዝብ አሰፋፈር ሁኔታ የሚያውቁትን ያህል እንዲያብራሩ ማድረግ<br>• የአዲስ አበባንና ሞምባሳ ከተማ ሕዝብ አሰፋፈርን በተመለከተ ውስን ጥናት እንዲያካሂዱ ማድረግ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| መስመሮችን ማወቅ እና የሕዝብ አለመረጋጋት በፀጥታ መደፍረስ ላይ ያለውን ተፅዕኖ ያብራራሉ፡፡ | • መገናኛ መንገዶችና የፀጥታ ጉዳዮች ምሳሌ ጦርነት፣ ብጥብጥ ወይም የሕዝብ አለመረጋጋት፡፡ | • አዲስ አበባ ለም አፈር በያዘ ሸለቆና ጠቃሚ ወንዞች አካባቢ የተመሰረተች መሆኑዋን እንዲሁም ሞምባስ ደግሞ የወደብ ከተማና የባቡር ትራንስፖርት የተጀመረባት መሆኑዋን መግለፅ፡፡ የአዲስ አበባ ቡና አሻጊ ሰራተኞችንና የሞምባስ ወደብ ሰራተኞችን ማወዳደር፡፡ ከዚህ በመነሳት ስራዎቸ ሁሉ ከአየር ንብረት ጋር መያያዛቸውን መግለፅ<br>• ጦርነትና አለመረጋጋት /ብጥብጥ/ በሕዝብ እንቅስቃሴና በመገናኛና ትራንስፖርት ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ እንዲወያዩ ማድረግ፡፡ |

## ምዘናና ግምገማ

እያንዳንዱን ተማሪ ከዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ ምን እንደጨበጡ መመዘን እና የተቀመጠለትን አላማ ለማሳካት የተቀመጠው ዝቅተኛ መስፈርት ውጤት ማምጣት አለማምጣቱን ማረጋገጥ፡፡ የተቀመጠውን ዝቅተኛ ተፈላጊ ውጤት ያመጣ አንድ ተማሪ የሚከተሉትን ነገሮች መጨበጥ ይገባዋል፡፡

- የአፍሪካ ይዘት /ስፋት/ እና ቅርፅ ከሌሎች ክፍለ አህጉራት ጋር ማወዳደር
- በአፍካ የሚገኙ የቋንቋ  ግንዶችን ስም /ዝርያዎችን/ መጥራት መቻል፡፡
- አፍሪካ የተለያዩ ቆዳ ቀለም ሕዝብ መኖሪያ መሆኗን ማድነቅ
- ጥንታዊ ግብፅና ካርቴጅ የአፍሪካ ቀድምት ስልጣኔ ማዕከል መሆናቸውን መገንዘብ፡፡
- የጥንታዊ ግብፃዊያንና ፊንቄዎች ስልጣኔ ጠቀሜታን መገለጫዎችን መዘርዘርና ያበረከቱትን መረዳት
- ጥንታዊ ማሊ፣ ሩንጂ እና ዝምባቡዌ የቅድመ ቅኝ አገዛዝ ዘመን ግዛት መሆናቸውን መረዳትና የነበሩትን የስልጣኔ ደረጃ ማድነቅ
- የሲራራ ንግድ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከማገናኘት አኳያ ያለውን አስተዋፅኦ ማድነቅ
- የጥንታዊት ዝምባቢዌን የሥነ ሕንፃ ጥበብ ማድነቅ እና የሰው ልጆችን መተዳደሪያ ሥራና የሕዝብ ስርጭትን የሚወስኑ ነገሮች ላይ ጥሩ ውይይት ማድረግ መቻል ተሟልተው መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡

ከዚህ ከዝቅተኛው ውጤተ በታች ያመጣን ተማሪ የተለየ ጊዜ ይዞ ድጋፍ መስጠት ይጠበቃል፡፡ ነገር ግን ከዝቅተኛ የብቃት መለኪያ በላይ አልፎ የሄደውን ተማሪ ለበለጠ ውጤት ማበረታታትና ማድነቅ ይገባል፡፡

## ***ምዕራፍ ሁለት፡- የመሬት መዋቅር*** *(12 ክ/ጊዜ)*

***አጠቃላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-*** ከዚህ ምዕራፍ ፍፃሜ በኋላ ተማሪዎች፡-

- የመሬትን መዋቅርና ክፍሎች /ቅርፊተ መሬትን፣ እምብርተ መሬትንና ማዕከለ መሬትን ከምን ከምን እንደተሰሩም ጭምር ይገልጻሉ፡፡
- የመሬት ውስጣዊ እንቅስቃሴና የሚያመጣውን የመሬት መሰንጠቅና የመሬት መንቀጥቀጥን ይገነዘባሉ፡፡
- የአለትን አፈጣጠር፣ አይነትና የሚሰጡትን ጠቀሜታ ይለያሉ፡፡
- የኬንትሮስና ኬክሮስ መስመሮች ጥቅም ያብራራሉ፣ እንዲሁም የሜሪዲያን ምንነት ይረዳሉ፡፡
- ንድፍ ካርታን ይስላሉ፡፡

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| *ተማሪዎች ከዚህ ርዕስ በኋላ፡-*<br>• የካርታን ምንነት ይተረጉማሉ፡፡<br>• የካርታን ጥቅም ያብራራሉ፡፡<br>• የአፍሪካን ካርታ በመሳል የሕዳግ መረጃዎችን ማሳየት ይችላሉ፡፡ | ***2. የመሬት መዋቅር***<br>**2.1. ካርታን በመጠቀም መረጃዎችን ማግኘትና መጠቀም** *(6 ክ/ጊዜ)*<br>• ካርታን መጠቀም<br>• የሕዳግ መረጃዎች (ርዕስ፣ አቅጣጫ፣ ቀን ወይም ዘመን፣ የካርታ መፍቻ) | • በካርታ ጥቅሞችና ካርታን ማን እንደሚሰራ ወይም ለምን እንደሚጠቀም መወያየት፣<br>• ከአዲስ አበባ የመንግስት ካርታ ቢሮ ሰራተኛ ውስን ጥናት እንዲያቀርብ ማድረግ፣<br>• በክፍል ውስጥ 1፡50.000 የሆነ ካርታ መስፈርት ከነሕዳግ መረጃው ቢያቀርብላቸው፣<br>• ተማሪዎቹ ከዚህ ካርታ ሕዳግ መረጃ ምን እንደሚያገኙ በመጠየቅ እንዲወያዩ ማድረግ፣ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | • ካርታ እንዴት እንደሚዘጋጅ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ባለሙያዎች ጠይቀው ዘገባ ማቅረብ<br>• ተማሪዎች በደብተራቸው ለይ የአፍሪካን ካርታ በመሳል ከተሞችን ፣ ወንዞችን፣ የተራራ ሰንሰለቶችን እንዲያሳዩ ማድረግ<br>• የካርታ መፍቻን እንዲያስታውሱ እና እንዲጠቀሙ ማድረግ፡፡<br>• ካርታው የተሰራበትን ዘመን መለየት፡፡ ለምን እንደሚጠቀሙ መጠየቅ |
| • የመሬት ንጣፋዊ ክፍሎችን ማብራራት ይችላሉ፡፡<br>• ቅርፊተ መሬት ከምን ከምን ነገሮች ነው የተሰራው የሚለውን ጥያቄ ይመልሳሉ፡፡ | 2.2. **የመሬት ንብርብሮች (ክፍሎች)** *(4 ክ/ጊዜ)*<br>• ቅርፊት መሬት፣ ማዕከለ መሬት እና ዕምብርተ መሬት እንዲሁም ጥልቀታቸው<br>• ቅርፊተ መሬት ከምን ተሰራ? | • መሬት ከሶስት ንብርብሮች መሰራቷን፣ የቅርፊተ ማዕከለና ዕምብርተ መሬትን ጥልቀት ላይ እንዲሁም በዕምብርተ መሬት ውስጥ ከፍተኛ ሙቀት መኖሩን ምክንያቱን ለመረዳት መወያየት<br><br>• የመሬትን የላይኛውን ክፍል ፎቶ ግራፍ በማንሳት ቅርፊተ መሬት ውሃ፣ አፈርና አለትን እንደሚይዝ ማብራራት |

| **የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች** | **ይዘቶች** | **ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች** |
|---|---|---|
| • የአለት አይነቶችና አፈጣጠራቸውን ይለያሉ፡፡<br>• የአለቶችን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያብራራሉ፡፡<br>• በኢትዮጵያ አለቶች እየሰጡ ያሉትን ጥቅሞች ያረጋግጣሉ፡፡ | 2.3. **የአለት አይነቶችና አፈጣጠራቸው** *(2 ክ/ጊዜ)*<br>• የአለት አፈጣጠር<br>• የአለቶች አይነትና ጥቅማቸው (የኖራ፣ ቅልጥ እና ዝቅጠት አለቶች)<br>• የአለቶች ኢኮኖሚያዊ ጥቅም | • የቅልጥ አለት በመሬት ውስጣዊ ሀይል ማዕከል መሬት ወጥቶ ወደ አለትነት እንደሚቀየር ማብራራት<br>• ስለ ኖራዊ፣ ቅልጥ እና ዝቅጠት አለት ውይይት በማድረግና ናሙና አምጥቶ ማሳየት<br>• ተማሪዎችን ስለሚያውቁት ጠቃሚ አለት እንዲናገሩና እንዲወያዩ መጠየቅ፣ ስለ ማዕድናት ለምሳሌ ስለ ወርቅ፣ መዳብ እና ስለ ከበሩ ድንጋዮች እንዲወያዩ ማድረግ<br>• እምቅ ማዕድናት የሚገኙባቸውን የኢትዮጵያ ከርሰ ምድር በካርታ ላይ እንዲያሳዩና እንዲወያዩ ተማሪዎችን መጠየቅ |

## ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን አጥጋቢ ውጤት ማምጣት አለማምጣታቸውን ለመለየትና ድጋፍ ለመስጠት ያመች ዘንድ በተከታታይ እስከ ምእራፉ መጨረሻ ድረስ እያንዳንዱን ተማሪ መመዘን፡፡

የሚጠበቀውን ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገበ ተማሪ ማወቅ የሚገባው፣

- የካርታን ምንነት ይተረጉማል
- ኬንትሮስንና ኬክሮስን ስለተጓዳኝና ዋልቴ ጋር አያይዞ ማብራራት መቻል
- የአፍሪካን ካርታ በመሳል መልክአ ምድራዊ ሁኔታ ማሳየት፣ የሕዳግ መረጃዎችን መግለፅ፣ የቦታዎችን አቅጣጫ ማመልከት፣ የመሬትን ንብርብሮች መግለፅና ቅርፊተ መሬት ከውሃማ አካልና ከየብስ ክፍል የተሰራች መሆኑዋን  መግለጽ ይኖርበታል/ይኖርባታል፡፡
- የአለት አይነቶችንና አፈጣጠራቸውን መለየትና አለቶች የሚሰጡትን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ማብራራት መቻል ይጠበቃል፡፡

እነዚህን ዝቅተኛ መስፈርት ያላሟሉ ተማሪዎች ካሉ የተለየ ፕሮግራም ተይዞላቸው የተለየ ድጋፍ መስጠት ነገር ግን ከዚህ መስፈርት ያለፈውን ተማሪ ማድነቅና ለበለጠ ስራ ማበረታታት ይገባል፡፡

## ***ምዕራፍ ሦስት፡- ሥርአተ ምህዳር እና ተፅኖ የሚያሳድሩ ችግሮች*** *(16 ክ/ጊዜ)*

***አጠቃላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፦*** *ከዚህ ምዕራፍ ፍፃሜ በኋላ ተማሪዎች፦*

- *የአፍሪካ የዕፅዋትና የዱር አራዊት ስርጭትን፣ ጠቀሜታንና ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮችን ያውቃሉ፡፡*
- *የንፁህ ውሀ በበቂ ሁኔታ መኖርና ያጋጠሙትን ችግሮች ያውቃሉ፡፡*
- *የተፈጥሮ ሀብቶችን እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል ያውቃሉ፡፡*

| **የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች** | **ይዘቶች** | **ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች** |
|---|---|---|
| *ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፦*<br>• የአፍሪካ የተፈጥሮ ዕፅዋቶች የሚገኙበትን ቦታ በመለየት በካርታ ላይ ያመለክታሉ፡፡<br>• ዋና ዋና የአፍሪካ የዱር እንስሳትን ይዘረዝራሉ፡፡<br>• እነዚህን አራዊቶች ከአካባቢያቸው ጋር ያዛምዳሉ፡፡<br>• እንስሳትና ዕፅዋት የብዝሀ ህይወት ክፍሎች መሆናቸውን ይረዳሉ፡፡ | **3.1. የተፈጥሮ ሀብቶች**<br>**3.1.1. የተፈጥሮ ዕፅዋትና የዱር እንስሳት** (*6 ክ/ጊዜ*)<br>• የተፈጥሮ ዕፅዋትና የዱር እንስሳት ስርጭት<br>• የተፈጥሮ ዕፅዋትና የዱር እንስሳት የሚሰጡት ሳይንሳዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ<br>• በተፈጥሮ ዕፅዋትና ዱር እንስሳት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች (የሰዎች ድርጊት፣ የንቃተ ህሊና ማነስ፣ ድህነት) በተፈጥሮ ምክንያት ለምሳሌ የአየር መዛባትና ሰደድ እሳት | • የአፍሪካ ካርታን በመጠቀም በአፍሪካ የሚገኙ የዕፅዋት አይነቶችንና ስርጭታቸውን እንዲያስተውሉ ማድረግ (እነርሱም የምድር ወገብ አካባቢ ደኖችን፣ የሳር ምድር፣ የበረሀማና ከፊል በረሃማ አካባቢ ዕፅዋቶችን እንዲሁም የሜዲትራኒያንና የሞቃታማ ከፍተኛ ቦታዎቸ ዕፅዋቶችን) በሚገባ እንዲለዩ ማድረግ፡፡ እንዲሁም በካርታ ላይም እንዲያመላክቱ ማድረግ<br>• በተለያዩ አካባቢዎች ከሚኖሩት እንሰሣት መካከል ከአንድ በላይ እጽዋት በሚገኙባቸው አካባቢዎች የሚኖሩት የተሻለ ነዋሪ መሆናቸውን አስመልክቶ ውይይት ማድረግ፡፡ እነዚህን የዱር |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • ዕፅዋቶች ከጠፉ የዱር እንስሳትም አብረው እንደሚጠፉ ይገነዘባሉ፡፡<br>• የሰው ልጅ እንቅስቃሴ በዱር እንሰሣት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያደርሱ ያብራራሉ፡፡<br>• የአየር መዛባትን መከላከል እንደሚቻል ያንጸባርቃሉ፡፡ | • የብዝሃ ህይወት መቀነስ | እንሰሣት ተማሪዎች እንዲዘረዝሩ ማድረግ<br>• ደኖች ቢጨፈጨፉ የዱር እንስሳት ላይ የሚከሰቱትን ችግሮች እየዘረዘሩ መወያየት፡፡ በመጥፋት ላይ ያሉ የዱር አራዊቶችን መግለጽ፡፡ የዱር እንስሳትና ዕፅዋት ሣይንሣዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም (ምሣሌ ከእጽዋት መድሃኒትን ለማግኘት ጥናት ለማካሄድ) በሚገባ እንዲወያዩ ማድረግ፡፡ ዕፅዋቶችና የዱር እንስሳቶች እየደረሰባቸው ያለው ጥፋት በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመረ መሆኑንም መግለፅ<br>• ተማሪዎች በሁለት ቡድን ከተከፈሉ በኋላ በትክክል የማያውቋቸውን እንስሳትን በስዕል በማሣየት ከየት እንደመጡና የት አካባቢ እንደሚኖሩ እንዲገልፁ ሙከራ መስጠት |
| • የሰው ልጅና ውሃ ያላቸውን ግንኙነት ያብራራሉ፡፡<br>• በአፍሪካ የመጠጥ ውሃ መገኘትንና እጥረትን ያወዳድራሉ፡፡ | **3.1.2. ውሃ፡ አፈርና አየር**<br>*(4 ክ/ጊዜ)*<br>• ውሃ ለሕይወት ያለው ጠቀሜታ<br>• ለመጠጥ ውሃ ችግሮች መንስኤ (የንፅህና ጉድለት፣ የከተሞች መጨመር፣ የኢንዱስትሪ | • ተማሪዎችን ውሃ ለምን እንደሚያስፈልግ እንዲወያዩ መጠየቅ፡፡ በአፍሪካ ምን ያህል ንፁህ ውሃ እንዳለና የአጠቃላይ የውሃ ይዘቱን መጠን የተመለከተ መረጃ መስጠት |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • የመጠጥ ውሃን ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶችንና የስጋቶችን መነሻዎችን ይተነብያሉ፡፡<br>• በአፍሪካ የአፈር ለምነት የሚከላበትን ሁኔታ ይለያሉ፡፡<br>• በከተሞች አካባቢ የሚከሰተውን የአየር ብክለት ይተነትናሉ፡፡ | መጨመርና የሕዝብ ብዛት)<br>• የአፈር ለምነት ችግር<br>• በከተሞች የአየር ብክለት መንስኤዎች | • ለተለያዩ ጉዳዩች በሚያስፈልገውና አሁን ባለው የውሃ መጠን መካከል ባለው ልዩነት ላይ መወያየት<br>• ተማሪዎችን በጥንድ በመከፋፈል ንፁህ የመጠጥ ውሃ ያለበትን ችግር /አደጋ/ እንዲወያዩ ማድረግ ( ምሣሌ የንፅህና ጉድለት፣ የከተሞች መስፋፋት፣ የኢንዱስትሪ ማደግ፣ የሕዝብ ቁጥር መጨመር)<br>• ተማሪዎች የማጠቃለያ ዘገባ እንዲያቀርቡ በማድረግ ውይይቱን ማጠቃለል<br>• በፎቶግራፍ በማስደገፍ የባህርዳር፣ ጎንደርና ደሴ ሕዝብ ብዛትንና የተሰሩ አዳዲስ ሕንፃዎችን አስመልክቶ ውስን ጥናት ማካሄድ<br>• ተማሪዎች በአፈርና በአየር ላይ የሚመጡ አደጋዎችን እየዘረዘሩ እንዲወያዩ ማድረግ<br>• በአዲስ አበባ ያለውን የአየር ብክለት በፎቶ ግራፍ አስደግፎ ውይይት ማካሄድ<br>• የአፈር፣ የውሃ፣ የአየር፣ የዕፅዋትና የእንስሳት እንክብካቤ ያላቸውን ትስስር ሃሣባዊ ካርታ አማካኝነት ማሣደግ፡፡ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • ዕፅዋትን መንከባከብ ከሌሎች ተፈጥሮ ሀብቶች ጋር ያለው ቀጥተኛ ትስስርን ይገነዘባሉ፡፡<br>• የአየርንና ውሃን ብክለት እንዴት መቆጣጠር እንደሚቻል ይለያሉ<br>• በቤት ውስጥ ያለንን ውሃ ንፅሕና ለመጠበቅ ያለን ተነሳሽነት/ፍላጎት/ እና ንፁህ ውሃ መጠቀም ያለውን ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ፡፡ | **3.1.3. የተፈጥሮ ሀብትን ለመንከባከብ የሚወሰዱ ዕርምጃዎች** *(6 ክ/ጊዜ)*<br>• ዕፅዋትን መንከባከብ ዋነኛ ቁልፍ መሆኑን<br>• የአየር እና የውሃ ብክለትን መቆጣጠር<br>• አማራጭ የመከላከያ ዘዴዎችን መጠቀም<br>• ዩ.ኤን.ኢ.ፒ ወይም የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ እንክብካቤ ፕሮግራምና ሃላፊነታችን | • በት/ቤታቸውና በአካባቢያቸው ንጽህ ውሃ እንክብካቤ ላይ ተማሪዎች እንዲሳተፉ የሚያስችል የፕሮጀክቶችን ንድፍ ወይም ዲዛይን እንዲሰሩ ማድረግ፡፡<br>• ተማሪዎችን በሶስት ቡድን በመክፈል አንዱ ቡድን በዕዋት እንክብካቤ ላይ፣ ሌላኛው ደግሞ በውሃ እንክብካቤ የቀረው በአየር ብክለት መከላከያ ከባለሙያ ጠይቀው ዘገባ አንደያዘጋጁና እንዲወያዩ ማድረግ፡፡ በመቀጠልም የእያንዳንዱ ቡድን መሪ ወይም ተወካይ ለክፍል ጓደኞቻቸው ዘገባ እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡ ተማሪዎች የሚሰጡትን አስተያየት መምህሩ በጥቁር ሰሌዳ ላይ አስተካክሎ ማስፈር<br>• በመቀጠልም ተማሪዎችም ፍሬ ሃሣቡን በማስታወሻቸው እንዲያሰፍሩ ማድረግ፡፡<br>• የተበከለ ውሃ ሲጠጡ የሚያማቸው ከሆነ እንዴት ንፁህ ውሃን ማግኘት እንደሚችሉ ይወያዩ፡፡ ንፁህ ውሃ በተግባር ፈትሾ ማግኘት የሚቻልበትን መንገድ እንዲጠቀሙ ማድረግ፡፡ ውሃ ከምንጩ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | እስከሚጠጣ ድረስ እንዴት በንጽህና ሊያዝ እንደሚገባ የሚያውቅ ሰው ጠይቀው ዘገባ እንዲያዘጋዳና እንዲያቀርቡ ማድረግ<br>• ኬኒያ ስለሚገኘው የተባበሩት መንግስታት አካባቢ እንክብካቤ ፕሮግም ውስን ጥናት እንዲቀርብ ማድረግ፡፡ ማንኛውም ሰው ሀገር በቀል እንስሳትን የመንከባከብ ግዴታ እንዳለበት ተማሪዎችን ማወያየት፡፡ |

## ምዘናና ግምገማ

አላማውን መሰረት በማድረግ በምእራፍ ይዘት በሙሉ እያንዳንዱ ተማሪ በተከታታይ ተመዝኖ የሚጠበቀውን ዝቅተኛ ውጤት ማምጣት አለማምጣታቸውን ማወቅ፡፡

የሚጠበቀውን ዝቅተኛ ውጤት የሚያሚሏ/የምታሚላው ተማሪ

- በአፍሪካ የሚገኙ የተፈጥሮ ዕፅዋቶችን መለየት
- በአፍሪካ የሚገኙትን የዱር አራዊት አይነቶችን መለየት
- በአፍሪካ ካርታ ላይ የዕፅዋት ስርጭትን ማመልከት
- በአፍሪካ የሚገኙ ዕፅዋትና እንስሳት ጠቀሜታን መረዳት
- ዕፅዋትና እንስሳት እርስ በርስ ያላቸውን ዝምድና መተንተን
- የሰው ልጆች በእጽዋትና በዱር አራዊት ላይ የሚያሳድሩትን አሉታዊ ተፅእኖ መረዳት
- በዕፅዋትና የዱር እንሰሣት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያመጡ ተፈጥሮአዊ መንስኤዎችንና የመቆጣጠሪያ መንገዶችን መለየትና ለመተግበር ፍላጎት ማሣየት
- ንፁህ የመጠጥ ውሃን አቅርቦትና አጠቃቀም ማወዳደርና ልዩነቱን ማወቅ
- ንፁህ የመጠጥ ውሃ ለማግኘት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ማወቅ
- በአፍሪካ የአፈር ሀብትን ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ማወቅ
- የእጽዋት እንክብካቤ ከሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች አንክብካቤ ጋር ያላቸውን ተዛምዶ መተንተን
- የአየርና ውሃ ብክለትን እንዴት መከላከል እንደሚቻል መወያየት
- ለቤት ውስጥ ውሃን ንጽህ አድርጎ ለመጠቀም ፍላጎት ማሣደር

ይህንን ዝቅተኛ ውጤት ላላመጣ ተማሪ ልዩ ድጋፍ ማድረግና በጣም አልፎ ለሄደ ተማሪ ደግሞ አድናቆትን መስጠት፡፡

## ምዕራፍ አራት፡- ሕዝባዊ ጉዳዩች *(17 ክ/ጊዜ)*

***አጠቃላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፦*** ከዚህ ምዕራፍ ፍፃሜ በኋላ ተማሪዎች፦

- ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ በአፍሪካ የሚያደርሰውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ይተነትናሉ፡፡
- የመልካም አስተዳደር እጥረት በአፍሪካ እያስከተለ ያለውን ችግር ያረጋግጣሉ፡፡
- በአፍሪካ የተመሰረቱ ክልላዊ ድርጅቶችና አላማቸው እንዲሁም ያላቸውን ሽፋን ይለያሉ፡፡
- በአፍሪካ ፈጣን የሕዝብ ዕድገት የሚያስከትለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ይተነትናሉ፡፡

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| *ይህንን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ተማሪዎች፦*<br>• ኤች አይ ቪ. ኤድስ በአፍሪካ እያደረሰ ያለውን ጉዳት ይተነትናሉ፡፡<br>• ጉዳቱን ለመከላከል ሊወሰድ በሚገባው መፍትሄ ላይ ይወያያሉ፡፡ ይተገብራሉ፡፡ | **3. የሕዝባዊ ጉዳዩች**<br>**3.1. ሕዝብ ነክ ጉዳዮች**<br>**4.1.1. ኤች አይ ቪ. ኤድስ በከፍተኛ ፍጥነትመስፋፋት በአፍሪካ እያስከተለ ያለው አሉታዊ ተፅዕኖ** *(3 ክ/ጊዜ)*<br>• በአፍሪካ የኤች አይ ቪ. ኤድስ ስርጭት ያለበት ሁኔታ<br>• ኤች አይ ቪ. ኤድስ በአፍሪካ ላይ የሚያደርሰው ችግር | • የአለም ጤና ድርጅትና በጤናው መስክ እየተጫወተ ያለውን ሚና በተለይ ደግሞ በበሽታ የተጠቁና ያልተጠቁ ሰዎችን መረጃ በመለየት ያለውን ፋይዳ ለተማሪዎች መግለፅ፡፡ ተማሪዎች ስታትስቲካዊ መረጃውን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው የተረዱ መሆናቸውን መጠየቅ<br>• የአለም ጤና ድርጀት በአፍሪካ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ዙሪያ ያገኘውን መረጃ (ቁጥር) ለተማሪዎች በማቅረብ ምን እንደሚሉ ማወያየት |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| | | • የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሕሙማን ቁጥርን ከተለያዩ ሀገሮች በመሰብሰብ ማወዳደር፣<br>• በደቡብ አፍሪካ በአንድ ቤተሰብ ላይ የተጠናውን ውስን ጥናት ማቅረብ<br>• ተማሪዎች የሽረሪት ስዕላዊ መግለጫ ሰርተው እንዴት ቤተሰብ በሙሉ ችግር ውስጥ እንደሚገቡ (በበሽታው ቢጠቁ) መጠየቅ፡፡ አንድ ሀገር የተማሩ ወጣቶችን በቀላሉ ማጣት የሌለባት መሆኑን ትኩረት ሰጥቶ መግለጽ |
| • የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በአፍሪካ የሚያስከትለውን ውጤት ያብራራሉ፡፡<br>• በየአካባቢያቸው በሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምክንያት ምን ምን ችግሮች እንደሚከሰቱ ዘገባ ያቀርባሉ፡፡ | **4.1.2. የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ውጤት** *(4 ክ/ጊዜ)*<br>• የፍላጎትና ሀብት አለመጣጣም<br>• ሥራ አጥነት<br>• ድህነት | • ሚና ጨዋታ በማዘጋጀት በሕዝብ ቁጥር መጨመር የሚመጡ ውጤቶች ላይ ሀሳብ እንዲሰነዝሩ ማድረግ<br>• ጨዋታው ማተኮር ያለበት በፍላጎትና ሀብት አለመጣጣም፣ በሥራ አጥነት እንዲሁም በድህነት ላይ ሊሆን ይገባል፡፡ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቋሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • የሕፃናትን መብት አስመልክቶ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስምምነት ይዘትን ይለያሉ፡፡<br>• በአካባቢቸው የሚታዩ የሕፃናት መብት ጥሰትን ይገልፃሉ፡፡<br>• ሕፃናት እንዴት መብታቸውን መጠበቅ እንደሚችሉ ያብራራሉ፡፡ | **4.2 የመብትና የደህንነት ጉዳይ**<br>**4.2.1. የሕፃናት መብት ጥሰትን መዋጋት**<br>(3 ክ/ጊዜ)<br>• የሕፃናት መብትን የሚደግፉ ሕጎችና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች<br>• የመብት ጥሰትን ማስወገጃ መንገዶች (ሀላፊነት ለሚሰማቸው ጎልማሶች መንገር፣ ስለ ጥሰቱ አደገኛነት ለጓደኞቻቸው ማስረዳት … ሌሎች ሕጋዊ መከላከያዎችን መጠቀም) | • ተማሪዎች ስለ ሕፃናት መብት ጥሰት የሚያውቁትን ያህል እንዲወያዩ ማድረግ፣<br><br>• ሕፃናትን በሚደበድብና ጎረቤት እንዲሁም ሴት ልጅን አስገድዶ በመጥለፍ ተግባር ላይ የተሰማራ ወንጀለኛ  እንደ ገፀ ባህሪያት በመቁጠር በድራማ ማቅረብ፡፡<br>• ተማሪዎች ከድራማው ምን እንዳገኙ ውይይት መክፈት<br>• የጥንቃቄ መመሪያዎችን መጠቀም ለምሳሌ የት እንደምትሔዱ ከማን ጋር እንደሆናችሁ ለቤተሰብ እንዲናገሩ ማድረግ፡፡<br>• መጀመሪያ ተማሪዎችን መጠቀም የሚገባቸውን መብቶች እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፡፡ ከዚያ በኋላ በተ.መ.ድ. ሕፃናት መብት ስምምነት ውስጥ የተቀመጡትን መብቶች በፖስተር ለጥፎ ማሳየት፡፡ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • በአፍሪካ መልካም አስተዳደር እጦት ምሳሌዎችን ማስቀመጥና የመልካም አስተዳደር ችግርን ያብራራሉ፡፡<br>• በአካባቢያቸው ያሉትን መልካም አስተዳደርና የመልካም አስተዳደር እጦትን አስመልክተው ዘገባ ያቀርባሉ፡፡ | **4.2.2. በአፍሪካ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር እጦት ምሳሌዎች** *(3 ክ/ጊዜ)*<br>• ሙስና<br>• የርስ በርስ ጦርነት ውጤት<br>• የተማሪዎች የክፍል ምርጫ ዘመቻ፤ እናንተ ብትመረጡ የመልካም አስተዳደር ችግርን እንዴት ታሻሽሉታላችሁ? | • ተማሪዎችን ስለ መንግስታት አሰራር በቴሌቪዥን  የተመለከቱት፣ የሰሙትና በሬዲዮ ያዳመጡት እንዲሁም ያነበቡት ነገር ካለ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ማድረግ<br>• አንድን ባለሙያ ሰው በመጋበዝ በአካባቢያቸው መንግስት እንዴት እንደሚሰራ/የመንግስት አሰራርን እንዲያስረዳቸው በማድረግ ማስተማር፡፡<br>• መልካምና መልካም ያልሆኑ የአስተዳደር ዳር መገለጫዎችን ነጥቦችን አንስቶ ማወያየት<br>• የምርጫ ዘመቻቸውን እንዲያቅዱ ማድረግ፡፡<br>• እናንተ ብትመረጡ የመልካም አስተዳደር እጦትን እንዴት እንደምታሻሽሉ ዘገባ አድርጉ፡፡ |

| የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች | ይዘቶች | ጠቃሚ የመማር ማስተማር ክንውኖችና ስልቶች |
|---|---|---|
| • የአፍሪካ ክልላዊ ድርጅቶች እና የነዚህ ድርጅት አባል ሀገሮችን መለየት<br>• የአፍሪካ ክልላዊ ድርጅቶች የአጋርነት አላማዎችን መገንዘብ<br>• በአፍሪካ አንድነት ድርጅት አመሰራረት እና ወደ አፍሪካ ህብረት ስለመቀየሩ ይወያያሉ፡፡ | **4.3 አጋርነትን ለማጠናከር የተያዙ እቅዶች** *(4 ክ/ጊዜ)*<br>• ዋና ዋና ክልላዊ የአፍሪካ ድርጅቶች የሚባሉት (ኮ.ሜ.ሳ፣ ኢ.ኮ.ዋ.ስ፣ ሰ.ድ.ክ፣ የናይል ተፋሰስ ሀገሮች፣ ኤ.ዩ)<br>• የኢ.ኢ.ድ ምሥረታ<br>• ዋና ዋና የአፍሪካ ክልላዊ ድርጅቶች አላማ | • የክልላዊ ድርጅቶችን ስም በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ተማሪዎች ስለነርሱ ምን ያህል እንደሚያውቁ መጠየቅ፡፡ ስለ እነዚህ ድርጅቶች ተግባርና ዓላማ ማስተማር፡፡ የድርጅቶቹ አባል ሀገሮች እነማን እንደሆኑ የመለየት ተግባር ማከናወን፡፡<br>• የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አመሰራረትና እንዴት ወደ አፍሪካ ሕብረት እንደተቀየረ ማወያየት<br>• የአፍሪካ ሕብረት ፅ/ቤት ኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑ ለኢትዮጵያ ምን ምን ጥቅም እንዳለው ተማሪዎችን በመጠየቅ እንዲገልፁ ማድረግ<br>• በድርጅቶቹ ዓላማ ላይ በመወያየት የተገኘውን ሀሳብ ሰንጠረዥ ለያንዳንዱ በመስራት አላማዎቹን በመፃፍ ማስተማር |

## ምዘናና ግምገማ

ከተቀመጠው የብቃት መለኪያ አኳያ ከምዕራፉ መጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ እያንዳንዱን ተማሪ በመመዘን የሚጠበቀውን ዝቅተኛ ውጤት መድረስ አለመድረሱን በሚከተለው ሁኔታ ማረጋገጥ
አንድ የተቀመጡትን ዝቅተኛ ውጤት የሚያስመዘግብ ተማሪ ማወቅ ያለበት

- በአፍሪካ የኤች. አይ. ቪ/ኤድስ በሽታ መስፋስትንና ያስከተለ ያለውን አሉታዊ ተፅዕኖ
- በአፍሪካ ከፍተኛ የሕዝብ ዕድገት የሚያመጣውን አሉታዊ ተፅዕኖ አስመልክቶ ሪፖርት ማድረግ፣ በአካባቢያቸውም ያለውን ሁኔታ አብረው መግለፅ
- በአፍሪካ ለመልካም አስተዳደር እጦት መንስኤዎችን መግለፅና አጭር ፅሑፍ በአካባቢያቸው በሚታየው መልካም አስተዳደር አለመኖርና መኖር ላይ መፃፍ መቻል፡፡
- የሕፃናትን መብት የሚደግፈው የተ.መ.ድ ኮንቬንሽን መለየት በአካባቢያቸው የሚታዩ የሕፃናት መብት ጥሰትን መተቸት፣ ማውገዝ
- ወጣት ወንጀለኝነትን መከለካል ወንጀልን መተርጎም፣ በአፍሪካ የሚገኙ ክልላዊ ድርጅቶችን ስም መዘርዘር፣ አላማቸውንና አባል ሀሮችንም መለየት
- የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አመሰራረትንና እንዴት ወደ አፍሪካ ሕብረት እንደተዛወሩ ማወቅ፡፡

ይህንን ዝቅተኛ ውጤት ያላሳካን ተማሪ ልዩ ፕሮግራም ተይዞለት ልዩ ድጋፍ መስጠት፡፡ ከሚጠቀመው የብቃት መለኪያ በላይ ተማሪ ካለ ግን ከፍተኛ አድናቆት በመስጠት ማበረታታት ይገባል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# በአፍሪካ መኖር

**ለምዕራፉ የተመደበው ጠቅላላ ክፍለ ጊዜ፡ 23**

**የምዕራፉ ትምህርት ሲጠናቀቅ የሚጠበቁ ውጤቶች**

*ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኋላ፡-*

- ስለ አፍሪካ የቆዳ ስፋት፣ ቅርጽ፣ መገኛና፣ ዋና ዋና ቋንቋዎችን ያብራራሉ፡፡
- ስለ አፍሪካ ጥንታዊ ስልጣኔ ቅድመ ቅኝ ግዛት ዘመን ሀገሮች ይገነዘባሉ፡፡
- በአፍሪካ ሕዝቦች አሰፋፈር ሥርጭትና አኗኗር ላይ ተጽእኖ ስላላቸው ነገሮች ያብራራሉ፡፡

**ንዑሳን ርዕሶች**

- የአፍሪካ የቆዳ ስፋት፣ ቅርጽና መገኛ
- ኬንትሮስና ኬክሮስ
- የአፍሪካ ዋና ዋና ቋንቋዎች፣ ቤተሰቦችና ሥርጭታቸው
- ጥንታዊ የአፍሪካ ሥልጣኔ በግብጽና በካርቴጅ
- የቅድመ ቅኝ ግዛት ዘመን ግዛቶች
- የሲራራ ንግድ የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ለማገናኘት የነበረው አስተዋፅኦ
- ሕዝብ

## 1.1 የአፍሪካ የቆዳ ስፋት፣ ቅርጽና መገኛ

**የተመደበው ክፍል ጊዜ 2**

### ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት፡-

*ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ፡-*

- የአፍሪካን የቆዳ ስፋት እና ቅርፅ ከሌሎች አኅጉራት ጋር ያወዳድራሉ::
- የአፍሪካን ፍጹማዊ መገኛ ይለያሉ::

### ለ. ይዘቶች

- የአፍሪካ የቆዳ ስፋት
- የአፍሪካ ቅርፅ
- የአፍሪካ መገኛ
- የአፍሪካ ፍጹማዊ መገኛ

### ሐ. የትምህረቱ መሰረተ ሀሳብ

የተጠላለፉት የሀሳብ መስመሮች ማለትም ኬክሮሶችና ኬንትሮሶች የአንድን ቦታ ፍፁማዊ መገኛ ያመለክታሉ:: ስለዚህ የአፍሪካ ፍፁማዊ መገኛ በ37 (ዲግሪና) በ21(ደቂቃ) ሰሜን እና በ34 (ዲግሪ) 52 (ደቂቃ) ደቡብ መካከል ሲሆን እንዲሁም በ17(ዲግሪ) በ33(ደቂቃ) ምዕራብ እና በ51(ዲግሪ) በ28 (ደቂቃ) ምሥራቅ መካከል ነው:: የአፍሪካ ከሰሜን - ደቡብ ርዝመት 8000 ኪሎ ሜትር ሲሆን ከምዕራብ-ምሥራቅ ርዝመት 7600 ኪሎ ሜትር ነው:: የአፍሪካ የአየር ንብረት በሁለቱ የሀሩር መስመሮች ውስጥ የሚገኝ ነው:: አፍሪካ የተጠጋጋ ቅርፅ ያላት አኅጉር ነች:: ከዚህም በላይ የምድር ሰቅ አፍሪካን ከሁለት ቦታ እኩል ይከፍላታል::

የአፍሪካ የቆዳ ስፋት 30,335,000 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ነው:: በመሆኑም ሁለተኛዋ ታላቋ አኅጉር ናት::

## መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ

### 1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የአፍሪካ ተፈጥሮአዊ ካርታ
- የአፍሪካ የንድፍ ካርታ
- የአለም ተፈጥሮአዊ ካርታ

### 2. የማስተር ሥነ ዘዴዎች

- ገለፃ
- ውይይት
- የቡድን ሥራ

### 3. ቅድመ-ዝግጅት

- የአፍሪካን ካርታ ክፍል ውስጥ ያሳያሉ
- የአፍሪካን የንድፍ ካርታ በሚታይ ቦታ ያስቀምጡ
- የዕለቱን የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅተው ለማገናዘቢያነት ያስቀምጡ

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

### 1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ

ተማሪዎቹን የሚከተሉትን አይነት ጥያቄዎች በመጠየቅ ትምህርቱን መጀመር ይችላሉ

- አፍሪካ የምትገኘው የት ነው?
- የተጠጋጋ ቅርፅ ማለት ምን ማለት ነው?
- የአፍሪካን መጠን ከሌሎች አኅጉሮች ጋር ያወዳድሩ፡፡

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

- የአፍሪካን ተፈጥሮአዊ ካርታ በማቅረብ ትምህርቱን ይጀምሩ፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ ሀሳቦችን እንዲያሰሙ ያበረታቶአቸው፡፡ ስለ አፍሪካ መጠንና ቅርፅም ተማሪዎች ይነጋገሩ፡፡
- ፍፁማዊ መገኛ ምን ማለት እንደሆነ ይግለፁ፡፡
- የአፍሪካን ፍፁማዊ መገኛ አመልክቱ፡፡

## ረ. ምዘናና ክትትል

### 1. ምዘና

የሚከተሉትን አይነት ጥያቄዎች ይጠይቁ

- አፍሪካ ምን ያህል ትልቅ አህጉር ነች።
- በአፍሪካ ዙሪያ ያሉትን የውሀ አካሎች ግለፁ።
- የአፍሪካ አህጉር የትኛው ክፍል በስፋት ይበልጣል? ከምድር ወገብ በስተሰሜን ወይንስ በስተደቡብ ያለው?

### 2. ክትትል

ተማሪዎች የአፍሪካን ካርታ በንድፍ እንዲሰሩ ይጠይቋቸው። ከዚያም በሚከተሉት ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ።

- የአፍሪካ መጠን
- የአፍሪካ አቀማመጥ
- የአኅጉር የተጠጋጋ ባህሪ

## 1.2 ተንዳኝና ቋሚ መስመሮች (የኬንትርስና የኬክሮስ መስመሮች)

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡ 3**

## ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

*ተማሪዎች ይህንን ንኡስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ*

- የአፍሪካን ፍፁማዊ መገኛ መግለፅ ይችላሉ።
- በኬክሮስና በኬንትሮስ መሐከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ መወያየት ይችላሉ።
- የአለም አቀፍ የቀን መለያ ወይም 180(ዲግሪ) ኬንትሮስ አስፈላጊነትን መግለፅ ይችላሉ።
- በቦታዎች መካከል ያለውን የጊዜ ልዩነት ማስላት ይችላሉ።
- የተንዳኝ፣ የቋሚ መስመሮችንና ሜሪዲያኖችን ምንነት ማስረዳት ይችላሉ።

## ለ. ይዘቶች

- ተዳጋኝ መስመሮች
- ቋሚ መስመሮች
- አካባቢያዊ ጊዜ
- ዓለም አቀፍ የጊዜ ክልል
- ዓለም አቀፍ የቀን መለያ

## ሐ. የትምህርቱ መሰረተ ሃሳቦች

የኬክሮስና የኬንትሮስ መስመሮች ካርታ ወይም ሉል ላይ ያሉ ቦታዎችን ትክክለኛ መገኛ ለማወቅ ይረዱናል፡፡

ለምሳሌ በግልፅ ካርታ ላይ አፍሪካ የሚገኘው በ37 (ዲግሪ) 21(ደቂቃ) ሰሜን እና 34(ዲግሪ) 52(ደቂቃ) ደቡብ ኬክሮስ መካከል ሲሆን እንዲሁም በ17(ዲግሪ) 33(ደቂቃ) ምዕራብና በ51 (ዲግሪ) 28 (ደቂቃ) ምስራቅ ኬንትሮስ መካከል ነው፡፡

እንደ ማጣቀሻ የሚጠቀሙ አምስት የኬክሮስ መስመሮች ይገኛሉ፡፡ እነዚህም የኬክሮስ መስመሮች የፀሐይ ብርሃን መጠን የሚያገኙትን ቦታዎች ለማወቅ ያግዛሉ፡፡

- የመሬት ሰቅ(የመሬት ወገብ) (0° ኬክሮስ)፡- በምድር ሰቅ የፀሀይ ብርሃን በቀጥታ ያገኛል፡፡
- የካንሰር ሃሩር እና የካፕሪኮርን ክልሎች የሚገኘው ከምድር ሰቅ በ$23^1/_2$ ሰሜን እና በ$23^1/_2$ ደቡብ ላይ ነው፡፡ በእነዚህ ሁለት መስመሮች መካከል የሚገኘው ክልል ዝቅተኛ ኬክሮሶች ወይም ሀሩሮች ይባላል፡፡
- የአርክቲክ ክበብ፡- ከምድር ሰቅ $66^1/_2$ ሰሜን ላይ ይገኛል፡፡ ነገር ግን በ $66^1/_2°$ ደቡብ ላይ የሚገኘው የአንታርክቲክ ክበብ ነው፡፡ በሁለቱ አካባቢዎች አንድ ሙሉ ቀን የፀሀይ ብርሃን ሲገኝ አንድ ሙሉ ቀን ጨለማ ይሆናል፡፡ ከአርክቲክ ክበብ በስተጫፍ ያለውና ከአንታርክቲክ በስተ-ደቡብ ጫፍ ያለው አካባቢ ከፍተኛ ኬክሮሶች ወይም የዋልታ አካባቢ በመባል ይታወቃል፡፡

* መነሻ ዋልቴ (ፕራይም ሜሪዲያን) ወይም 0° (ዲግሪ) ኬንትሮስ የሚያመራው ከሰሜን ዋልታ እስከ ደቡብ ዋልታ ነው፡፡ የሚያልፈውም ከለንደን አቅራቢያ በሚገኘው በግሪንዊች የጠፈር ምርምር ጣቢያ በኩል ነው፡፡

በአለም ላይ የጊዜ አቆጣጠር የሚጀምረው ከዚሁ 0° (ዲግሪ) ሜሪዲያን ነው፡፡ አለም አቀፍ የቀን መለያ መስመር ቀናት አንድ ተብለው የሚጀምሩበት እና የሚያቆሙበት መስመር ነው፡፡ ከሰሜን ዋልታ ወደ ደቡብ ዋልታ የሚያመራው በ180° (ዲግሪ) ሜሪዲያን ላይ ነው፡፡ ይህንን መስመር አቋርጠው የሚያልፍ ተጉዋዦች የቀን መቁጠሪያቸውን ማስተካከል ይኖርባቸዋል፡፡ አንድ ቀን መጨመር ወይም መቀነስ ይገደዳሉ፡፡

## መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ

### 1. የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

* ሉል
* አትላስ(የተለያዩ ካርታዎችን የያዘ መፅሀፍ)
* የግድግዳ ካርታ
* የመሬትን አቀማመጥ የሚያሳይ ካርታ
* በጥቁር ሰሌዳ ላይ የተሳሉ ንድፎች

### 2. የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች

* ገለፃ
* ውይይት
* ከአምስት ያላነሱ የተማሪዎች ቡድን ውይይት
* የመስክ ምልከታ

### 3. ቅድመ -ዝግጅት

* ተገቢ የሆኑትን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ማዘጋጀት
* የግድግዳ ካርታ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ማሳየት
* ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅነት የላቸውን ማጣቀሻ መፅሀፍት አስቀድመው እንዲያነቡ ተማሪዎችን ማሳወቅ፡፡

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

### 1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ

የሚከተሉትን አይነት ጥያቄዎች ተማሪዎችን በመጠየቅ ትምህርቱን መጀመር ይቻላል::

- ካርታ ተመልክታችሁ የአፍሪካን መገኛ እና ዋናውን ገፅታ አብራሩ::
- መነሾ ዋልቴ (ፕራይም ሜሪዲያን) ምንድን ነው? አስፈላጊነቱ ላይ ተወያዩ::
- ዝቅተኛ እና ከፍተኛ ኬክሮስ አካባቢዎችን ግለፁ
- አለም አቀፍ የቀን መለያ መስመር ምንድን ነው?

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

- በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ላይ በተገለጸው መሰረት የአንድን ቦታ ፍፁማዊ መገኛ ዘዴ በተመለከተ ተወያዩ::
- ስለ ካንሰር እና ካፕሪኮርን የሀሩር መስመሮች እንዲሁም ስለ መሬት ሰቅ እና የመሬት ዛቢያ ተማሪዎቹ በስድስተኛ ክፍል ትምህርታቸው ያወቁትን አስታዉሷቸው:: በሰሌዳ ላይ ይሳሉላቸው::
- ቀጥለው ሌሎች የኬክሮስ መስመሮችን አሳወቁ ከዚያም ከሜሪዲያኑ በመጀመር የኬክሮስ መስመሮችን አሳውቁ:: ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ጥያቄ ያቅርቡ::
- ተማሪዎች ስእላዊ መግለጫውን እንዲገለብጡ ያድርጉ::
- በመጨረሻና ወደ ምስራቅ አንድ ሰአት ስንጓዝ 15° (ዲግሪ) ኬንትሮስ እንደሚሆን ለተማሪዎች ይግለፁላቸው::

## ረ. ምዘና ክትትል

*ሀ) ግምገማ*

ተማሪዎቹን የሚከተሉትን አይነት ጥያቄዎች ጠይቋቸው::

- የአዲስ አበባና የኢትዮጵያ ፍፁማዊ መገኛ ምንድን ነው?
- በሚከተሉት መካከል ያለውን ልዩነት ይግለፁ
  - በኬንትሮስና በኬክሮስ

- በዝቅተኛ ኬክሮስና በከፍተኛ ኬክሮስ
- በመነሾ ዋልቴ (ፕራይም ሜሪዲያን) እና በአለም አቀፍ የቀን መለያ መስመር

*ለ) ክትትል*

ተማሪዎች የሚከተሉትን ክንዋኔዎች እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡

- የዓለምን ካርታ ከሰሩ በኋላ አምስቱን የኬክሮስ መስመሮች ያመልክቱ፡፡
- አለም አቀፍ የቀን መለያ መስመር ሲታለፍ አንድ ቀን ሰለሚጨምርበት ወይንም ስለሚቀንስበት ጉዳይ ተወያይተው በፅሁፍ ያቅርቡ፡፡፡

**1.3 የአፍሪካ ዋና ዋና ቋንቋ ቤተሰቦች እና ስርጭታቸው**

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡ 2**

***ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት***

*ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ፡-*

- የአፍሪካን ዋና ዋና ቋንቋዎችን ስም ይዘረዝራሉ፡፡

**ለ. ይዘት**

- ዋና ዋና የቋንቋ ቤተሰቦች

**ሐ. የትምህርቱ መሰረተ ሀሳብ**

በአፍሪካ ውስጥ ከአንድ ሺህ በላይ ቋንቋዎች ይነገራሉ፡፡ እነዚህም በአራት የቋንቋ ቤተሰብ ይመደባሉ፡፡ ኒጀር ኮንጎ፣ አፍሮ እስያዊ፣ ናይሎ ሰሃራዊ እና ኮይሳን ይባላሉ፡፡ ኒጀር ኮንጎ በጣም ብዙ ተናጋሪዎች ሲኖሩትከ300-400 ሚሊዮን ይገመታሉ፡፡ በሁለተኛዉ ደረጃ የሚገኘዉና ከ200-300 ሚሊዮን ተናጋሪ ያለው አፍሮ እስያዊ ነው፡፡ የኮይሣን የቋንቋ ቤተሰብ ተናጋሪዎች ከ300.000 አይበልጡም፡፡ እነርሱም የሚኖሩት በደቡባዊ አፍሪካ በጥቂት ቦታዎች ላይ ነው፡፡ የኒጀር ኮንጎ ተናጋሪዎች በምዕራብ፣ በማእከላዊ፣ በምሥራቅና በደቡባዊ አፍሪካ ይኖራሉ፡፡ የአፍሮ እስያዊና ናይሎ ሰሀራዊ ተናጋሪዎች ደግሞ በኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ይገኛሉ፡፡

## መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ

### 1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የአፍሪካ የቋንቋ ስርጭት ካርታ

### 2. የተጠቀሙ የማስተማር ዘዴዎች

- ገለፃ
- ውይይት
- የቡድን ሥራ

### 3. ቅድመ-ዝግጅት

- ተያያዥ ዋቢ መጽሐፍን እንዲያገናዝቡ ያዘጋጁላቸው
- ከላይ የተገለጸውን የትምህረት መርጃ መሳሪያ ያሳዩ
- የዕለቱን የትምህርት ዕቅድ ያዘጋጁ

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

### 1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ

*ተማሪዎቹን የሚከተሉትን አይነት ጥያቄዎች ይጠይቋቸው*

- ምን ያህል የከፍተኛ የቋንቋ ቤተሰቦች አሉ::
- በአፍሪካ ውስጥ ያሉትን የከፍተኛ ቋንቋ ቤተሰቦች ስም ፃፉ::
- በኢትዮጵያ ስንት ቋንቋዎች ይገኛሉ?

### 2 የትምህርቱ አቀራረብ

- ተማሪዎች የአፍሪካን ከፍተኛ የቋንቋ ቤተሰቦች ስሞች እንዲገልፁ ይጠይቋቸው::
- የከፍተኛ ቋንቋ ቤተሰቦችን ስርጭት አጠር አድርገው ይግለፁ::
- የአፍሪካን ካርታ ለተማሪዎች ያቅርቡና የከፍተኛ ቋንቋ ቤተሰቦችን መገኛ ቦታ እንዲያመለክቱ ይጠይቋቸው::
- የክፍሉን ተማሪዎች በተለያየ ቡድን ይመድቡ:: እያንዳንዱ ቡድን በተመረጡ ከፍተኛ የቋንቋ ቤተሰብ ላይ ጥናት ካደረገ በኋላ የጥናቱን ውጤት በክፍል ውስጥ ለውይይት ያቅርብ::

## ረ. ምዘናና ክትትል

*ሀ) ምዘና*

*ተማሪዎቹን የሚከተሉትን አይነት ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡*

- የትኛው ከፍተኛ የቋንቋ ቤተሰብ ነው ብዙ ተናጋሪዎች ያሉት?
- የትኛው ከፍተኛ የቋንቋ ቤተሰብ ነው አነስተኛ (ጥቂት) ተናጋሪዎች ያሉት?
- በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ በስፋት የሚነገሩትን ከፍተኛ የቋንቋ ቤተሰቦች ስም እንዲጠሩ ያድርጉ፡፡

*ለ) ክትትል*

- ተማሪዎቹ በአፍሪካ ካርታ ላይ የከፍተኛ ቋንቋ ቤተሰቦች ስርጭትን መገኛዎች እንዲያሣዩ ይጠይቋቸው፡፡
    - አፍሮ እሲያዊ
    - ናይሎ ሰሀራዊ
    - ኮይሳን
    - ኒጀር ኮንጎ

## 1.4 ጥንታዊ የአፍሪካ ሥልጣኔ በግብጽና በካርቴጅ

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡- 2**

### ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት፡-

*ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ*

- የጥንታዊ አፍሪካ ሥልጣኔ ማዕከል የነበሩትን የግብፅንና የካርቴጅን መገኛ ያመለክታሉ፡፡
- ጥንታዊ ግብፅና ካርቴጅ ለአለም ሥልጣኔ ያበረከቱትን ጠቀሜታ ያብራራሉ፡፡

## ለ. ይዘቶች

- የጥንታዊ ግብፅ ሥልጣኔ
  - ጥንታዊ ፒራሚድ
  - መካነ መቃብር
  - ቤተ ፀሎት
  - እርሻና ንግድ
  - የሄሮግላፊክስ አፃፃፍ
- የጥንታዊ ካርቴጅ ስልጣኔ

## ሐ. የትምህርቱ መሰረተ ሀሳብ

- የጥንታዊ ግብፅ ሥልጣኔ የተጀመረው በ3000 ዓ.ዓ አካባቢ ነው የተጀመረውም በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ በናይል ሸለቆ ነበር፡፡ የጥንታዊ ግብፅ ህዝብ አብዛኞቹ ደሀ አርሶ አደሮች ሲሆኑ የሚኖሩት ከጭቃ በተሰሩ ደሳሳ ጎጆ ውስጥ ነበረ፡፡ ስንዴ፣ ገብስ ቀይሽንኩርትና የተለያዩ የቅጠላቅጠል ምግቦችን ያመርታሉ፡፡ የጥንታዊ ግብፅ አርሶ አደሮች የመሥኖ ስራ በሰፊው ይጠቀሳል፡፡ በተጨማሪ በቤተ መቅደስ እና መካነ መቃብር ግንባታዎች ይሳተፋሉ፡፡ የጥንታዊ ግብጽ መሪዎች ፈርኦን ይባላሉ፡፡ ለፈርኦኖች የሚሠሩት ግዙፍ መካነ-መቃብሮች ፒራሚድ ይባላል፡፡ ጥንታዊ ግብፆች ከሞት በኋላ ህይወት አለ ብለው ያምናሉ፡፡ አስክሬኑ ሳይፈርስ ጠብቆ የማቆየት ጥበብ አላቸው፡፡ በተጨማሪም ሔሮግላፊክስ የተሰኘ የአፃፃፍ ዘዴ ነበራቸው፡፡ ይህንን ስእላዊ አፃፃፍ በመጀመሪያ የሚፅፉት በድንጋይ እና በእንጨት ላይ እየቀረፁ ነበረ፡፡ ዘግይተው ግን ፓፒረስ በተሰኘ ነገር ላይ መጻፍ ችለዋል፡፡ ጥንታዊ ግብፆች በሂሳብ በስነ ህንፃና በህክምና ሙያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ ፒራሚዶች የጥንታዊ ግብፆች ታላቅ የስራ ውጤቶች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ጥንታዊ ግብጾች ከቀረው የዓለም አካባቢ ጋር የባህልና የንግድ ግንኙነት ነበራቸው፡፡

ኑቢያ በጥንታዊ ግብጻውያን ዘንድ "የወርቅ ሃገር" በመባል ትታወቃላች ኑቡያ የምትገኘው ከግብፅ በስተደቡብ በናይል(አባይ) ወንዝ አካባቢ ነበር ጥንታዊ ግብጻውያን ነጋዴዎች ወደ ኑቢያ በመጓዝ የዝሆን ጥርስ፣ ዕጣን፣ ብርታ ብረት እና ወርቅ ይገዙ እንደነበር ይታወቃል፡፡

- ካርቴጅ የበለፀገች የንግድ ማእከል ስትሆን የምትገኘውም በሰሜን አፍሪካ የባህር ዳርቻ በዛሬዋ ቱኒስ ከተማ አቅራቢያ ነበረ፡፡ ከተማዋ የተመሰረተችው ፎኒሺያውያን በተባሉ ሰዎች እ.አ.አ በ814 አካባቢ ነው፡፡ የካርቴጅ ከተማ በበላይነት የምትቆጣጠረው ግዛት ሰሜን አፍሪካ ደቡባዊ ስፔንና የኮርሚካን፣ ሳርዲኒያና የሲሲሊን ደሴቶች በሙሉ ያጠቃላል፡፡ የካርቴጅ ህዝብ ከጦርነት ይልቅ ንግድ ላይ ነበረ የሚያተኩረው ሆኖም ካርቴጅ ከሮም ጋር የፑኒክ ጦርነት የተባሉ ሶስት ውጊያዎችን አድርጋለች፡፡ በመጨረሻ ካርቴጅ ተሸንፋ የሮማውያን ግዛት አካል ሆናለች፡፡

## መ. የትምህርት መርጃ

### *1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች*

- ካርታዎች
- ስእሎች
- ፎቶግራፎች

### *2. የተጠቀሙ የማስተማር ሥነ ዘዴዎች*

- ውይይት
- ገለፃ
- የቡድን ሥራ

### *3. ቅድመ-ዝግጅት*

- የዕለቱን የትምህርት እቅድ ለማጣቀሻነት ያዘጋጁ
- ከላይ የተገለፁትን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ያሳዩ፡፡
- ዋቤ መፅሐፍት ያዘጋጁ
- የቅድመ ንባብ የቤት ሥራ ለተማሪዎች ይስጡ (በርዕሱ ላይ)፡፡

*ሠ. የመማር-ማስተማር ሒደት*

*1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ*

*ተማሪዎቹን የሚከተሉትን አይነት ጥያቄዎች ይጠይቋቸው::*

- *ፈርኦኖች ምን ነበሩ?*
- *የፒራሚዶች ጥቅም ምን ነበረ?*

*2. የትምህርቱ አቀራረብ*

- በካርታ ላይ ተማሪዎቹ ግብፅን ፈልገው እንዲያገኙ ይጠይቋቸው::
- የጥንታዊ ግብፆች የአፃፃፍ ስርአትን በተመለከተ ተማሪዎች እንዲወያዩ ያድርጉ::

**ረ. ምዘናና ክትትል**

*ሀ) ምዘና*

የሚከተሉትን አይነት ጥያቄዎች ይጠይቁ::

- ጥንታዊ ካርቴጅን በካርታ ላይ እንዲያገኙ ተማሪዎችን ይጠይቁ::
- የጥንታዊ ግብፅንና የጥንታዊ ካርቴጅን ሥልጣኔዎች ያወዳድሩ::

*ለ) ክትትል*

- የጥንታዊ ግብፅ እና ካርቴጅ ስልጣኔዎች ባሁኑ ጊዜ ላለው ስልጣኔ ያደረገውን አስተዋፅኦ በተመለከተ ተማሪዎች እንዲወያዩ ያድርጉ::

## ርዕስ 1.5 የቅድመ ቅኝ ግዛት ዘመን ሀገሮች

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ: 3**

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

*ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ*

- በቅድመ ቅኝ አገዛዝ ዘመን የጥንታዊ ማሊና ሩንጅ የምጣኔ ሀብት መሠረት ይተነትናሉ::

- በቅድመ ቅኝ አገዛዝ ዘመን የነበረውን ዚምባብዌን የሥነ ሕንጻ ጥበብ ያደንቃሉ፡፡

**ለ. ይዘቶች**

- ጥንታዊ ዚምባብዌ
- ጥንታዊ ፉንጅ
- ጥንታዊ ማሊ

**ሐ. የትምህርቱ መሰረተ ሀሳቦች**

- እ.አ.አ በ1000 ዓ.ም አካባቢ ሾና የተባሉ ማህበረሰቦች ዚምባብዌ የተሰኘ ከተማ መሰረቱ፡፡ በሾና ቋንቋ ዚምባብዌ ማለት ከድንጋይ የተሰራ ቤት ማለት ነው፡፡ በ1400ዎቹ ውስጥ ካራንጋ በመባል የሚታወቅ የሾና ቅርንጫፍ ማህበረሰብ ሞኖሞታፓ የተሰኘ ሌላ መንግስት አቋቋመ፡፡ ይህ መንግስት ከቻይና እና ከህንድ ጋር የንግድ ግንኙነት መስርቶ ነበር፡፡ ነገርግን ሮዝዊ የተሰኘ የደቡባዊ ካራንጋ ቡድን ቻንግማይር የተሰኘ መንግስት መስርቶ የዚምባብዌ ከተማን ተቆጣጠረ፡፡ በመጨረሻም አንጉኒ በመባል የሚታወቅ ማህበረሰብ በተራው ቻንግማይርን አስወገደ፡፡ ከዚህ በኋላ የዚምባብዌ ከተማ እየወደቀችና እየተተወች መጣች፡፡
- እ.አ.አ ከ 1240 እስከ 1500 ዓ.ም ባለው ጊዜ ማሊ ታዋቂ እየሆነች መጣች፡፡ የመጀመሪያው ታዋቂ መሪ ሱንዲያታ ይባላል፡፡ እ.አ.አ ከ1312 እስከ 1337 ዓ.ም ደግሞ ማንሳ ሙሳ የማሊ መሪ ነበረ፡፡ በርሱ ዘመነ መንግስት ማሊ ከፍተኛ የእድገት ደረጃ ላይ ደርሳለች፡፡ ቲምቡክቱ በጣም የታወቀች የእስልምና ሀይማኖት ትምህርት ማእከል ሆናለች፡፡ ሌሎች የማሊ ከተሞች የሲራራ ንግድ ማእከል ነበሩ፡፡ የማሊ ሕዝቦች ጠንካራ ገበሬዎች እና አርብቶ አደሮች ነበሩ፡፡ በ1500 ዓ.ም አካባቢ የሶንጋሀይ መንግሥት ማሊን ተቆጣጠረ፡፡
- ፉንጅ በዛሬዋ ሱዳን የሚገኝ የሙስሊም መንግስት ነበረ፡፡ የፉንጅ መንግስት የተመሰረተው በ1500 ዓ.ም አካባቢ ነበረ፡፡ከ1600 እስከ

1650 ዓ.ም የፉንጅ መንግስት ታዋቂ እየሆነ መጣ፡፡ በ1500 ዓ.ም ስናር በመባል የምትጠራውን ዋና ከተማ መሰረቱ፡፡ በመጨረሻ የፉንጅ መንግስት እየተዳከመ ሔዶ በ1821 ዓ.ም በግብፅ ተያዘ፡፡

## መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴ

### 1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የአፍሪካ ቅድመ ቅኝ አገዛዝ ካርታ
- ሥዕሎች
- ፎቶግራፎች

### 2. የተጠቆሙ የማስተማር ሥነ ዘዴዎች

- ውይይት
- ገለፃ
- የቡድን ስራ

### 3. ቅድመ-ዝግጅት

- ከላይ የተገለፁትን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ያሟዩ፡፡
- ለተማሪዎች የተሰጣቸውን ስራ ይሰብስቡና ለክፍል ውይይት ያቅርቡ፡፡

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

### 1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ

*የሚከተሉትን አይነት ጥያቄዎች ይጠይቁ*

- የዚምባብዌ ቅድመ ቅኝ አገዛዝ መጠሪያ ማን ነበረ?
- በአፍሪካ ዚምባብዌ የምትገኘው የት አካባቢ ነው?
- ማሊ በአፍሪካ የትኛው አካባቢ ነው የምትገኘው?

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

- በካርታ ላይ ዚምባብዌን እንዲያሳዩ ይጠይቋቸው፡፡
- ተማሪዎቹ የዚምባብዌን እና የማሊን ስልጣኔ እንዲያነጻጽሩ አድርጓቸው፡፡

**ረ. ምዘናና ክትትል**

*ሀ) ምዘና*

*የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ይጠይቁ*

- በአፍሪካ ካርታ ላይ የማሊንና የሩንጂን ቅድመ ቅኝ አገዛዝ መንግስታትን ተማሪዎቹ እንዲያመለክቱ ጠይቋቸው::

*ለ) ክትትል*

- በዚምባብዌ፣ በማሊና በሩንጅ መንግስታት የታዩትን ክንዋኔዎች በተመለከተ ተማሪዎች እንዲወያዩ ያግዟቸው::
- በሚያስደስታቸው አንድ አፍሪካዊ (የዚምባቡዌ/ የማሊ ወዘተ) ባህል ላይ አጭር ጽሁፍ እንዲያቀርቡ ተማሪዎችን ይጠይቋቸው::

## 1.6. የሲራራ ንግድ የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ለማገናኘት የነበረው ፋይዳ

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት፡-**

**የተሰጠው ክፍለ ጊዜ፡- 3**

*ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ*

- የኢትዮጵያን ህዝብ በማግኘት በኩል የሲራራ ንግድ ያደረገውን አስተዋፅኦ ይረዳሉ::
- የንግድ መስመሮችን መነሻ ይለያሉ::

**ለ. ይዘቶች**

- የሲራራ ንግድ በኢትዮጵያ

**ሐ. የትምህርቱ መሰረተ-ሐሳብ**

ንግድ በዋናነት አንድ ቦታ ሰፍሮ በመኖር፣ ወይም በመዘዋወር የተረፈ ምርትና የማህበራዊ ስራ ክፍፍል ውጤት ነው:: ንግድ አካባቢያዊና የረዥም ርቀት ተብሎ በሁለት ይከፈላል:: አካባቢያዊ ንግድ የሚካሄደው በአንድ አካባቢ በሚኖሩ ሰዎች መካከል በታወቀ ሳምንታዊ የገበያ ቀን/ቀናት ነው:: ባንፃሩ የረጅም ርቀት ንግድ የሚካሄደው በተለያዩ

አካባቢዎች ህዝቦች እና ገበያዎች ሆኖ ውስጣዊና ውጫዊ ንግዶችን አጣምሮ የያዘ ኢኮኖሚያዊ ክንዋኔ ነው፡፡ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ዋና ዋናዎቹ ነጋዴዎች ጀባርቲ እና አፍቃላ በመባል ይታወቃሉ፡፡ ጀባርቲ የሚባሉት ከሰሜን ኢትዮጵያ የተገኙ ሙስሊም ነጋዴዎች ሲሆኑ አፍቃላ የተባሉት ደግሞ የደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ሙስሊም ኦሮሞ ነጋዴዎች ነበሩ፡፡ የረዥም ርቀት ንግድ ስራ የሚሰራው በሲራራ ነጋዴዎች ነበረ፡፡ የሲራራ ነጋዴዎች መሪዎች ነጋድራስ በመባል ይታወቃሉ፡፡ በ19ኛው ክፍለ-ዘመን ወደ ውጭ የሚላኩት ዋና ዋና ሸቀጦች የዝሆን ጥርስ፣ ዝባድ፣ ወርቅ፣ ቡና እና ባሮች ሲሆኑ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡት ደግሞ መዳብ፣ ቅመማ ቅመሞች፣ ጨርቃ ጨርቅ፣ የሀር ጨርቅ፣ ጨሌ፣ የብር ማዕድን፣ የጦር መሳሪያ እና ቀለሀዎች ነበሩ፡፡ ወደ ሰሜን አቅጣጫ የሚያመራው የንግድ መስመር መድረሻው የምፅዋ ወደብ ሲሆን ወደ ምስራቅ አቅጣጫ የሚሄደው መስመር መዳረሻ በኤደን ባህረ-ሰላጤ አካባቢ የሚገኙት የዘይላ እና የበርበራ ወደቦች ነበሩ፡፡ ከደቡብ ምእራብ ወደ ሰሜን በሚወስደው የንግድ መስመሮች ላይ የሚገኙት የገበያ ሥፍራዎች የሚከተሉት ነበሩ ቦንጋ፣ ሂርማታ፣ አስንዳቦ፣ ባሶ እና አድዋ ናቸው፡፡ እንዲሁም ከምእራብ ወደ ምስራቅ በሚያመራው የንግድ መስመር ላይ የሚገኙት የገበያ ስፍራዎች ሶዶ፣ አንኮበር፣ አልዩ አምባ፣ ድሬዳዋ እና ሀረር በጣም የታወቁ ነበሩ፡፡ በረጅም ርቀት ንግድ አይነተኛ ው የመገበያያ ገንዘብ አሞሌ ጨው ነበረ፡፡ ውሎ አድሮ ከብር ማእድን የተዘጋጀውና ማሪያ ቴሬዛ የተሰኘው የሳንቲም አይነት ገንዘብ በንግድ ስራ ላይ ውሏል፡፡ የረዥም ርቀት ንግድ በኢትዮጵያ ህዝቦች መሀከል የኢኮኖሚ ትስስር እንዲኖር ምቹ ሁኔታ ፈጥሮአል፡፡ በተጨማሪም በጊቤ ወንዝ ሸለቆ ውስጥ በሚኖሩት የኦሮሞ ህዝቦች መካከል የእስልምና ሀይማኖት እንዲስፋፋ አድርጎአል፡፡

## መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ

### 1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ካርታዎች
- ፎቶግራፎች

**2. የተጠቀሙ የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች**

- ውይይት
- ገለፃ
- የቡድን ስራ

**3. ቅድመ- ዝግጅት**

- ከላይ የተገለጹትን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ያሣዩ::
- የዋቢ መጻሕፍት ያዘጋጁ::
- በርእሱ ላይ የተመሠረተ ቅድመ ንባብ የቤት ሥራ ለተማሪዎች ይሰጡ::

**ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት**

**1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ**

*የሚከተሉትን አይነት ጥያቄዎች ተማሪዎቹን ይጠይቋቸው::*

- ረጅም ርቀት ንግድ ምንድንነው?
- በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኘው ዝነኛው የረዥም ርቀት ንግድ ወደብ ማን ነበረ?
- በምስራቅ ኢትዮጵያ የሚገኙት ዋና ዋና የረጅም ርቀት ንግድ ወደቦች እነማን ነበሩ?
- የሢራራ ነጋዴዎች መሪ ምን የሚል ማዕረግ ነበረው?

**2. የትምህርቱ አቀራረብ**

- በኢትዮጵያ ካርታ በመታገዝ የረዥም ርቀት ንግድ መስመሮችን ዋና ዋና የገበያ ስፍራዎችንና ወደቦችን ግለጹ::
- በረጅም ርቀት ንግድ ወደ ውጭ የሚላኩትንና ወደ ሀገር ውሰጥ የሚገቡትን ሸቀጦች ተማሪዎቹ ለይተው እንዲያውቁ ያግዙአቸው::

ረ. ምዘናና ክትትል

*ሀ) ምዘና*

የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ይጠይቁ

- የመገበያያ ገንዘቦችን በተመለከተ የአሞሌ ጨውና የማሪያ ቴሬዛ ገንዘቦችን በማነጻጸር ውይይት ያድርጉ፡፡
- የረጅም ርቀት ንግድ በህዝቦች መካከል የእርስ በርስ መወዳደርን መፍጠሩን በተመለከተ ተማሪዎች ውይይት እንዲያካሂዱ ይጠይቋቸው፡፡

*ለ) ክትትል*

- ተማሪዎቹ በሚኖሩበት አካባቢ የሚገኝ የገበያ ቦታ ሄደው ከተመለከቱ በኋላ በገበያ ላይ የቀረቡትን የሸቀጣሸቀጥ አይነቶችንና መምጫቸውንም ጭምር ይመዝግቡ፡፡ በገበያው ላይ ከሚሳተፉት ነጋዴዎች የትኞቹ የሀገር ውስጥ ምርቶችን እንደሚሸጡና የትኞቹ ከውጭ የመጡ ሸቀጦች እንደሚሸጡ በሚገባ ይለዩ፡፡
- በኢትዮጵያ ውስጥ ሰዎች በባህላዊ መንገድ እንዴት አድርገው ገንዘብ እንደሚያጠራቅሙ ተማሪዎች መረጃ እንዲሰበስቡ የቤት ስራ ይስጧቸው፡፡

## 1.7 የሕዝብ ስርጭትና አሰፋፈር

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ:- 3**

**ሀ) ከንዑስ ርዕስ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት፡-**

*ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ፡-*

- በሕዝብ ሥርጭት ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ምክንያቶችን መግለጽ ይችላሉ፡፡
- የሕዝብ ሥርጭትን የሚወስኑ ምክንያቶችን ከሕዝብ አሰፋፈር ጋር ታዛምዳላችሁ፡፡
- የአፍሪካ ሕዝብ አሠፋፈር ምን እንደሚመስል ትለያላችሁ፡፡

**ለ) ይዘቶች**

- የሕዝብ ስርጭትና አሰፋፈርን የሚወስኑ ቁልፍ ምክንያቶች

**ሐ) የትምህረቱ መሠረተ ሃሣብ**

በአፍሪካ ውስጥ የሕዝብ ስርጭትና አሠፋፈር እኩል ወይም የተመጣጠነ አይደለም:: በአፍሪካ ውስጥ በጣም ሰፊ አካባቢዎች ዝቅተኛ የሕዝብ ጥግግት ያላቸው ሲሆን በጣም ትንሽ አካባቢዎች ደግሞ ከፍተኛ የሕዝብ ጥግግት አላቸው፡፡ የሕዝብ ስርጭትና አሠፋፈር በአፍሪካ እንዲህ የተለያየ ሊሆን የቻለው በሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች የተነሣ ነው፡፡ እነርሱም ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡ ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች የሚባሉት፡- የመሬት አቀማመጥ፣ የአየር ንብረት፣ የእጽዋት ሽፋን፣ የአፈር ዓይነት፣ የበሽታዎች መኖር የመሳሰሉት ሲሆኑ ሰው ሠራሽ ምክንያቶች የሚባሉት ደግሞ፡- ጦርነትና የእርስ በርስ ብጥብጥ ናቸው፡፡

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማርያ ሥነ-ዘዴ**

***1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች***

- የአፍሪካ የሕዝብ ስርጭት ካርታ
- የአፍሪካ የተፈጥሮ ስርጭት ካርታ

***2. የማስተማር ዘዴዎች***

- ገለፃ
- ውይይት
- ጉብኝት (የመስክ ጉብኝት)

***3. ቅድመ-ዝግጅት***

- የአፍሪካን የሕዝብ ስርጭት ካርታ ክፍል ውስጥ ግርግዳ ላይ ይሰቅላሉ፡፡

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

### 1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ

ተማሪዎቹን የሚከተሉትን አይነት ጥያቄዎች በመጠየቅ ትምህርቱን መጀመር ይችላሉ፡፡

- በሕዝብ ስርጭትና በሕዝብ ጥግግት መሐከል ያለው ልዮነት ምንድ ነው?
- የሕዝብ ስርጭትና አሠፋፈር ልዩነት ዋነኛ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?
- በአፍሪካ ከፍተኛ የሕዝብ ጥግግት ያለባቸውን አካባቢዎች ጥቀሱ፡፡

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

- የአፍሪካን የሕዝብ ስርጭት ካርታ በማሳየት ትምህርቱን ይጀምሩ፡፡
- ተማሪዎች የተለያዩ መረጃዎችን እንዲያመጡ ያበረታቷቸው፡፡ ስለአፍሪካ የሕዝብ ስርጭት ይነጋገሩ፡፡
- የስርጭቱ የልዩነት ምክንያቶችን ይግለጹ፡፡
- በአፍሪካ ከፍተኛ የሕዝብ ጥግግት ያለባቸውን አካባቢዎች ያመልክቱ፡፡

## ረ. ምዘናና ክትትል

*ሀ) ምዘና*

የሚከተሉትን አይነት ጥያቄዎች ይጠይቁ

- የአፍሪካ የሕዝብ ስርጭት ወጥነት አለውን?
- ለሕዝብ ስርጭት ምክንያት ከሆኑት ምክንያቶች ጥቂቶቹን ግለጹ፡፡
- ጦርነትና ርሃብ ለሕዝብ ስርጭነት ልዮነት ምክንያት የሚሆኑት እንዴት ነው?

*ለ) ክትትል*

ተማሪዎች የአፍሪካን የሕዝብ ስርጭት ንድፍ ካርታ እንዲሠሩ ይጠይቋቸው፡፡ ከዚያም በሚከተሉት ነጥቦች ዙሪያ እንዲወያዩ ያድርጉ፡-

- የአፍሪካ ሕዝብ ስርጭትና ጥግግት
- ከፍተኛ የሕዝብ ጥግግት ያላቸው የአፍሪካ ክፍሎች
- የሕዝብ ስርጭትና ጥግግት ዋነኛ ምክንያቶች

## 1.8 የአፍሪካ ሕዝብ አኗኗር፡-

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡- 23**

### *ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት*

*ተማሪዎች ከዚህ ንዑስ ርዕስ በኋላ*

- የአፍሪካ ሕዝብ አኗኗርን ያብራራሉ፡፡
- የሕዝብ አኗኗር ከአየር ንብረትና ከእጽዋት ጋር ያለውን ግንኙት ያዛምዳሉ፡፡

### ለ. ይዘቶች

- የአፍሪካ ሕዝብ አኗኗር
- የሕዝብ አኗኗር ከአየር ንብረትና ከእጽዋት ጋር ያለው ግንኙነት

### ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሃሣብ

በምድር ወገብ አካባቢ የሚገኙ የአፍሪካ ዝቅተኛ ቦታዎች ከ0° እስከ 6/7° ሰሜንና ደቡብ ያለውን አካባቢ ይሸፍናሉ፡፡ የአካባቢ የአየር ንብረት የምድር ወገብ (Equatorial climate) የአየር ንብረት ነው፡፡ ይህ የአየር ንብረት በአፍሪካ በጊኒ ባሕረ-ሰላጤ፣ በኮንጐ ተፋሰስ እና በምሥራቅ አፍሪካ ዝቅተኛ ቦታዎች ይገኛሉ፡፡

በአፍሪካ የምድርን ወገብ ዝቅተኛ አካባቢ የሚኖሩ ሕዝቦች የዘንባባ ፍሬ ዘይት፣ በማምረት፣ አሣ በማስገር፣ የተለያዮ የምግብ ሰብል (ካሳቫ፣ በቆሎ፣ ስኳር ድንች፣ ማሽላ፣ ዘንጋዳ፣ ያም፣ አትክልትና ፍራፍሬ) በማምረትና በከብት ርባታ ኑሮአቸውን ይመራሉ፡፡

ከሳሐራ በታች የአፍሪካ(sub-sahara Africa) ከፍተኛ ቦታ የሚባለው ሥፍራ ከባሕር ጠለል በላይ ከ1500 ሜትር በላይ ይሸፍናል፡፡ አማካይ ዕለታዊ ሙቀቱ ከ20° ሴልሸየስ አይበልጥም:: ከዚህ ከፍታማ ምድር 75% የሚሆነው የሚገኘው በምስራቅ አፍሪካ ነው፡፡

በአፍሪካ ከፍታማ ቦታዎች የሚከተሉት የእርሻ ምርቶች ይመረታሉ፡፡ እነርሱም፡- ቡና፣ የሻይ ቅጠል፣ የአበባ ምርት የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴ**

1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፡-
    - የአፍሪካ ተፈጥሮአዊ (physical feature) ካርታ
    - የአፍሪካ ምጣኔ ሀብታዊ ካርታ
    - ስዕሎችና ፎቶግራፎች
2. የማስተማር ዘዴ
    - ገለፃ
    - ውይይት
3. ቅድመ ዝግጅት
    - የአፍሪካ ተፈጥሮአዊ ካርታ ክፍል ውስጥ ያሳያሉ፡፡

**ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት**

***1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ***

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ትምህርቱን መጀመር ይችላሉ፡-

- የአፍሪካ ከፍተኛ ቦታዎች የሚባሉት የት አካባቢ ይገኛሉ? በእነዚህ አካባቢዎች የሕዝቦች ኑሮ በምን በምን ላይ የተመሠረተ ነው?
- የአፍሪካ ዝቅተኛ ቦታዎች የትኞቹ አካባቢዎች ናቸው::
- በዚህ አካባቢ የሚኖሩ የአፍሪካ ሕዝቦች አኗኗር በምን በምን ላይ የተመሠረተ ነው?

2. *የትምህርቱ አቀራረብ፦*

- የአፍሪካ ተፈጥሮአዊ ካርታ በማሳየት ትምህርቱን ይጀምሩ፡፡
- ተማሪዎች የአፍሪካን መልክአ-ምድር በተመለከተ የተለያዩ መረጃዎችን እንዲያሰሙ ያበረተታቷቸው፡፡ ስለ አፍሪካ ሕዝብ አኗኗርም ይነጋገሩ፡፡

**ረ. ምዘናና ክትትል**

1. *ምዘና*

የሚከተሉትን አይነት ጥያቄዎች ይጠይቁ

- የአፍሪካ ከፍተኛ ቦታዎች በየት በየት አካባቢ ይገኛሉ?
- በአፍሪካ ከፍተኛና ዝቅተኛ አካባቢ የሚኖሩት ሕዝቦች የአኗኗር ልዮነት አላቸውን? ልዮነታቸውን በምሳሌ አስረዱ፡፡

2. *ክትትል*

- ተማሪዎች የአፍሪካን ተፈጥሮአዊ ካርታ እንዲሠሩ ያድርጓቸው፡፡
- ከዚያም በሚከተሉት ነጥቦች ዙሪያ እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡
  - የአፍሪካ ከፈተኛ እና ዝቅተኛ ቦታዎችን በተመለከተ፡፡
  - በአፍሪካ ከፍተኛና ዝቅተኛ ቦታዎች አካባቢ የማኖሩ ሕዝቦች የአኗኗር ልዮነታቸውን በተመለከተ (ከምሳሌ ጋር)

## 1.9 የሕዝብ ሥርጭትን፣ አሠፋፈርንና አኗኗርን የሚወስኑ ነገሮች

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ፦ 2**

**ሀ. ከንዑስርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

*ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ*

- ሕዝብ በከተማ የሚሠፍርባቸውን ምክንያቶች ታብራራላችሁ፡፡

- የመገናኛ አውታሮች፣ የሕዝብ አለመረጋጋትና የደህንነት ጉዳዮች በሕዝብ ስርጭት፣ አሠፋፈርና አኗኗር ላይ ያላቸውን ተጽእኖ ታስርዳላችሁ::

**ለ. ይዘቶች**

- በከተማ ውስጥ የመስፈር ምክንያቶች (ምሳሌ አዲስ አበባና ሞምባሳ)
- የመጓጓዣ መስመሮች፣ ጦርነትና የእርስ በእርስ ብጥብጥ በሕዝብ ሥርጭት፣ አሠፋፈርና አኗኗር ላይ ያላቸው ተጽእኖ

**ሐ. የትምህርቱ መሰረት-ሃሳብ**

በአንድ ሀገር ሥርጭትን፣ አሠፋፍርና አኗኗርን የሚወሰኑ ተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ ምክንያቶች አሉ:: የመልክአ ምድር አቀማመጥና መገኛ፣ የአየር ንብረት፣ የተፈጥሮ ሀብትና የአፈር ዓይነት ለሕዝብ ስርጭትና ጥግግት፣ ለምጣኔ ሀብት ዕድገት ልዩነት፣ ለአኗኗር ዘይቤ መመሳሰልና መለያየት ወሳኝ ሚና አላቸው:: ከዚህ በተጨማሪ የመሠረተ ልማት መሟላት፣ በማኅበራዊ አገልግሎት ተቋማት በቅርብ መገኘትና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ለማካሄድ የሚያስችል ሁኔታ መኖር አንድን አካባቢ ለመኖሪያነት ተመራጭ ያደርገዋል::

በአፍሪካ የመሠረተ ልማት አውታሮችን ልማት ለማፋጠን የቴክኖሎጂና የምጣኔ ሀብት (ገንዘብ) ውስንነት አለ:: በዚህ ላይ ችግሩን የባሰ የተወሳሰበ የሚያደርገው በሀገሮች መሐከል በየጊዜው የሚካሄደው ጦርነትና የውስጥ የእርስ በእርስ ብጥብጥ ነው::

**መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴ**

1. የትምህረት መርጃ መሣሪያዎች
   - ካርታዎች
   - ስዕሎች
   - ፎቶግራፎች
   - ፊልሞች

2. የማስተማር ዘዴ
    - ገለፃ
    - ውይይት
    - የመስክ ጉዞ
3. ቅድመ-ዝግጅት
    - ከላይ የተዘረዘሩትን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ለተማሪዎች ያሳዩ፡፡
    - ለገለፃ እንዲመችም የአካባቢያችሁ መሠረተ ልማት የሚያመለክት ንድፍ ካርታ ያዘጋጁ፡፡

## ሠ. የመማር ማስተማር ሂደት

### *1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ*

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለተማሪዎችን በማቅረብ ትምህርቱን መጀመር ይችላሉ፡፡

- ለሰዎች በአንድ አካባቢ በብዛት መስፈር መሠረታዊ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?
- ጦርነትና የእርስ በእርስ ብጥብጥ በመሠረተ ልማት (መንገድ፣ የባቡር ሀዲድ ... ወዘተ) እድገትና በሕዝቦች አሠፋፈርና አኗኗር ሁኔታ ላይ ያላቸው ሚና ምንድ ነው?

### *2. የትምህርቱ አቀራረብ*

- በአፍሪካ ፓለቲካ ካርታ በመታገዝ ተማሪዎች በዋና ዋና ከተማዎች ስፈራ ዙሪያ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡
- አዲስ አበባና ሞምባሳ አሁን በሚገኙት ቦታ ላይ እንዲቆረቆሩ የደገፏቸውን ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች በተመለከተ ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡

- ጦርነትና ያለመረጋጋት ሕዝቦች ከቦታ ወደ ቦታ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ በተመለከተ ተማሪዎች እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡

**ረ. ምዘናና ክትትል**

*1. ግምገማ*

የሚከተሉትን አይነት ጥያቄዎች ይጠይቁ

- ለከተማ ሰፈራ እድገት መሠረቶቹ ምንድ ናቸው?

*2. ክትትል*

- በከተሞች የመጓጓዣ መስመሮች ሊጫወቱት የሚችሉትን ሚና በተመለከተ ተማሪዎች አጭር ጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

## የምዕራፍ አንድ የክለሳ ጥያቄዎች መልስ

**ሀ) የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ**

1. ሐሰት 3. ሐሰት 5. እውነት 7. እውነት
2. ሐሰት 4. እውነት 6. ሐሰት 8. እውነት

**ለ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ**

1. መ 2. መ 3. ሐ 4. ለ 5. ለ

**ሐ) የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በተገቢ ቃል ወይንም ሐረግ ሙሉ**

1. በ1886 ዓ.ም
2. የደቡብ
3. አንጻራዊ መገኛ
4. ናይል ወንዝ ሸለቆ
5. ማንሣ ሙሣ

**መ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ**

1. አፍሪካ ብዙ ውሃ በጥልቀት የሚገባባቸው ዳርቻዎች ወይም ጠረፋማ አካባቢዎች የሌላት መሆኗ ተፈጥሮአዊ ወደቦችን የማግኘት ዕድሏን አጥቦታል፡፡ በመሆኑም ወደቦችን ለማደራጀት ከፍተኛ ወጪ ይጠይቃል ማለት ነው፡፡
2. 30,335,000 ስኩዌር ኪሎ-ሜትር ነው፡፡
3. ዓለም- አቀፍ የቀን መለያ መስመር ከሌሎች ቋሚ መስመሮች የሚለየው በዓለም አቀፍ ደረጃ የጊዜ ርዝመት ወጥነት እንዲኖረው የጊዜ መስመር ሆኖ እንዲያገለግል በመወሰኑ ነው፡፡ ስለዚህም ከመነሻ ዋልቴ ተነስተን ወደ ምሥራቅ ስንጓዝ ጊዜ ይጨምራል፡፡ በተቃራኒው ከመነሻ ዋልቴ ተነሥተን ወደ ምዕራብ ስንጓዝ ጊዜ ይቀንሳል፡፡ ከዚህም በላይ ይህንን መስመር (180°) አቋርጠን ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ስንጓዝ አንድ ሙሉ ቀን ስንቀንስ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ይህንን መስመር ስናቋርጥ አንድ ቀን እንጨምራለን፡፡
4. ኒጀር ኮንጐ፣ አፍሮ እስያዊ፣ ናይሎ ሠሐራዊ፣ እና ኰይሣን ናቸው፡፡
5. “አሞሌ ጨው” ነበረ

# ምዕራፍ ሁለት

## የመሬት አወቃቀር

**ለምዕራፉ የተመደበው ጠቅላላ ክፍለ ጊዜ:- 12**

**የምዕራፉ ትምህርት ሲጠናቀቅ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**
**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኋላ:-**

- የመሬትን አወቃቀርና የቅርፊተ መሬት ልዩ ልዩ ክፍሎችን ይገልፃሉ፡፡
- የአለት ንብርብሮች እንቅስቃሴንና የሚያመጣውን የመሬት መንቀጥቀጥ ይገነዘባሉ
- የአለት አፈጣጠርን፣ዓይነትና የሚሰጠውን ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ ይለያሉ፡፡
- ንድፍ ካርታን ይስላሉ፡፡

**ንዑሳን ርዕሶች**

- በካርታ ላይ መረጃ መፈለግና መጠቀም
- የመሬት ንጣፍ
- የአለት ዓይነቶችና አፈጣጠር

### 2.1 ከካርታ ላይ መረጃ መፈለግና መጠቀም

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ: 6**

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ**

- የካርታን ምንነት ይተረጉማሉ፡፡
- የካርታን ጥቅሞች ያብራራሉ፡፡
- የአፍሪካን ንድፍ ካርታ በመስራት የሕዳግ መረጃዎችን ያሣያሉ፡፡

## ለ. ይዘቶች

- ካርታን መጠቀም
- የሕዳግ መርጃዎች (ርዕስ፣ አቅጣጫ፣ ቀን ወይም ዘመን፣ የካርታ መፍቻ)

## ሐ. የትምህርቱ መሰረተ-ሀሳብ

- ካርታ ማለት የመሬት ሙሉ ገጽ ወይም የተወሰነ ክፍል በመሥፈርት መሠረት ተቀንሶ የሚቀመጥበት ሠነድ ነው፡፡
- የሚሠራውም በካርታ ሥራ በሚገባ በሰለጠነ ባለሞያ ነው፡፡ ይኸም ባለሞያ ካርቶግራፈር በሚል ስም ይጠራል፡፡
- የአንድ ካርታ አቀራረብ፣ ተነባቢነትና ጠቀሜታው የሚወሰነው በመሥፈርቱ፣ በቀለም አጠቃቀሙ እና በሥራ ላይ ባዋላቸው ምልክቶች ነው፡፡
- መሥፈርት ማለት ካርታ ላይ በተሠጠ ርቀት እና እርሱ በሚወክለው ተመሳሳይ የመሬት ርቀት መሐከል ያለውን ሬሽዮ (መመዛዘን) የሚያመለክት ነገር ማለት ነው፡፡
- የአንድ ካርታ መሥፈርት ካርታው ውስጥ ማስቀመጥ የሚቻለውን የመረጃ መጠን ይወስናል፡፡ ይኸም ማለት ካርታው ባለትልቅ መሥፈርት ካርታ ከሆነ ካርታው ላይ የምናመለክተው መረጃ በቁጥሩ ትንሽ ሆኖ ነገር ግን ያንኑ መረጃ አጉልተን የምናሳይበት ሲሆን በአንፃሩ ካርታው ባለትንሽ መሥፈርት ከሆነ ግን የምናመለክተው መረጃ በርካታ ሆኖ ዳሩ ግን የመረጃዎቹ መጠን ተቀንሶ የሚታየበት ነው፡፡
- የካርታ ጥቅም ጥንታዊና ዘመናዊ በመባል በሁለት ይከፈላል፡፡

**ጥንታዊው የካርታ ጥቅም፡-**

- የጥንት ሰዎች ጥሩ የአደን አካባቢን፣ ከፍተኛ የውሃ ክምችት ያለበትን ሥፍራ ለማመልከትና ወደዚያም እንዴት መድረስ እንደሚቻል ለመጠቆም አሸዋ ላይ ካርታ ይሠሩ ነበር፡፡

**ዘመናዊው የካርታ ጥቅም፡-**

- ዘመናዊው የካርታ ጥቅም በጣም ብዙ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ካርታዎች የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ክስተቶችን ስርጭትና በመሐከላቸውም ያሉ ግንኙነቶችን ያመለክታሉ፣ ለምርምር ሥራ ያገለግላሉ፣ የድንበር ግጭቶችን መፍቻ ሠነድ ሆነው ያገለግላሉ፣ የአየር ጠባይ ትንበያ ማድረግ ያስችላሉ፣ ወ.ዘ.ተ.

- የካርታ የሕዳግ መረጃዎች የምንላቸው የሚከተሉት ናቸው፡- ርዕስ፣ መሥፈርት፣ የኮምፓስ አቅጣጫ፣ የቀለምና የምልክ ቶች መፍቻና የሕትመት ቀንና ዓመት ምህረት ናቸው፡፡
- ሦስት ዓይነት መስፈርቶች አሉ፡፡ እነርሱም፡-
  - ዐረፍተ ነገራዊ መስፈርት፡- 1 ሴንቲሜትር ለ1 ኪሎሜትር
  - በክፍልፋይ የሚወከል መስፈርት $\frac{1}{100}$ ወይንም 1:100
  - መስመራዊ መስፈርት 1 0 1 2 3 ኪ.ሜ

## መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ

### *1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች*

- ለተለያዩ ሥራ (ጥቅም) የተዘጋጁ የናሙና ካርታዎች
- የሕዳግ መረጃዎችን የያዙ ካርታዎች

### *2. የማስተማሪያ ዘዴዎች*

- ገለፃ
- የተግባር ገለፃ
- የቡድን ውይይት

### *3. ቅድመ ዝግጅት፡-*

- ከላይ የተገለጹትን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ያሰባስቡ፡፡

- የሕዳግ መረጃዎችን የሚያሳይና የተለየ ግልጋሎት ያለውን የግልዎን ካርታ ይሥሩ፡፡

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

### 1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ትምህርቱን መጀመር ይችላሉ፡፡

- ካርታ ማለት ምን ማለት ነው?
- የካርታ ግልጋሎቶች ምን ምን ናቸው?
- የካርታ ሕዳግ ላይ የሚገኙ መረጃዎች ምን ምን እንደሆኑ አስረዱ፡፡

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

- ጠቅለል ያለ የካርታን ትርጉም ለማቅረብ ይሞክሩ፡፡
- የሕዳግ መረጃዎችን በመጥቀስ የእያንዳንዱን መረጃ ጥቅም ያብራሩ፡፡
- ጥቂት የካርታ ጥቅሞችን ይጥቀሱ፡፡

## ረ. ምዘናና ክትትል

### 1. ምዘና

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቁ፡-

- ካርታ ማለት ምን ማለት ነው?
- የካርታ ግልጋሎቶች/ጥቅሞች ምን ምን ናቸው?
- የካርታ የሕዳግ መረጃዎች ምን ምን ናቸው?

### 2. ክትትል

- ተማሪዎችዎ ተስማሚ የሆነ የአፍሪካ ካርታ እንዲሠሩና በሚከተሉት ነጥቦች ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡
- የሠሩት ካርታ ለየት ያለ ግልጋሎት ምን እንደሆነ

- ካርታቸው ሕዳግ ላይ ያሠፈሯቸው የሕዳግ መረጃዎች ምን ምን እንደሆኑ

## 2.2 የመሬት ንጣፎች

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡ 4**

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኂላ**

- የመሬት ንጣፎችን ይገልፃሉ፡፡
- የቅርፊተ መሬት፣ ይዘቶችን ይለያሉ፡፡

**ለ. ይዘቶች፡-**

- ቅርፊተ መሬት፣ ማዕከለ መሬት እና እምብርት መሬት (የእያንዳንዳቸው ጥልቀት /ውፍረት)
- ዋና ዋና የቅርፊተ መሬት ይዘቶች፡-

**ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሀሳብ፡-**

ቅርፊተ መሬት የውጪኛው የመሬት ንጣፍ ሲሆን ውፍረቱም ልክ የፓም ፍሬ ልጣጭ ከሚበላው ክፍል ጋር ሲነፃፀር ያለውን ያክል ውፍረት ይመስላል፡፡ ቅርፊተ መሬት ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ እነርሱም፡- የውቅያኖስ ሥር ቅርፊተ መሬት (sima) እና አኀጉራዊ(የየብስ) ቅርፊተ መሬት (sial) ተብለው ይጠራሉ፡፡ የውቅያኖስ ሥር ቅርፊተ መሬት ውፍረቱ ከ4ኪሎ ሜትር እስከ 7ኪሎ ሜትር ሲደርስ ሙቀቱም እስከ 1200° ሴልሽየስ ይደርሳል፡፡ አህጉራዊ ቅርፊተ-መሬት ደግሞ ውፍረቱ እስከ 70 ኪሎሜትር ይደርሳል፡፡ ማዕከለ-መሬት ጥልቀቱ 2900 ኪሎሜትር ሲሆን የሙቀቱ መጠንም 5000° ሲልሽየስ ነው፡፡ ማዕከለ መሬት በአብዛኛው የተሠራው ከሲሊኬት አለቶች ስለሆነ በብረትና ማግኒዝየም የዳበረ ነው፡፡ የመጨረሻው የመሬት ንጣፍ እምብርተ

መሬት ጥልቀቱ እስከ 6371ኪሎሜትር የሚደርስ ሲሆን የ6000° ሴልሽየስ የሙቀት መጠን አለው።

## መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ

### *1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች*

- የፖም ፍሬ ወይም የተቀቀለ እንቁላል።
- ሦስቱን የመሬት ንጣፎች የሚያሳይ ሥዕል
- ሦስቱንም የመሬት ንጣፎች የሚያሳዩ የአለቶች ፎቶግራፎች።

### *2. የማስተማሪያ ዘዴዎች፡-*

- ገለፃ
- ሠርቶ ማሳየት
- የቡድን ውይይት
- የመስክ ጉብኝት

### *3. ቅድመ-ዝግጅት፡-*

- ከላይ የተጠቆሙትን ቁሳቁሶች ዝግጁ ማድረግ
- የመሬት ንጣፎችን የሚሳይ ሥዕል መሥራት
- የዕለቱን የትምህርት ዕቅድ ዝግጁ ማድረግ

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

### *1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ*

- ለተማሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማቅረብ ትምህርቱን መጀመር ትችላለህ/ትችያለሽ፡-
  - መሬት ስንት ንጣፎች አሏት?
  - የቅርፊተ መሬት ይዘቶች ምን ምን ናቸው?
  - በአኅጉራዊ እና በውቅያኖስ ሥር ያለ ቅርፊተ መሬት መሐከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

- የፓሞ ፍሬና የተቀቀለ እንቁላል ከመሬት ንጣፎች ጋር እንዴት ማመሳሰል ወይም ማያያዝ ይቻላል?
- የሦስቱ የመሬት ንጣፎች ይዘት ምንድነው? ወይም ከምን ከምን ነገሮች የተሠሩ ናቸው?

*2. የትምህርቱ አቀራረብ*

- የተቀቀለ እንቁላል ወይም የፓም ፍሬን በማስረጃነት በመጠቀም መሬት ከንጣፎች እንዴት እንደተሠራች ገለፃ ያድርጉ፡፡
- የሦስቱን የመሬት ንጣፎች ውፍረትና ሙቀት በተመለከተ ተማሪዎች ማብራሪያ እንዲሰጡ ያበረታቷቸው፡፡
- ተማሪዎች የሦስቱ የመሬት ንጣፎች ይዘቶችን (አፈር፣ ውሃ እና አለት) ፎቶግራፍ በመጠቀም ገለፃ እንዲያደርጉ ይጠይቋቸው፡፡

**ረ. ምዘናና ክትትል**

*1. ምዘና*

- ለተማሪዎችዎ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያቅርቡ፡-
  - የሦሥቱን የመሬት ንጣፎች ስም ጥቀሱ፡፡
  - የሁለቱን የቅርፊተ-መሬት ክፍሎች በመለየት ግለጹ፡፡
  - የውፍረትና የሙቀት መጠናቸው ጋር በተያያዘ የመሬት ንጣፎች ባሕርይ ወይም ተፈጥሮ ምን ይመስላል?

*2. ክትትል*

- ተማሪዎችዎ የሚከተሉትን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ያበረታቷቸው፡-
  - የመሬት ንጣፎችን የሚያሳይ ሥዕል በመሳል የእያንዳንዱን ንጣፍ ስም፣ ውፍረት እና የሙቀት መጠን እንዲያመለክቱ

- የመሬት ንጣፎችን የሚያሳይ ፎቶግራፍ እንዲፈልጉና ከዚህ ፎቶግራፎ የንጣፎቹን ይዘት እንዲለዩ
- የውፍረትና የሙቀት መጠናቸው ጋር በተያያዘ የመሬት ንጣፎችን ባሕርይና ተፈጥሮ በተመለከተ ውይይት እንዲያደርጉና ሪፖርት በተወካያቸው በኩል ለአጠቃላይ ክፍሉ እንዲያቀርቡ

## 2.3. የአለት ዓይነቶችና አፈጣጠር

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡ 2**

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

**ተማሪዎች ይህንን ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- የአለት ዓይነቶችን አፈጣጠር ይለያሉ፡፡
- የአለቶችን ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ ያስረዳሉ፡፡
- አለቶች በኢትዮጵያ ያላቸውን ጠቀሜታ ይገልፃሉ፡፡

**ለ. ይዘቶች**

- የአለቶች አፈጣጠር
- የአለት ዓይነቶችና ጥቅሞቻቸው፡፡ (ቅልጥ አለት፣ ዝቅጥ አለት እና ልውጥ አለት)
- ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ ያላቸው አለቶች

**ሐ. የትምህርቱ መሠረተ-ሀሳብ**

አለት ከተለያዩ ማዕድናት ስብስብ የተፈጠረ ነው፡፡ አንድ ማዕድን አንድ ወይም ከዚያ የሚበልጡ ኬሚካላዊ ንጥረ-ነገሮች የያዘ ሲሆን ግልጽ የሆነ ፊዚካዊ አቋምና ኬሚካላዊ ጥንቅር አለው፡፡ በአለት ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ኬሚካላዊ ንጥረ-ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡- ኦክሲጅን(47%)፣ ሲሊኮን(8%)፣ ብረት (5%)፣ አሉሚኒየም (8%)፣ ካልስየም (4%)፣ ሶድየም፣ ፓታስየም እና ማግኔዝየም

(እያንዳንዳቸው ከ2 እስከ 3%)፡፡ እነዚህ ኬሚካላዊ ንጥረ ነገሮች በአንድነት የቅርፊተ መሬት 98% ይይዛሉ፡፡ የአለት ዓይነቶች በቀለም፣ በጥንካሬ እና ባላቸው የልስላሴና የሸካራነት ባሕርይ ይለያሉ፡፡ ከዚህም በላይ በአመጣጥና አፈጣጠራቸውም ይለያሉ፡፡ ስለሆነም አለቶች በአፈጣጠራቸውና በዕድሜያቸው ይመደባሉ፡፡ ቅልጥ አለቶች (ግይ አለቶች) ውስጣዊ (አጎጥጓጭ ግይ አለት) ወይም ውጪያዊ (አግጣጭ ግይ አለት) ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ውጪያዊ የሚሆኑ በገሞራ ትፍነት ወደ ውጪ ወጥተው በመቀዝቀዝ ጠጣር አለቶች ሲሆኑ ነው፡፡ ውስጣዊ የሚሆኑት ደግሞ ገሞራ ህፅሞ በቅርፊተ መሬት ውስጥ በመቀዝቀዝ ጠጣር አለት ሲሆን ነው፡፡ ዝቅጠት አለት የሚፈጠረው ቀድሞ ከነበሩ አለቶች በፍርፈራና በሸርሸራ አማካይነት ነው፡፡ ስለሆነም በአፈጣጠሩ ሁለተኛ ነው ማለት ነው፡፡ አለቱ የንጣፍ ንብርብሮሽ ይታይበታል፡፡ በሌላ አካባቢ ደግሞ ይኸ አለት መሠረቱ የሞቱ እንስሳትና የወዳደቁ ተክሎች ብስባሽ ሆኖ ይገኛል፡፡ ልውጥ አለቶች እንደስማቸው ልውጥ ናቸው፡፡ በጊዜ ሂደት ግን ቅልጥ አለቶችና ዝቅጠት አለቶች በንክኪ ልውጠትና በሀይለኛ(ዳይናሚክ)ልውጠት አማካይነት ወደ ልውጥ አለትነት ይቀየራሉ፡፡ አለቶች የሚመደቡበት ሁለተኛው ሥርዓት ደግሞ ዕድሜያቸውን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ በዝቅጠት አለት ውስጥ የሚገኙ ማዕድናት ማለትም እንደ ከሰል፣ የተፈጥሮ ጋዝ እና ፔትሮልየም የመሳሰሉ የኃይል ምንጭ ናቸው፡፡ የልውጥ አለት ማዕድናት ብረት ነክ ማዕድናት፣ ወርቅ፣ አልማዝ፣ መዳብ፣ ብረት፣ ፕላቲንየም፣ እርሳስ እና ኒኬል የመሳሰሉት ለጌጣጌጥ፣ ለግንባታ፣ ለኤሌክትሪክ መሣሪያዎች፣ለኢንዱስትሪ መሣሪያዎች፣ ለፋብሪካ ያገለግላሉ፡፡ የግይ አለት ማዕድናትም ቢሆን ለመንገድና ሕንፃ ግንባታ የሚያስፈልጉ ንጥረ ነገሮች ናቸው፡፡

## መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች

### 1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፡-

- የናሙና አለቶች
- የአለቶችን አፈጣጠርና ሂደት የሚያሳይ ሥዕል (ቻርት)

### 2. የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች፡-

- ገለፃ
- ሠርቶ ማሳየት
- የመስክ ጉብኝት

### 3. ቅድመ-ዝግጅት፡-

- ከላይ የተጠቀሙትን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በማሰባሰብ ክፍል ውስጥ ለዕይታ በሚያመች መልክ ግድግዳ ላይ መሰቀል፡፡
- ተማሪዎች የተለያዩ የአለት አፈጣጠር መንገዶችን የሚመለከት ፅሁፍን በማንበብ ክፍል ውስጥ ለሚካሄድ ውይይት ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ማድረግ
- ተማሪዎች የአለት አይነቶችን መለየት እንዲችሉ ለማድረግ እና ስለአፈጣጠራቸውም ግንዛቤ እንዲኖራቸው የመስክ ጉብኝት ማቀድ፡፡

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

### 1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ

- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለተማሪዎች በማቅረብ ትምህርቱን መጀመር ይቻላል፡-
  - ወደ ክፍል ያመጧቸውን የናሙና አለቶች በማሳየት ዓይነታቸውና የአፈጣጠራቸውን መንገድ እንዲለዩ መጠየቅ
  - የአለቶችን የተለያዩ ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ እንዲገልፁ መጠየቅ

### *2. የትምህርቱ አቀራረብ*

- የእያንዳንዱን የአለት አፈጣጠር መግለጽ
- ክፍል ውስጥ ይዘውት የመጡትን የአለቶች የአፈጣጠር ሂደት (ዑደት) የሚያሳየውን ቻርት ያብራሩ።
- ተማሪዎች ዋጋ (ጠቀሜታ) ስላለቸው አለቶችና ማዕድናት ስምተው የሚያውቁ ከሆነ ስለእነሱ አንዳንድ ነገር እንዲናገሩ ይጠይቋቸው።
- በመጨረሻም ተማሪዎችዎ የኢትዮጵያ የማዕድናት ካርታን እንዲገለብጡ በማድረግ ስለአንዳንድ ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ ስላላቸው ማዕድናት በርስዎ መሪነት ተወያዩ።

## ረ. ምዘናና ክትትል

### *1. ምዘና*

- ተማሪዎችዎን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡-
  - በዓለም ላይ ስንት ዓይነት ማዕድናት አሉ?
  - እያንዳንዱ አለት እንዴት ነው የተፈጠረው?
  - የቅልጥ (ግይ) አለት ዓይነቶች ምን ምን ተብለው ይጠራሉ?
  - የአለት ዓይነቶችን እድሜ የምናውቀው እንዴት ነው?
  - የአለቶች ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታዎች ምን ምን ናቸው?

### *2. ክትትል*

- ተማሪዎች የሚከተሉትን ሥራዎች ያከናውኑ፡-
  - በየመኖሪያ አካባቢያቸው የመስክ ጉብኝት በማድረግ ለናሙና የሚሆኑ አለቶችን እንዲሰበስቡ ይደረግ። በኋላም በዓይነት በአይነታቸው ለመመደብ በሚያደርጉት ጥረት ይርዷቸው።
  - ተማሪዎች የማዕድናት ስርጭትን የሚያሳይ የኢትዮጵያ ካርታ እንዲሰሩ ያድርጉ።

## የምዕራፍ ሁለት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ

**ሀ) የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች እውነት ወይም ሐሰት በሉ፡፡**

1. እውነት
2. እውነት
3. ሐሰት
4. ሐሰት
5. እውነት

**ለ) በ“ሀ” ረድፍ ሥር የሚገኙትን በ“ለ” ረድፍ ሥር ከሚገኙት ጋር አዛምዱ፡፡**

1. ሐ
2. መ
3. ሀ
4. ለ

**ሐ) ከዚህ በታች ለተሰጡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. ሐ
2. ለ
3. መ
4. መ
5. መ

**መ) ባዶውን ሥፍራ በትክክለኛ ቃል ወይም ሐረግ ሙሉ፡፡**

1. የጎዳግ መረጃውን
2. የሞሆ ዲስኮንቲንዊቲ
3. ልውጠት (metamorphism)
4. የካርታው ራስጌ (የካርታው አናት)
5. ሥዕላዊ መስፈርት (የመስመር መስፈርት)

**ሠ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ፡፡**

1. ሀ) ቅርፊተ መሬት የመሬት የውጪኛው ንጣፍ ነው፡፡ የተሠራውም በዋነኛነት ከዝቅጠት አለት ሲሆን ከሥሩም ጠንካራ ቅልጥ አለት እንደ ከረጭ ድንጋይ እና ኮተቤ ድንጋይ የያዘ ነው፡፡

   ለ) ማዕከለ መሬት ብረትና ማግኔዝየም የመሳሰሉት የስሊኬት አለቶች በብዛት የሚገኙበት የመሬት ንጣፍ ከመሆኑም በላይ በከፊል የቀለጠ ንጣፍ ነው፡፡

ሐ) እምብርተ- መሬት ብረትና ኒኬል በብዛት የያዘ ሲሆን የውጨኛውና የውስጠኛው እምብርተ- መሬት ተብሎ በሁለት የተከፈለ ነው፡፡ የውጨኛው እምብርተ-መሬት በከፊል የቀለጠ ሲሆን የውስጠኛው እምብርተ-መሬት ጠጣር ነው፡፡

2. ሀ) የካርታ ርዕስ፡- ማንኛውም ካርታ ርዕስ ወይም ስም አለው፡፡ እያንዳንዱ ካርታ ርዕስ ያለው በመሆኑ ከሌሎች ካርታዎች በቀላሉ መለየት ይቻላል፡፡

ለ) መሥፈርት፡- በመሬትና በካርታ ላይ የሚታየውን የቦታ ርቀት፣ ስፋት ከፍታና መጠን የምናዛምድበት ልኬት ነው፡፡

ሐ) አቅጣጫ ጠቋሚ ቀስት፡- ካርታ ጎዳግ ላይ የሚሠፍር ሰሜን አቅጣጫን የሚያመለክት ቀስት ነው፡፡ ከዚህ ቀስት በስተቀኝ ምስራቅ አቅጣጫ ሲሆን ከቀስቱ በስተግራ በኩል የሚገኘው ደግሞ ምዕራብ አቅጣጫ ነው፡፡ ከሰሜን በተቃራው ያለው አቅጣጫ ደቡብ አቅጣጫ ነው፡፡

መ) የኅትመት ዘመን፡- ካርታው መቼ እንደታተመ አመልካች ነው፡፡ የኅትመት ዘመኑን በመመልከት የምንፈልገውን ዓይነት ካርታ መምረጥ ያስችለናል፡፡

ሠ) የምልክቶችና የቀለማት መፍቻ፡- ካርታውን ለማንበብ የሚረዳን ወሳኝ የጎዳግ መረጃ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# ሥርዓተ ምህዳር እና ተጽእኖ የሚያሳድሩበት ነገሮች

**ለምዕራፉ የተመደበው ጠቅላላ ክፍለ ጊዜ፡- 16**

**የምዕራፉ ትምህርት ሲጠናቀቅ የሚጠበቁ ውጤቶች፡**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኋላ**

- የአፍሪካ የእጽዋትና የዱር እንስሳት ስርጭትን! ጠቀሜታንና ተጽእኖ የሚያሳድሩ ነገሮችን ይገነዘባሉ፡፡
- የንፁሕ የመጠጥ ውኃ ሀብት መኖርና የሚያጋጥሙ ሥጋቶችን ይረዳሉ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብቶች እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል ይገነዘባሉ፡፡

**ንዑሳን ርዕሶች**

- የተፈጥሮ ሀብቶች
- የተፈጥሮ እጽዋትና የዱር እንሰሳት
- ውኃ፣ አፈርና አየር
- የተፈጥሮ ሀብትን ለመንከባከብ የሚወሰዱ እርምጃዎች

## 3.1.1 የተፈጥሮ እጽዋትና የዱር እንስሳት

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡ 6**

### ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

***ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኂላ፡-***

- የአፍሪካን የተፈጥሮ እጽዋት በካርታ ላይ ያመለክታሉ፡፡
- ዋና ዋና የአፍሪካ የዱር እንስሳትን ይዘረዝራሉ፡፡

- የአፍሪካ የዱር እንስሳትን ከአካባቢያቸው ጋር ያዛምዳሉ፡፡
- እንሰሳት እጽዋት የብዝኀ ሕይወት ክፍሎች እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡
- እጽዋት ከጠፉ የዱር እንስሳትም አብረው እንደሚጠፉ ይረዳሉ፡፡
- የሰው ልጅ እንቅስቃሴ በዱር እንሰሳት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚያደርስ ያብራራሉ፡፡
- የአየር ንብረት መዛባትን ለመከላከል መሥራት እንደሚቻል ያላቸውን ያንፀባርቃሉ፡፡

## ለ. ይዘቶች

- የተፈጥሮ እጽዋትና የዱር እንስሳት
- የተፈጥሮ እጽዋትና የዱር እንስሳት ግልጋሎት (ጥቅሞች) (ከሣይንስ፣ ከምጣኔ ሀብትና ከአካባቢ ሁኔታ ጋር በተያያዘ)
- የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት ላይ ተጽንዖ የሚያሳድሩ ነገሮችና ውጤቶቻቸው(ለምሳሌ፡- የሕዝብ ብዛት የሚፈጥረው ጫና፣ የሕዝብ የግንዛቤ ችግርና ድህነት … ወ.ዘ.ተ.)
- የብዝኃ ሕይወት (ባዮዳይቨርስቲ) መጥፋት ወይም መመናመን

## ሐ. የትምህርቱ መሠረተ-ሀሳብ

አፍሪካ አምስት ዓይነት የተፈጥሮ እጽዋት አሏት፡፡ እነርሱም፡- የሐሩር አውራጃ ዝናባማው ደን፣ የሐሩር አውራጃ የሣር ምድር፣ የበረሃማና ከፊል-በረሃማ አካባቢዎች የተፈጥሮ እጽዋት፣ የሜዲትራንያን አካባቢ የተፈጥሮ እጽዋት እና የሐሩር አውራጃ ከፍታማ ቦታዎች የተፈጥሮ ዕጽዋት ናቸው፡፡

- የምድር ወገብ(የሐሩር አውራጃ) ዝናባማው ደን የሚገኘው ከምዕራብ አፍሪካ ተነስቶ የሩዋንዳንና ቡሩንዲን ከፍታማ ቦታዎች፣ ከቶጎና ቤኒን በስተቀር የምዕራብ አፍሪካ ጠረፋማ አካባቢዎችን የሚሸፍን ሲሆን ከፍተኛ ዝናብና ርጥበት እንዲሁም ከፍተኛ ሙቀት አለው፡፡ ደኑም ጥቅጥቅ ያለ ከመሆኑም በላይ

ከፍተኛው፣ መሀከለኛው እና ዝቅተኛው በመባል የሚታወቅ ደረጃዎች አሉት፡፡ በርካታ የዛፍ ዝርያዎች ያሉት ሲሆን ታዋቂ የሆኑ ዛፎችም ለምሳሌ፡- እንደ ማሆጋኒ፣ ሮዝውድ፣ አይረን ውድ፣ ኢቦኒ የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

- የሐሩር አውራጃ የሣር-ምድር እጽዋት ሣርና ዛፎች የሚገኙበት ሲሆን የምድር ወገብ ዝናባማው ደንን ዙሪያ ይሸፍናል፡፡ ከምድር ወገብ በሰተሰሜን ያለው የሣር ምድር ከምዕራብ ጠረፍ እስከ ምሥራቅ ጠረፍ ተንሰራፍቶ ይገኛል፡፡ ይሄ የሣር ምድር ከፍተኛው የሐሩር አውራጃ የሣር ምድር፣ የፓርክ መልክ ያለው የሐሩር አውራጃ የሣር-ምድርና ቁጥቋጦአማ የሀሩር አውራጃ የሣር ምድር በሚል ሦስት ቦታ ይከፈላል፡፡
- የበረሃና ከፊል በረሃማ የተፈጥሮ እጽዋት፡- እነዚህ አካባቢዎች ምንም እንኳ የበረሃማነት ጠባይ ቢኖራቸውም ሙሉ በሙ እጽዋት አልባዎች አይደሉም፡፡ ራሳቸውን ከአካባቢው ጋር አስማምተው የሚኖሩ ዜሮፋይትስ እየተባሉ የሚጠሩ አጫጭር ሣሮችና የጫጩ ዛፎች የሚገኙበት አካባቢ ነው፡፡ ምሳሌ፡- የቁልቋል ዛፍ፡-
- የሜዲትራኒያን አካባቢ የተፈጥሮ እጽዋት፡- የዚህን ዓይነት የተፈጥሮ እጽዋት በአህጉሪቱ ሰሜንና ደቡብ ጫፎች አካባቢ ይገኛሉ፡፡ ርጥበት በአለበት አካባቢ የቡሽ ዛፎችና የመሳሰሉት ይገኛሉ፡፡ ከዚህም በላይ ማኩዊስ እየተባሉ የሚጠሩ፡፡ አጫጭር ቁጥቋጦዎች (ማለትም ምንጊዜም ባለአረንጓዴ ቅጠሎችና እሾሀማ ተክሎች) እንዲሁም ሣሮች በስፋት ይገኛሉ፡፡
- የሐሩር አውራጃ የከፍታማ ቦታዎች የተፈጥሮ እጽዋት፡- የዚህን ዓይነት እጽዋት በሐሩር አውራጃ ከፍተኛ ቦታዎች በሙሉ ይገኛሉ፡፡ በከፍታቸውም ምክንያት የእነዚህ አካባቢዎች ሙቀት ዝቅተኛ ነው፡፡ እነዚህ ከፍታማ ቦታዎች የታችኛው ክፍላቸው ላይ ትክክለኛውን የሐሩር አውራጃ ደኖች ማግኘት አስቸጋሪ

ነው፡፡ በምትኩ በብዛት የሚገኙት ለምሳሌ ምሥራቅ አፍሪካ አካባቢ ባሉ የሀሩር አውራጃ ከፍታማ ቦታዎች የተመናመነ የሣር ሽፋንና ተራርቀው የሚገኙ ዛፎች ማየት የተለመደ ነው፡፡ ከባሕር ወለል በላይ 2000 ሜትር አካባቢ የቀርከሀ ደን ሲኖር ከዚያ በላይ በሆነ ከፍታ ላይ ግን አጫጭር ዛፎችና ቁጥቋጦዎች ይገኛሉ፡፡

- አፍሪካ በዱር እንስሳት ሐብት እጅግ የበለፀገች አኅጉር ነች፡፡ በምድር- ወገብ ዝናባማው ደን ውስጥ ደማቅ ቀለም ያላቸው ወፎች፣ ጦጣና ዝንጀሮዎች፣ በአፍሪካ ውስጥ ብቻ የሚገኘው ጎሬላ ተብሎ የሚጠራው ገመሬ ዝንጀሮች ሲገኙ የሐሩር አውራጃ የሣር ምድር ደግሞ ሳር በል እና ሥጋ በል የሆኑ በርካታ እንስሳትን የያዘ ነው፡፡

## መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች

### *1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች*

- የተፈጥሮ ደኖችና የዱር እንስሳት ስርጭትን የሚያሳዩ የአፍሪካና የዓለም ካርታዎች

### *2. የማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች*

- ገለፃ
- ውይይት
- ሠርቶ ማሳየት

### *3. ቅድመ- ዝግጅት*

- ለሠርቶ ማሳያ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ማሰባሰብ
- ይህን ትምህርት በተመለከተ ተገቢነት ያላቸውን የማጣቀሻ መጻሕፍት ተማሪዎች በቅድሚያ አንብበው እንዲዘጋጁ መንገር፡፡

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

### 1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ

- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለተማሪዎች በማቅረብ የዕለቱን ትምህርት መጀመር ይቻላል፡፡
  - የተፈጥሮ እጽዋት የሚለውን ቃል ተርጉሙ፡፡
  - የተፈጥሮ እጽዋት ግልጋሎቶችን (ጥቅሞችን) ዘርዝሩ
  - በአፍሪካ ውስጥ የሚገኙትን የተፈጥሮ እጽዋት ዓይነቶች ዘርዝሩ
  - የዱር እንስሳት ምን ማለት እንደሆነ ግለጹ
  - የዱር እንስሳት ግልጋሎቶች(ጥቅሞች) ምን ምንድ ናቸው?

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

- በተማሪዎች መማርያ መጽሐፍ ውስጥ በዚህ ንዑስ ርዕስ ላይ ያለውን መረጃ እና ሥዕል መሠረት በማድረግ የተፈጥሮ እጽዋት ትርጉምን፣ ስርጭትና ጠቀሜታውን በተመለከተ ገለፃ ማድረግ፡፡ እንዲሁም የዱር እንስሳትን፡፡
- ተማሪዎች የተፈጥሮ እጽዋትና የዱር እንስሳት ስርጭት በዓለም አቀፍ ደረጃ ልዩነት ያለው መሆኑን መረዳት እንዲችሉ ማገዝ፡፡ በዚህ አጋጣሚም የሰው ልጅ ጣልቃ ገብነትንም እንዲያስተውሉ መርዳት፡፡

## ረ. ምዘና እና ክትትል

### 1. ምዘና

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተማሪዎች እንዲመልሱ ማድረግ፡-

- የበረሃማ አካባቢ የተፈጥሮ እጽዋት ቁልቋልና እሾሃማ ቁጥቋጦዎች ናቸው፡፡ የበረሃ የተፈጥሮ እጽዋት ዜሮፋይት በሚል ስም ይጠራሉ፡፡ ይህ ለምን የሆነ ይመስላችኋል?
- የተፈጥሮ እጽዋት ውድመት በዱር እንስሳት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተጽእኖ አብራሩ፡፡

- በዛፍ ላይ እንስሳት የከበረው የአፍሪካ ክፍል የትኛው ነው?
- በሐሩር አውራጃ ክልል ምን ምን ዓይነት የተፈጥሮ እጽዋትና የዱር እንስሳት እናገኛለን? ይህ ለምን ሆነ? ጥቂት ምሳሌዎችን ጥቀሱ።

*2. ክትትል*

ተማሪዎች የሚከተሉትን ተግባራት እንዲያከናውኑ

ማበረታታት፡-

- አንድ የአፍሪካና ሌላ አንድ የኢትዮጵያ ካርታ ይሥሩ።
- በአፍሪካ ካርታ ላይ የተፈጥሮ እጽዋት ስርጭትን ሲያመለክቱ በኢትዮጵያ ካርታ ላይ ደግሞ የዱር እንስሳት ስርጭትን እንዲያሳዩ ይደረግ።

**3.1.2 ውሃ፣ አፈርና አየር**

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡ 4**

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ካጠናቀቁ በኋላ**

- የሰው ልጅና ውኃ ያላቸውን ግንኙነት ያብራራሉ።
- በአፍሪካ ያለውን ንፁሕ የመጠጥ ውኃ አቅርቦትና እጥረትን ማወዳደር ይችላሉ።
- በአፍሪካ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የንፁሕ የመጠጥ ውኃ ሥጋቶችንና መነሻቸውን መገመት ይችላሉ።
- በአፍሪካ የአፈር ለምነት የሚከላበትን ሁኔታ ይለያሉ።
- በከተሞች አካባቢ የሚከሰተው የአየር ብክለት ምክንያቶችን ይተነትናሉ።

**ለ. ይዘቶች**

- ውኃ ለሕይወት ያለው ጠቀሜታ
- የመጠጥ ውሃ ችግሮች (ማለትም ከንፅሕና፣ ከከተማ እድገት፣ ከፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ ጋር በተያያዘ)

- የአፈር ለምነት የማጣት ችግር
- በከተሞች የአየር ብክለት መንስኤዎች

## ሐ. የትምህርቱ መሠረተ-ሀሣብ

ውኃ በምድር ላይ በሕይወት የሚገኙ አካላት እንደ ሰው፣ የእፅዋት ዝርያዎች እና እንስሳት የመሳሰሉት በሙሉ ኑሮአቸውን ያለስጋትና ችግር ለመቀጠል ከሚያስፈልጓቸው ነገሮች መሐከል ዋነኛው ነው፡፡ ከመሬት የቆዳ ስፋት 70% የሚሆነው በውኃ የተሸፈነ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የተፈጥሮ ሀብት በዓለም ዙሪያ በእኩልነት የተሰራጨ አይደለም፡፡ የቀላይና የውኃ ሀብት መገኛዎች የገፀ-ምድር ውኃ፣ የከርሰ-ምድር ውኃ፣ የውቅያኖስ ውኃ፣ በትነት መልክ ያለ ውኃና የቀዘቀዘ (የበረዶ ውሃ) ናቸው፡፡ ከውኃ ግልጋሎቶች (ጠቄሜታዎች) የሚከተሉት ጥቂቶች ናቸው፡፡ እነርሱም፡- የቤት ውስጥ ግልጋሎት፣ የኢንዱስትሪ ግልጋሎት፣ የእርሻ ግልጋሎት፣ የኃይል ምንጭ፣ የመጓጓዣ ግልጋሎት፣ የአካባቢ ደህንነት ግልጋሎት የመዝናኛ ግልጋሎትና ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታዎች ናቸው፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የውኃ ዋነኛው ችግር ብክለት ነው፡፡ ብክለት ሲባል በውኃ ጥራት ላይ አላስፈላጊ የሆነ ለውጥ መከሰት ማለት ነው፡፡ የተበከለ ውኃ ራሱን የማጥራት ወይም የማደስ የተፈጥሮ አቅም የቀነሰ ወይም ከነጭራሱ ያጣ ማለት ነው፡፡ ከዚህም በላይ የተበከለ ውኃ ለመጠጥም ሆነ ለመታጠቢያ የማይሆን፣ መጥፎ ሽታ ያለው፣ የበርካታ በሽታዎች ምንጭና የጤንነት ጠንቅ ነው፡፡ የውኃ መበከል ዋነኛ ምክንያቶች የሽንት ቤት ፈሳሽ ቆሻሻና የኢንዱስትሪ ዝቃጭ፣ ከመስኖ የሚወጡ የኬሚካል ፍሳሾች፣ የብረታ ብረት፣ የጨው ዝቃጮች ናቸው፡፡ ሽርሽራ የሚከተሉትን ሊይዝ ይችላል፡- የውኃ ሽርሽራ፣ የንፋስ ሽርሽራ በመጥፎ የእርሻ አያያዝ ልምድ የሚከሰት ሽርሽራ የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ልክ ተፈጥሮአዊ የውኃ በካይ ነገሮች እንዳሉ ሁሉ ተፈጥሮአዊ የአየር በካይ ነገሮችም አሉ፡፡ ይሁን እንጂ ሠው ሠራሽ በካዮችም አሉ፡፡ የአየር በካይ ከሆኑት ነገሮች መሐከል

ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡- ከቃጠሎ የሚወጣ ጭስ፣ ንፋስ ያስነሳው አቧራ የመሳሰሉት ናቸው። እነዚህ በሙሉ ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች ሲሆኑ ሠው ሠራሽ የሆኑት በካዮች ደግሞ፡- ቅሪተ አካሎችን (ፎሲል) ማቃጠል፣ ከነዳጅ የሚወጣ ጭስ፣ የኢንዱስትሪ ጭስ፣ ደረቅ ቆሻሻዎችን ማቃጠል፣ በእርሻ ምክንያት የሚከሰት ቃጠሎና የደን ቃጠሎ ናቸው።

## መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ

### *1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፡-*

- ሽርሸራን፣ የውኃና የአየር መበከልን የሚያሳዩ ፎቶግራፎች
- የስላይድ ፊልሞች

### *2. የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች፡-*

- ገለፃ
- ውይይት
- ሠርቶ ማሳየት፡-

### *3. ቅድመ-ዝግጅት*

- ከላይ የተገለፁትን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ማሰባሰብ፡-

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

### *1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ*

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተማሪዎች መልስ እንዲሰጡባቸው ማቅረብ፡-

- የውኃ መገኛ ዋነኛ ምንጮች ምን ምን ናቸው?
- የውኃና የአየር በካይ ከሆኑት ጥቂት ምሳሌዎችን ስጡ።
- የአፈር መሸርሸር ስንል ምን ማለታችን ነው?
- በመጠጥ ውኃ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ደኅንነቱን የሚጐዱ አስቸጋሪ ነገሮች ወይም አደጋዎች (threats) የምንላቸው ምን ምን ናቸው? በጋራ ተወያዩ።

- ውኃ ለምን እንደሚያስፈልገን በጋራ ተወያዩ።
- በአፍሪካ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ በተጨባጭ ያለውን የንፁሕ ውኃ መጠንና ወደፊት በጥቅም ላይ ሊውል የሚችለውን የንፁሕ ውኃ መጠን የሚያመለክት አህዝ ለተማዎች ይቅረብላቸው። ከዚያም አሁን ባለውና በሚፈለገው መጠን ባለው ልዩነት ላይ ውይይት ያካሂዱ። በመጨረሻም ለምን እንዲህ እንደሆነ የራሳቸውን ምክንያቶች ያቅርቡ።

*2. የትምህርቱ አቀራረብ*

- በመጠጥ (ንፁሕ) ውኃ፣ በንፁሕ አየር፣ በሸርሸራና በአፈር መመናመን ዙሪያ ገለፃ ማድረግ
- በአፍሪካ ውስጥ የንፁሕ ውኃ ስጋቶች (አደጋዎች) የሚባሉትን የወደፊት ሁኔታ ግምት መስጠትና ምክንያቶቻቸውንም መግለጽ።
- የከተማ አየር የብክለት ምክንያቶችን መተንተን።
- በአፍሪካ ውስጥ አፈርን ሊሸረሽሩ ይችላሉ ተብሎ እንደ ስጋት (አደጋ) የሚቆጠሩትን ነገሮች መለየትና ለተማሪዎች ማሳወቅ፡-
- በአሁኑ ጊዜ በአፍሪካ ውስጥ በተጨባጭ ባለው ንፁሕ የመጠጥ ውኃ አቅርቦትና በእጥረቱ መሐከል ያለውን ልዩነት ተማሪዎች እንዲያወዳድሩ ማድረግ።

## ረ. ምዘና እና ክትትል

*1. ምዘና*

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተማሪዎች መልስ እንዲሰጡባቸው ማቅረብ

- የአፍሪካ የውኃ መገኛ ምንጮች ምን ምንድናቸው?
- በአፍሪካ ውስጥ የውኃ እጥረት የሚታይባቸው አካባቢዎች የትኞቹ ናቸው?

- በኢትዮጵያ የትኞቹ ምክንያቶች ናቸው ለአፈር መሸርሸር ዋነኛ የሆኑት?

*2. ክትትል*

- የአየርና የውኃ ብክለትን እንዲሁም ውጤቶቻቸውን፣ የአፈር መመናመን፣ መሸርሸርንና ውጤቶቻቸውን የሚያሳዩ ፎቶግራፎች ተማሪዎች እንዲሰበስቡ ማድረግ፡-
- የተሰበሰቡትን ፎቶግራፎች መሠረት በማድረግ ከላይ በምዘናው ክፍል ላይ በቀረቡት ጥያቄዎች ዙሪያ ተማሪዎች የጋራ ውይይት እንዲያካሄዱና ሃሣብ እንዲለዋወጡ ማድረግ።

## 3.1.3 የተፈጥሮ ሀብትን ለመንከባከብ የሚወሰዱ እርምጃዎች

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡ 6**

### ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት፡-

**ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ፡-**

- እጽዋትን መንከባከብ ከሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች ጋር ያለውን ትስስር ይገልፃሉ።
- የተፈጥሮ እጽዋት ጥበቃን  ከሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች ጥበቃና እንክብካቤ ጋር ማዛመድ ይችላሉ።
- የውኃ እና የአየር ብክለትን እንዴት መከላከል ወይም መቆጣጠር እንደሚቻል ያብራራሉ።
- የውኃን ንጽሕና ለመጠበቅ ጥረት ያሳያሉ።

### ለ. ይዘቶች

- የተፈጥሮ ሀብቶች ተደጋፊነት
- የውኃና የአየር ብክለትን መቆጣጠር
- አማራጭ የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠበቂያ ዘዴዎችን መጠቀም
- UNEP (የተባበሩት መንግሥታት የአካባቢ ጥበቃ ፕሮግራም) እና የሰው ልጅ ግዴታዎች

### ሐ. የትምህርቱ መሠረተ-ሀሳብ

- የተፈጥሮ እጽዋት ጥበቃና እንክብካቤ ዋነኛ ዓላማዎች የጠፋውን ደን በመትከልና በመተካት ወደነበረበት ይዞታ መመለስ ሲሆን ይህም ተግባራዊ የሚሆነው አዲስ ችግኝ በመትከል፣ ተገቢ የደን አያያዝና አስተዳደር ተግባራዊ በማድረግ እና ምትክ የኃይል ምንጮችን በመጠቀም፣ በአንድ ቦታ የደን ልማትና የእርሻ ሥራን አጣምሮ በመሥራትና የሕዝብን ንቃተ-ሕሊና ወይም ግንዛቤ በማሳደግ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት የውኃ ጥበቃና እንክብካቤ የሚከተሉት ነገሮችን ተግባራዊ ማድረግን ይጠይቃል፡- የከተማ እና የኢንዱስትሪ ፍሳሽና ዝቃጭ ቆሻሻዎች በሚገባ ማከም፣ ከእርሻ፣ ከማዕድን ቁፋሮ ሥፍራ እንዲሁም ከፋብሪካዎች የሚወጣውን በካይ የኬሚካል ፍሳሽ በሚገባ መቆጣጠር ናቸው፡፡ ከዚህም በላይ የተሻሻለ ቴክኖሎጂን ሥራ ላይ ለማዋል መሞከር፣ ቆሻሻ ውኃን አክሞ ወይም አድሶ እንደገና መጠቀም፣ ውኃን የማጣሪያ እንደ ክሎሪን የመሳሰሉትን ኬሚካሎች መጠቀም ተጨማሪ ውኃን የመጠበቂያና የመንከባከቢያ ስልቶች ናቸው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አየርን ከብክለት ለመከላከል የሚከተሉት ርምጃዎች መወሰድ አለባቸው፡፡ እነርሱም ሕግ ማውጣት፣ አየር የማጣሪያ ዘዴዎችን መጠቀም፣ የጭስ መውጫዎችን መቀየር፣ አሮጌና ጭስ የሚበዛባቸው መኪናዎች ወደ መሀል ከተማ እንዳይገቡ መከልከል፣ በግል መኪና ከመጠቀም ይልቅ የጋራ ትራንስፖርት መጠቀም ወ.ዘ.ተ. ናቸው፡፡ UNEP (የተባበሩት መንግሥታት የአካባቢ ጥበቃ ፕሮግራም) የተባበሩት መንግሥታት የአካባቢ ጥበቃ እንቅስቃሴ የሚያስተባብር አለም አቀፍ አካል ነው፡፡ ይኸው ድርጅት ሀገሮች ጤናማ የሆነ የአካባቢ ጥበቃ ፓሊሲዎችን ሲያወጡና ተግባራዊ ሊያደርጉ የሚረዳና የሚያበረታታ አካል ነው፡፡ የተቋቋመውም በ1972 እ.አ.አ ሲሆን ዋና ጽ/ቤቱም በኬንያ ዋና ከተማ በናይሮቢ ይገኛል፡፡

## መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ

### 1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፡-

- የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ ዘዴዎች እንዲሁም ብክለት መቆጣጠሪያ መንገዶችን የሚያሳዩ ፎቶግራፎች ማሰባሰብ የስላይድ ፊልሞችን ጨምሮ፡፡

### 2. የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች

- ገለፃ
- ውይይት
- ሠርቶ ማሳየት

### 3. ቅድመ-ዝግጅት

- የተጠቀሙትን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በቅድሚያ ማሰባሰብ፡፡
- ተማሪዎች ተገቢ የሆኑ የማጣቀሻ መጽሐፍትን ከትምህርቱ በፊት በማንበብ እንዲዘጋጁ መንገር፡፡

## ሠ. ትምህርቱን ማቅረብ

### 1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማቅረብ የእለቱን ትምህርት መጀመር ይቻላል፡፡

- የተፈጥሮ እጽዋት ጥበቃና እንክብካቤ ስንል ምን ማለታችን ነው?
- አየርና ውኃን ከብክለት እንዴት መከላከል ይቻላል?
- አማራጭ የተፈጥሮ ሀብቶች የመጠበቂያና የመንከባከቢያ መንገዶች የምንላቸው ምንድናቸው?
- UNEP ምንድነው?

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

- ርዕሱን በተመለከተ በተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን ማብራሪያ መሠረት በማድረግ የመጠጥ ውሃ ስጋቶችና አደጋዎችን፣ የውሃና የዓየር ብክለት መንስኤዎችን፣ በመጨረሻም የመከላከያ የጥበቃ ዘዴዎችን በተመለከተ ገለፃና ውይይት ማድረግ፡-
- ተማሪዎች አማራጭ የተፈጥሮ ሐብት መጠበቂያና መንከባከቢያ ዘዴዎችን እንዲያውቁ ወይም እንዲያጠኑ መርዳት፡፡

## ረ. ምዘናና ክትትል

### 1. ምዘና

ተማሪዎች የሚከተሉት ጥያቄዎችን መልስ እንዲሰጡባቸው ማድረግ፡-

- የመጠጥ ውኃ ስጋቶችና አደጋዎች ሲባል ምን ማለት ነው?
- የውኃና የአየር በካዮችን ዘርዝሩ
- ጤናማና ከአደጋ ነፃ የሆነ አካባቢ ከመፍጠር አኳያ፣ የUNEP ሚና ምንድነው?

### 2. ክትትል

ተማሪዎች የሚከተሉትን እንዲያከናውኑ ማበረታታት፡-

- ተማሪዎቹ ሦስት ቡድን እንዲፈጥሩ ማድረግ፡-
- የመጀመሪያው ቡድን በተፈጥሮ እጽዋት ጥበቃና እንክብካቤ ዙሪያ ይወያዩ፡፡
- ሁለተኛው ቡድን በውኃ ጥበቃና እንክብካቤ ዙሪያ ይወያዩ፡፡

- የመጨረሻውም ቡድን በአየር ጥበቃና እንክብካቤ ዙሪያ ይወያዩ፡፡
- የሦስቱም ቡድኖች ተወካዮች የየቡድናቸውን የውይይት ድምዳሜ ክፍል ውስጥ ጥቁር ሠሌዳው ላይ ያስፍሩና የጎደለ ነገር ካለ በክፍሉ አባላት እንዲሟሉ ይደረግ፡፡
- ከዚህ በኋላ ሁሉም ተማሪዎች ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ ያስፍሯቸው፡፡
- ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎች በሙሉ ውሃን ከቆሻሻ የማጣሪያ ዘዴዎችን ደብተራቸው ላይ እንዲፅፉ ይደረግ፡፡

## የምዕራፍ ሦሥት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ

**ሀ) የሚከተሉት ዓረፍተ-ነገሮች እውነት ወይም ሐሰት በሉ፡፡**

1. እውነት
2. ሐሰት
3. ሐሰት
4. እውነት
5. ሐሰት

**ለ) በ"ሀ" ረድፍ ሥር የሚገኙትን በ"ለ" ረድፍ ሥር ከሚገኙት ጋር አዛምዱ፡፡**

1. ሰ
2. ረ
3. መ
4. ለ
5. ሸ

**ሐ) ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎ ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛው መልስ ምረጡ፡፡**

1. ሐ
2. ለ
3. ለ
4. ሐ

**መ) የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሐረግ ሙሉ፡፡**

1. ሰባ በመቶ
2. የተፈጥሮ ሀብቶች
3. ከ1500 እስከ 2500

**ሠ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ፡፡**

1. የዱር እንስሳት ቁጥር የሚቀንስበት ምክንያቶች
   - በሕገ-ወጥ አደን ምክንያት ስለሚገደሉ፡፡
   - መጠለያና የምግብ ምንጫቸው የሆነው ደን ሲቃጠልና ሲመነጠር መጠለያና ምግብ በማጣታቸው ምክንያት ናቸው፡፡
2. እጽዋት ለእድገታቸው ለም አፈር ያስፈልጋቸዋል፡፡ እጽዋትም አፈር እንዳይሸረሸርና ለምነቱን እንዳያጣ ከዝናብና ከወራጅ ውሃ

ይከላከሉለታል፡፡ ከዚህም በላይ ከእጽዋት የሚወዳደቁ ቅጠላ-ቅጠሎች ይበሰብሱና የአፈሩን ለምነት ይጨምራሉ፡፡

3. ሥነ-ምኅዳር እንስሳትና ተክሎች እርስ በርሳቸውና ከአካባቢያቸው ጋር ያላቸውን መስተጋብር የሚያጠና የሥነ-ሕይወት ሳይንስ አንድ ቅርንጫፍ ነው፡፡

4. ሀ) የአፈር መከላት ምክንያቶች
   - የውሃ ሸርሸራ - የቦይ ሸርሸራና በወጥነት የሰፊ አካባቢ ሸርሸራ
   - የንፋስ ሸርሸራ
   - የተዛባ የአስተራረስ ሥርዓት ናቸው

   ለ) የአፈር መከላትን ለመከላከል መወሰድ ያለባቸው ርምጃዎች፡-
   - ድነና
   - መልሶ ድነና
   - የቀለበት ወይንም የእርከን እርሻ
   - ሰብል መቀያየር
   - የእርሻ ቦታን መቀያየር (አፈሩ እንዲያገግም ፋታ መስጠት የመሳሰሉት ናቸው)
   - የቦይ ሸርሸራን ለመከላከል ክትር መስራት (check dam)
   - የእርሻ ማሳ ዙሪያ ዛፎችን መትከል (shelter belts)

# ምዕራፍ አራት

# ሕዝባዊ ጉዳዮች

**ለምዕራፉ የተመደበው ጠቅላላ ክፍለ ጊዜ፦ 17**

## የምዕራፉ ትምህርት ሲጠናቀቅ የሚጠበቁ ውጤቶች

*ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኋላ፤*

- ኤች አይቪ ኤድስ በአፍሪካ የሚያደርሰውን ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ተጽዕኖ ይተነትናሉ፤
- የመልካም አስተዳደር እጦት በአፍሪካ እያስከተለ ያለውን ችግር ይዘረዝራሉ፤
- በአፍሪካ የተመሠረቱ ክልላዊ ድርጅቶች ዓላማቸውን እንዲሁም ያላቸውን ሽፋን ይለያሉ፤
- በአፍሪካ ውስጥ ፈጣን የሕዝብ ዕድገት የሚያስከትለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ይተነትናሉ።

**ንዑሳን ርዕሶች**

- ሕዝብ ነክ ጉዳዮች
- የመብትና የደኅንነት ጉዳይ
- የአጋርነት መርሐ ግብር

## 4.1 ሕዝብ ነክ ጉዳዮች

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ: 7**

### ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

*ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ፣*

- ኤች አይ ቪ ኤድስ በአፍሪካ እያደረሰ ያለውን ጉዳት ይተነትናሉ፡፡
- የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በአፍሪካ የሚያስከትለውን ውጤት ያብራራሉ፡፡
- በአካቢያቸው በሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምክንያት ምን ምን ችግሮች እንደሚከሰቱ ዘገባ ያቀርባሉ፡፡

### ለ. ይዘት

- ኤች አይ ቪ ኤድስ በአፍሪካ እያስከተለ ያለው አሉታዊ ተጽእኖ
- ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ውጤት

### ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሐሳብ

- በዓለም ላይ ካለ የትኛውም አካባቢ የበለጠ በአፍሪካ ከሠሐራ በስተ ደቡብ የሚገኙ ሀገሮች በኤች አይ ቪ ኤድስ የተጠቁ ናቸው፡፡ በዚህ የአፍሪካ አካበቢ ወደ 22.4 ሚሊዮን የሚደርስ ሕዝብ ከኤች አይ ቪ ጋር የሚኖር ነው፡፡ እ.ኤ.አ በ2008 ዓ.ም. ከሠሐራ በስተ ደቡብ በሚገኙ ሀገሮች ውስጥ ወደ 1.4 ሚሊዮን የሚገመት ሕዝብ በኤድስ ሞቷል፡፡ ከ14 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሕጻናት ወላጅ አልባ ሆነዋል፡፡
- በአፍሪካ ሀገሮች መካከል የሚታየው የኤች አይ ቪ ኤድስ ሥርጭት የተለያየ ነው፡፡ በሦስት የደቡባዊ አፍሪካ ሀገሮች ማለትም በሌሶቶ፣ በቦትሰዋና እና በስዋዚላንድ የሚታየው የኤች አይ ቪ ኤድስ ሥርጭት መጠን ከ20% በላይ ነው፡፡ በደቡብ

አፍሪካ በኤች አይ ቪ ኤድስ የተያዘው ሕዝብ 19.9% ሲሆን ይኸውም በዓለም ላይ ከፍተኛ ቁጥር ከሚባሉት አንዱ ነው።

- በምዕራብ አፍሪካ የምትገኘው ኮትዲቯር በዓለም ላይ እጅግ በጣም አስከፊ በሆነ ሁኔታ ከተጠቁት 15 ሀገሮች መካከል አንዷ ነች። በናይጀሪያ የኤች አይ ቪ ሥርጭት መጠን 3.1% ሲሆን በካሜሮን ደግሞ 5.1% እንደሆነ ይታወቃል።
- በምሥራቅ አፍሪካ ማለትም በኬንያ በኡጋንዳና በታንዛኒያ የኤች አይ ቪ ኤድስ ሥርጭት መጠን ከ5% በላይ ነው።
- በበሽታው የመያዝና የሥርጭቱ መጠን ከፍ ብሎ የሚታየው ዕድሜያቸው ከ13 - 20 ዓመት መጀመሪያ ላይ በሚገኙ ሴቶች ላይ ነው። ወጣት ሴቶች ከወጣት ወንዶች ይበልጥ በቀላሉ በበሽታው ሊያዙ ይችላሉ።
- ኤች አይ ቪ ኤድስ በግልጽ የሚያስከትለው ነገር ሕመምና ሞት ነው። ነገር ግን ኤች አይ ቪ ኤድስ ከሚያደርሳቸው ሌሎች ተጽእኖዎች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፦ በአማካይ የመኖር ዕድሜን በመቀነስ፣ በቤተሰብ አባላት፣ በጤና ተቋም ሠራተኞችና ሥራ ላይ፣ በሕጻናት ላይ፣ በመማር ማስተማር ሒደት ላይ፣ በምርታማነትና ባጠቃላይ በኢኮኖሚ ላይ ናቸው።
- የሕዝብ ቁጥር በፍጥነት ሲጨምር እንደ ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያ፣ የጤና አጠባበቅ፣ የሥራ ዕድልና የመሣሠሉት የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶች ይጨምራሉ። ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በእነዚህ መሠረታዊ ፍላጎቶች ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ ያሣርፋል። በዓለም ላይ ያለው የምግብ አቅርቦት እያደገ የመጣውን የሕዝብ ብዛት በበቂ ሁኔታ ሊያዳርስ እንደማይችል የሥነ-ሕዝብ ባለሙያዎች ሥጋታቸውን ይገልጻሉ። በተጨማሪም ዛሬ ሰዎች ያለውን የተፈጥሮ ሀብት አሙዋጠው ቢጠቀሙበት ለወደፊቱ ከባድ ችግር ያጋጥማቸዋል። ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ለመማር ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች ቁጥር እንዲጨምር

ያደርጋል፡፡ የሕዝብ ቁጥር በፍጥነት ሲጨምር የጤና ማዕከላት፣ ሆስፒታሎች፣ የትምህርት ተቋማት፣ የመንገዥ አገልግሎት ወዘተ ብዛት እያነሰ ይመጣል፡፡ ከሁሉም በላይ የሕዝብ ቁጥር መጨመር በአንድ ሀገር ውስጥ እንደ ደን መራቆት እና የአፈር መሸርሸር የመሳሰሉ በጣም አሳሳቢ የአካባቢ ችግሮችን ያስከትላል፡፡

- የሕዝብ ቁጥር በፍጥነት ቢጨምር ከሚፈጠረው አዳዲስ የሥራ ዕድል መጠን ጋር አይጣጣምም፡፡
- የሕዝብ ቁጥር በፍጥነት ሲጨምር ወደ ድህነት ያመራል፡፡ ምክንያቱም ለዕድገት ሊውሉ የሚችሉ ሀብቶች ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡ ለመሠረተ ልማት የሚጠቅሙ ጥሬ ዕቃዎችን ለማዘጋጀት የሚውል ሀብት(ገንዘብ) መጠን እያነሰ ይመጣል፡፡

### *መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ*

### *1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች*

- ካርታ
- ሥዕላዊ መግለጫ
- ሥዕሎች
- የሕዝብ ቁጥርን (የኢትዮጵያን) የሚያሳዩ የረጅም ዓመታት ሰንጠረዥ

### *2. የተጠቆሙ የማስተማር ሥነ ዘዴዎች*

- ገለፃ
- ውይይት
- የቡድን ሥራ

### *3. ቅድመ -ዝግጅት*

- ተገቢውን የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ማዘጋጀት፣
- ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ማጣቀሻ መጻሕፍት አስቀድመው እንዲያነቡ ተማሪዎቹን ማሳወቅ

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

### 1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ

የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በመጠየቅ ትምህርቱን መጀመር ይቻላል

- ኤች አይ ቪ ኤድስ ምንድነው?
- በኤች አይ ቪ ኤድስ በከፍተኛ ሁኔታ የተጎዳው የትኛው የአፍሪካ ክፍል ነው?
- በደቡባዊ፣ ምዕራባዊና ምሥራቃዊ አፍሪካ በኤች አይ ቪ የተያዙ ጎልማሶችን የሥርጭት መጠን ዘርዝሩ።
- በቤተሰብ አባላት፣ በአማካይ የመኖር ዕድሜ፣ በጤናው ዘርፍ፣ በሕጻናት፣ በትምህርት ዘርፍ፣ በምርታማነትና በኢኮኖሚ ላይ ኤች አይ ቪ ኤድስ ያለው ተፅዕኖ ምን ይመስላል?
- በፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር ጫና የሚፈጠርባቸው የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶች ምን ምን ናቸው?
- የሕዝብ ቁጥር መጨመር እንዴት የምግብ አቅርቦት ሊያቃውስ ይችላል?
- የተፈጥሮ ሀብቶች፣ የጤና፣ ትምህርትና የሥራ ዕድል በፈጣን የሕዝብ ቁጥር ማደግ እንዴት ሊጎዱ ይችላሉ?
- ፍጹማዊ ድህነት ምን ማለት ነው?

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

- የአፍሪካን ካርታ በክፍል ውስጥ በማሣየት ትምህርቱን ይጀምሩ። ተማሪዎች ስለአፍሪካ የተለያዩ መረጃዎችን እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው። ከሠሀራ በታች ስላሉት የአፍሪካ ሀገሮች እና ሕዝቦቻቸው ተማሪዎች እንዲወያዩ ያድርጉ።
- ኤች አይ ቪ ኤድስ ምን እንደሆነ ይግለፁ።

- ከሠሐራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገሮች የኤች አይ ቪ ኤድስን ስርጭት ያመልክቱ፡፡
- የሰው ልጆች መሠረታዊ ፍላጎት የሚባሉትን ተማሪዎች እንዲዘረዝሩ ይጠይቁአቸው፡፡
- የፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር በእነዚህ መሠረታዊ ፍላጎቶች ላይ የሚያሣርፈውን ተጽእኖ ያብራሩ፡፡
- ተማሪዎችን በቡድን ከከፋፈሉአቸው በኂላ የሕዝብ ቁጥር መጨመር የሚያስከትለውን ተፅዕኖ በተመለከተ የተመረጡ ርዕሶች ይስጡአቸው፡፡ ተማሪዎቹም የተሰጡአቸውን ርእሦች በሚገባ ካጠኑ በኃላ ከመማሪያ ክፍላቸው ውስጥ ለውይይት ያቅርቡ፡፡

## ረ. ምዘናና ክትትል

### *1. ምዘና*

የሚከተሉትን ዓይነትን ጥያቄዎች ተማሪዎች ይጠይቁ፤

- በሚከተሉት የአፍሪካ ክፍሎች የሚገኙትን ሀገሮች ተማሪዎች እንዲዘረዝሩ ይጠይቁ፡፡
  - ደቡባዊ አፍሪካ
  - ምዕራባዊ አፍሪካ
  - ምሥራቃዊ አፍሪካ
- እንዲሁም በእነዚህ ሀገሮች የኤች አይ ቪ ኤድስ የሥርጭት መጠን እንዴት እንደሆነ ተማሪዎች እንዲያብራሩ ይጠይቋቸው፡፡
- የሕዝብ ቁጥር መጨመር በምግብ አቅርቦት ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖ ምንድነው?
- የሕዝብ ቁጥር መጨመር በተፈጥሮ ሀብት ላይ ምን ዓይነት ተፅዕኖ አለው?
- የሕዝብ ቁጥር መጨመር በጤና በትምህርት ላይ ምን ተጽእኖ አለው?
- የሕዝብ ቁጥር መጨመር የሥራ እድልን እንዴት ያቃውሳል?
- ድህነት ምንድነው? ግለጹ፡፡

## 2. ክትትል

- ተማሪዎችን በቡድን ከከፋፈሉአቸው በኋላ በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ፈጣን የሕዝብ ቁጥር መጨመር የሚያስከትለውን ተጽእኖ በተመለከተ አጭር ሪፖርት ጽፈው እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

## 4.2 የመብትና የደህንነት ጉዳይ

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡ 6**

### 4.2.1. የሕፃናት መብት ጥሰትን መዋጋት

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡ 3**

### ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

*ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኃላ፤*

- የሕጻናት መብት አስመልክቶ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስምምነት ይዘትን ይለያሉ፡፡
- በአካባቢያቸው የሚታዩ የሕፃናት መብት ጥሰትን ይገልጻሉ፡፡
- ሕጻናት እንዴት መብታቸውን መጠበቅ እንደሚችሉ ያብራራሉ፡፡

### ለ. ይዘት

- የሕጻናት መብት ጥሰትን መዋጋት

### ሐ. የትምህርቱ መሠረት ሐሳብ

- የሕጻናት ሕጎች ሕጻናትን ከጭካኔ ተግባር፣ ከወሲባዊ በደል፣ ቸል ከመባል ወይም ከብዝበዛ ይከላከላሉ፡፡ የመማር ዕድል እንዲያገኙ ያደርጋሉ፡፡ አያሌ ሀገሮች የሕጻናትን ፍላጎቶች የሚያስጠብቁ ሕጎች አሏቸው፡፡ በአንዳንድ ሀገሮች ውስጥ ዕድሜያቸው ከ13 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ተቀጥረው

እንዳይሠሩ የሚከላከሉ ሕጎች አሉዋቸው፡፡ በኢትዮጵያ የሠራተኞች አዋጅ መሠረት ተቀጥሮ ለመሥራት የሚያስችለው ዝቅተኛ ዕድሜ 14 ዓመት እንዲሆን ተገልጾአል፡፡ ብዙ ሀገሮች ሕጻናት በርካታ ዓመታትን በትምህርት እንዲያሣልፉ ያደርጋሉ፡፡

- እ.ኤ.አ ኖቨምበር 20 1989 ዓ.ም. በተባበሩት መንግሥታት የሕጻናት መብት ኮንቬንሽን ፀደቀ፡፡ በኮንቬንሽኑ መሠረት ሕጻኑ ሐሣቡን የመግለጽ፣ በነፃነት የማሰብ፣ ከማንኛውም ዓይነት በደል የመጠበቅ መብት እና በመልካም ሁኔታ የመኖር መብቶች አሉት፡፡
- እ.ኤ.አ ዲሴምበር 9 ቀን 1991 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሽግግር መንግሥት የሕጻናት መብት ኮንቬንሽንን ተቀብሎ አጽድቆአል፡፡ እ.ኤ.አ በ1995 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ ሕገመንግሥት ላይ ሕጻናት የመኖርና ዜግነት የማግኘት መብት እንዳላቸው በግልጽ ሠፍሮ ይገኛል፡፡ እንደዚሁም ከወላጆቻቸው ወይም ኃላፊነት ካለባቸው ሰዎች እንክብካቤ የማግኘት መብታቸው ተገልጾአል፡፡ በተጨማሪም በአካለቸው ላይ ጉዳት ከሚያመጣ ድብደባና ቅጣት ነፃ የመሆን መብት አላቸው፡፡
- ነገር ግን አንዳንድ ሕጻናት አሁንም ከተለያዩ ዓይነት በደሎች ነጻ አልወጡም፡፡ አስከፊ የሆነ ድብደባዎች ማቃጠል እና ማነቅ የመሳሰሉ በደሎች የሚፈጸሙባቸው ሕጻናት አሁንም አሉ፡፡ ሌሎች ሕጻናት በቸልታ የመታየት፣ የወሲባዊ ጥቃት እና የጉልበት ብዝበዛ ሠለባ ሆነው የሚኖሩ አሉ፡፡
- ባልተለመደ መንገድ ከሚደባብሱአቸው ሰዎች እንዲጠነቀቁ ሕጻናት በጽኑ ይመከራሉ፡፡ ወሲባዊ ትንኮሣ በሚቃጣባቸው ወቅት ኃላፊነት ለሚሰማቸው ጎልማሳ ሰዎች ወዲያውኑ መናገር ይገባቸዋል፡፡

## መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ

### 1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ሥዕሎች
- ፎቶግራፎች
- ሥዕላዊ መግለጫዎች
- ካርታዎች

### 2. የተጠቀሙ የማስተማር ሥነ ዘዴዎች

- ገለፃ
- ውይይት
- የቡድን ሥራ

### 3. ቅድመ ዝግጅት

- ተገቢ የሆኑትን የማስተማሪያ መሣሪያዎች ማዘጋጀት
- የሕጻናት መብት ጥሰቶችን የሚያሣዩ ሥዕሎችን ማሳየት
- ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ማጣቀሻ መጻሕፍት አስቀድመው እንዲያነቡ ተማሪዎችን ማሳወቅ

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

### 1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ

የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ተማሪዎቹን በመጠየቅ ትምህርቱን መጀመር ይቻላል፡፡

- የሕጻናት መብት ኮንቬንሽን ይዘቶች ምንድናቸው?
- የኢትዮጵያ ሽግግር መንግሥት የሕጻናት መብት ኮንቬሽንን ተቀብሎ ያፀደቀው መቼ ነው?
- የሕጻናት ሕገ-መንግሥታዊ መብቶች ምን ምን ናቸው?

*2. የትምህርቱ አቀራረብ*

- የሕጻናት መብቶችን የሚያግዙትን ሕጎች ይግለጹ፤
- በተለያዩ የዓለም አካባቢዎች በህፃናት ላይ የሚደርሱ በደሎችንና የጉልበት ብዝበዛን በተመለከተ ለተማሪዎቹ ማብራሪያ ይሰጡአቸው፡፡
- የሕጻናት መብት ጥሰቶችን ለመከላከል የሚጠቅሙ የማምለጫ መንገዶችን ይግለጹ፡፡

## 6. ምዘናና ክትትል

*1. ምዘና*

- የሕጻናት መበደል እና የጉልበት ሥራ ምን እንደሆነ ተማሪዎቹ እንዲያብራሩ ይጠይቁአቸው
- በአፍሪካ ውስጥ የሕጻናት የጉልበት ሥራ ምን ይመስላል?

*2. ክትትል*

- በጥቂቶቹ የሕጻናት ሕገ-መንግሥታዊ መብቶች ላይ ተማሪዎች አጭር ሪፖርት እንዲያዘጋጁ ይጠይቋቸው፡፡ በሪፖርታቸው ላይ ለምሣሌ እንዲህ ብለው ይጀምሩ፡- ‹‹የመኖር መብት አለኝ…››፤ ‹‹በአካል ላይ ጉዳት ከሚያደርስ ቅጣት ነፃ የመሆን መብት አለኝ……››፤ ወዘተ

## 4.2.2. በአፍሪካ የሚታይ የመልካም አሰተዳደር እጦት

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡ 3**

### ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

*ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኋላ፣*

- በአፍሪካ የመልካም አስተዳደር እጦት ምሳሌዎችን መጥቀስና የመልካም አስተዳደር ችግርን ያብራራሉ፡፡
- በአካባቢያቸው የሚገኙትን የመልካምና መልካም ያልሆነ አስተዳደርን አስመልክተው አጭር ዘገባ ያቀርባሉ፡፡

## ለ. ይዘት

- በአፍሪካ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር እጦት

## ሐ. የትምህርቱ መሠረተ-ሃሳብ

- በማንኛውም ሀገር የመልካም አስተዳደር መኖር የሚረጋገጠው የዲሞክራሲ ሥርዓት ሲኖር ነው፡፡ የዲሞክራሲ ስርዓት በተዘረጋበት ሁሉ ከሙስና የፀዳ አሰራር አለ ማለት አይደለም፡፡
- ከሙስና የፀዳ መንግሥት ሲኖር ብቻ ነው መልካም አስተዳደር ሊኖር የሚችለው፡፡ በአፍሪካ ውስጥ ከሙስና የፀዳ መንግሥት ለፈጣን እድገት የተመቻቸ ሁኔታን የሚፈጥርና ቀልጣፍ አሰራር ያለው መንግሥት መኖር አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡
- በየትኛውም ሀገር ቢሆን ሙስና መቶ በመቶ የተወገደበት ሁኔታ የለም፡፡ ሙስና የኢኮኖሚ ዕድገትን ያቀጭጫል፡፡ አድልዎና ብልሹ የሆነ የመንግሥታዊ አሰራርን ይፈጥራል፡፡ ከዚህም በላይ ዲሞክራሲን ከስር መሠረቱ ሊንድ ይችላል፡፡ ስለሆነም ሙስናን በሰፊውና በብቃት መዋጋት ማለት መልካም አስተዳደርን፣ የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታንና የልማት ራዕይን ዕውን ማድረግ ነው፡፡ በማንኛውም ሀገር ቢሆን ዲሞክራሲ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የተስተካከሉ የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ፓሊሲዎችን መቀየስና በብቃት ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ሙስናን በቁጥጥር ስር አድርጐ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ህብረተሰቡን በሰፊው ማንቀሳቀስ በመንግሥት አሰራር ውስጥ ግልጽነትንና ተጠያቂነት ማስፈን ያስፈልጋል፡፡
- የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር አማራጭ የሰላም ሲሆን የፀረ-ዲሞክራሲ አማራጭ ግን የደም መፋሰስና የመበታተን አማራጭ ነው፡፡ የፀረ-ዲሞክራሲ አገዛዝ በጭቁን ብሔሮችና ብሔረሰቦች ላይ

ይደርስ ነበር፡፡ በደርግ መንግሥት መውደቂያ ዋዜማ ከ17 በላይ የታጠቁ የብሔረሰብ ተቃዋሚ ድርጅቶች ነበሩ፡፡ ከደርግ መንግሥት ውድቀት በኂላ ግን የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ግንባታ አማራጭ የግድ ይል ነበር፡፡

## መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማር ሥነ-ዘዴዎች

### 1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ሥዕሎች
- ፎቶ ግራፎች
- ሥዕላዊ መግለጫዎች
- ካርታዎች

### 2. የተጠቆሙ የማስተማር ስነ-ዘዴዎች

- ገለፃ
- ውይይት
- የቡድን ሥራ

### 3. ቅድመ-ዝግጅት

- ተገቢ የሆኑትን የማስተማር መሣሪያዎች ማዘጋጀት
- ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ማጣቀሻ መጻሕፍት አስቀድመው እንዲያነቡ ተማሪዎችን ማሳወቅ

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

### 1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ

የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ተማሪዎቹን በመጠየቅ ትምህርቱን መጀመር ይቻላል፡፡

- የመልካም አስተዳደር እጦት ማለት ምንድነው?
- በመልካም አስተዳደር እና በመጥፎ አስተዳደር መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?
- ተጠያቂነትንና ግልጽነትን አብራሩ፡፡

*2. የትምህርቱ አቀራረብ*

- የመልካም አስተዳደርን ትርጉም ለመስጠት ይሞክሩ፡፡
- የሙስናን ምንነት ያስረዱ
- ለእርስ በርስ ጦርነት መንስኤ የሚሆኑትን ይግለጹ፡፡

## ረ. ምዘናና ክትትል

*1. ምዘና*

- የሙስና መገለጫዎችን ይዘርዝሩ፡፡
- አድሎአዊነት የሚገለጸው እንዴት ነው?
- ያለመረጋጋትና የእርስ በርስ ጦርነት መነሻ ምክንያቶች ምንድናቸው?

*2. ክትትል*

- ተማሪዎችን በቡድን ይክፈሏቸውና በአካባቢያቸው የሚታየውን መልካም አስተዳደርና መጥፎ አስተዳደር በተመለከተ አጠር ያለ ዘገባ እንዲያዘጋጁ ያድርጉ
- ስለ አንዳንድ የአፍሪካ መንግሥታት ሥራዎች በቴሌቪዥን ያዩት ወይም በሬዲዮ የሰሙት ዜና ካለ፣ ያዩትን ወይም የሰሙትን መማሪያ ክፍል ውስጥ ለተማሪዎች እንዲወያዩ ይጠይቋቸው፡፡

## 4.3 የአጋርነት መርሃ ግብር

**የተመደበው ክፍለ ጊዜ: 4**

**ሀ. ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት**

*ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ካጠናቀቁ በኃላ፣*

- የአፍሪካን ክልላዊ ድርጅት እና የድርጅቶች አባል ሀገሮችን ይለያሉ፡፡
- የአፍሪካ ክልላዊ ድርጅቶች የአጋርነት ዓላማዎች ይዘረዝራሉ፡፡

- የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አመሠራረትና ወደ አፍሪካ ሕብረት ስለመሸጋገሩ ይወያያሉ፡፡

## ለ. ይዘቶች

- ዋና ዋና ክልላዊ የአፍሪካ ድርጅቶች (COMESA, ECOWAS, SADC) ናይል ተፋሰስ ኅብረት (NBI)
- የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምሥረታ
- ዋና ዋና የአፍሪካ ክልላዊ ድርጅቶች ዓላማ

## ሐ. የትምህርቱ መሠረተ ሐሳቦች

- የምሥራቅና የደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ (COMESA) የተመሠረተው እ.ኤ.አ በዲስምበር 1994 ዓ.ም. ነው፡፡ የተቋቋመው የቀድሞውን "አማራጭ የንግድ አካባቢ" የተባለውን ድርጅት ለመተካት ነው፡፡ ዋናው መሥሪያ ቤቱም በዛምቢያ ዋና ከተማ ሉሣካ ይገኛል፡፡ የድርጅቱ ዋና ትኩረት በአባል መንግሥታት ላይ የሚታየውን የንግድ እገዳ ለማንሳት የሚያስችል አንድ ግዙፍ የሆነ የኢኮኖሚና የንግድ ክፍል ማቋቋም ነው፡፡ ድርጅቱ 19 አባል ሀገሮች አሉት፡፡ አካባቢያዊ ትብብርና ብልፅግና ለማሣደግ አያሌ ተቋሞች ተመሥርተዋል፡፡
- የምዕራብ አፍሪካ መንግሥታት የኢኮኖሚ ማህበረሰብ (ECOWAS) በ15 የምዕራብ አፍሪካ ሀገሮች እ.ኤ.አ. ሜይ 28 1975 ዓ.ም. የተቋቋመ አካባቢያዊ ቡድን ነው፡፡ ተልዕኮው የኢኮኖሚ ውሕደት መፍጠር ነው፡፡ ይህ ድርጅት የአፍሪካ ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ አንዱ ምሳሌ ነው፡፡ በሦስት የተለያዩ ነገር ግን ጥቅማቸው እኩል በሆኑ ቋንቋዎች ይሠራል፡፡ እነርሱም እንግሊዝኛ ፈረንሣይኛና የፖርቹጋል ቋንቋ ናቸው፡፡
- የደቡባዊ አፍሪካ የልማት ማህበረሰብ(SADC) በመንግሥታት መካከል የተቋቋመ ድርጅት ነው፡፡ ዋናው ጽሕፈት ቤቱ የሚገኘው በቦትስዋና ዋና ከተማ በጋቦሮኔ ነው፡፡ ዋናው የድርጅቱ ግብ

ማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ ትብብር፣ ውህደት ለመፍጠርና እንዲሁም የፖለቲካና የደህንነት ትብብር ለመመሥረት ነው። 15 አባል ሀገሮችን ይይዛል።

- የናይል ተፋሰስ ኅብረት (Nile Basin Initiative/NBI) በናይል ወንዝ አካባቢ በሚገኙ መንግሥታት የተቋቋመ ትብብር ነው። እነዚህ መንግሥታት ወንዙን በጋራ ለማልማት ይፈልጋሉ። በተጨማሪም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ለመጋራትና ያካባቢውን ሰላምና ደህንነት ለማስከበር ጭምር ነው። ከምሥረታው ጀምሮ ኅብረቱ በዓለም ባንክ ሲታገዝ ቆይቶአል።
- የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (አአድ) የተመሠረተው እ.ኤ.አ. ሜይ 25 ቀን 1963 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ነው። የአ.አ.ድ ቻርተር መጀመሪያ የተፈረመው 31 በሚሆኑ ነፃነታቸውን በተቀዳጁ የአፍሪካ ሀገሮች ነበረ። የአአድ ዋና ዓላማ የአፍሪካ ሀገሮችን አንድነትና ወንድማማችነትን ማሳደግ፣ ለአፍሪካ ሕዝቦች የተሻለ ሕይወት እንዲኖራቸው ሕብረታቸውን የበለጠ ማጠናከር፣ ሉአላዊነታቸውንና የግዛት አንድነታቸውን እንዲሁም ነፃነታቸውን መጠበቅ፤ ሁሉንም ዓይነት ቅኝ አገዛዝ ከአፍሪካ ማስወገድ ናቸው። የአአድ ዋና ዋና አካላት የሚከተሉት ናቸው፡- የመንግሥታት መሪዎች ጠቅላላ ጉባኤ፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ ዋናው ጽሕፈት ቤት እና ሌሎችም በአፍሪካ ውስጥ የሚታየውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ትምህርታዊ፣ የጤናው ዘርፍ፣ እና የአመጋገብ ችግሮችን የሚመለከቱ ተቋሞች ናቸው። የአ.አ.ድ ጠንካራም ደካማም ጎን አለው።
- የአፍሪካ ሕብረት (አህ) የተመሠረተው እ.ኤ.አ. ጁላይ 9 ቀን 2002 ዓ.ም. ደቡብ አፍሪካ በምትገኘው ደርባን ከተማ ሲሆን ይህ ዕለት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ለመጨረሻ ጊዜ የተሰበሰበበት ቀንና የአፍሪካ ሕብረት በይፋ ሥራውን የጀመረበት ነው። የአፍሪካ ሕብረት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የዕድገት ውጤት ነው። የአ.ሕ አራቱ ዋና ዋና አካላት የመላው አፍሪካ ምክር ቤት

(ፓርላማ)፣ የሠላምና የደህንነት ምክር ቤት፣ የአፍሪካ ፍርድ ቤት እና የአፍሪካ የገንዘብ እና የኢንቨስትሜን ፈንድ ናቸው።

## መ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች

### 1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ካርታዎች
- ሥዕሎች
- ፎቶግራፎች
- ሥዕላዊ መግለጫዎች

### 2. የማስተማሪያ ሥነ ዘዴዎች

- ገለፃ
- ውይይት
- የቡድን ሥራ

### 3. ቅድመ -ዝግጅት

- ተገቢ የሆኑትን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ማዘጋጀት
- የአፍሪካ ካርታ በክፍል ውስጥ በሚታይ ሥፍራ መስቀል
- ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ማጣቀሻ መጻሕፍት አስቀድመው እንዲያነቡ ተማሪዎችን ማሳወቅ

## ሠ. የመማር ማስተማር ሒደት

### 1. ትምህርቱን ማስተዋወቅ

የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ተማሪዎችን በመጠየቅ ትምህርቱ መጀመር ይቻላል

- የሚከተሉትን አጠር ባለ መልክ ግለጹ
  - የምሥራቀና የደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ (COMESA)
  - የምዕራብ አፍሪካ መንግሥታት የኢኮኖሚ ማህበረሰብ (ECOWAS)
  - የደቡባዊ አፍሪካ የልማት ማህበረሰብ (SADC)

- የናይል ተፋሰስ ሕብረት (NBI)
- አፍሪካ ሕብረት (AU)
- አፍሪካ አንድነት ድርጅት (አ.አ.ድ)

- የምሥራቀና የደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ ዋናው ትኩረት ምንድነው?
- የምዕራብ አፍሪካ መንግሥታት የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ዋናው ተልዕኮ ምንድነው?
- የደቡባዊ አፍሪካ የልማት ማህበረሰብ ግብ ግለጹ
- የናይል ተፋሰስ ሕብረት አባል ሀገሮች የሚፈልጉት ምንድነው?

### 2. የትምህርቱ አቀራረብ

- የአፍሪካ አካባቢያዊ ድርጅቶችን አመሠራረት ይግለጹ
- የተለያዩት የአፍሪካ ክልላዊ ድርጅቶች እንዴት ለምን እና መቼ እንደተመሠረቱ በግልጽ ያስረዱ
- በአአድ እና በአሕ ያሉትን ልዩነቶች ይግለፁ

## ረ. ምዘናና ክትትል

### 1. ምዘና

የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ተማሪዎቹን ይጠይቁ

- የእያንዳንዱን አካባቢያዊ ድርጅት አባል ሀገር መገኛ ቦታ አሣዩ
- የእያንዳንዱን አካባቢያዊ ድርጅት ዋና መሥሪያ ቤት መገኛ ቦታ አሣዩ
- የአሕ ዋና ጽሕፈት ቤት የት ይገኛል?

### ለ) ክትትል

- ተማሪዎቹን በቡድን ይክፈሏቸውና እያንዳንዱ ቡድን በአፍሪካ አካባቢያዊ ድርጅቶች ላይ አጠር ያለ ሪፖርት ያዘጋጅና መማሪያ ክፍል ውስጥ ለውይይት ያቅርብ፡፡

## የምዕራፍ አራት የክለሳ ጥያቄዎች መልስ

**ሀ) እውነት ወይም ሐሰት**

1. እውነት
2. ሐሰት
3. እውነት
4. እውነት
5. ሐሰት

**ለ) አዛምዱ**

1. ረ 2. ሰ 3. ሠ 4. ሐ 5. መ

**ሐ) ትክክለኛውን መልስ ምረጡ**

1. ሀ 2. ለ 3. መ 4. ሐ 5. መ

**መ) አጫጭር መልሶችን ስጡ**

1. ፍጹም ድህነት ማለት ምግብ ልብስና መጠለያ የመሳሰሉትን ፍላጐቶች ለማርካት የማያስችል በቂ ገቢ በገንዘብም ሆነ በዓይነት ማጣት ነው፡፡
2. ሕጻናት የኢኮኖሚ ብዝበዛ እንዳይደረግባቸው፣ አደገኛ በሆነ የሥራ መስክ እንዳይሰማሩ፣ ትምህርታቸውን የማያሰናከል ከጤንነታቸው፣ ለአካል፣ ለአእምሮ፣ መንፈሳዊ፣ ሞራላዊና ማኅበራዊ ዕድገታቸው ተቃራኒ የሆነ ሥራ ያለመሥራት ያላቸውን መብት ያከብራል፡፡ (አንቀጽ 32)
3. የመልካም አስተዳደር እጦት ምሳሌዎች፡-
   - የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው ወደ ምርትና ልማት ከማተኮር ይልቅ ወደ ሜጭበርበርና የአየር በአየር ንግድ እንዲያዘንብል በማድረግ ልማትን ሊጎዳ ሲቻል፡፡
   - ሕዝባዊ አገልግሎት የሚበረከትበት ሥርዓት ሳይሆን ዝርፊያ የሚከናወንበትና የመንግስት ስልጣን ለመያዝ በዘራፊዎች መካከል የሞት ሽረት ትግል የሚካሔድበት መድረክ ሲሆን፡፡

4. የደቡብ አፍሪካ የልማት ማኀበረሰብ የተቋቋመበት ዓላማ በመንግሥታት መካከል ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ አንድነት መፍጠር፣ በተጨማሪም ፓለቲካዊና የፀጥታ ማስከበር ተግባራትን ማከናወን ነው።
5. አፍሪካ ኅብረትና አፍሪካ አንድነት ድርጅትን የሚያመሳስላቸው ሁለቱም ተመሳሳይ ራዕይና ዓላማ ያላቸው ድርጅቶች መሆናቸው ነው። ነገር ግን የአፍሪካ ኅብረት ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት የሚለየው አራት ጠንካራ መሠረቶች ስላሉት ነው። እነዚህም የመላው አፍሪካ ፓርላማ፣ የሰላምና የፀጥታ ምክር ቤት፣ የአፍሪካ ፍትሕና ሰብአዊ መብት ፍርድ ቤት እና የአፍሪካ የገንዘብ ፈንድና የኢንቨስትመንት ባንክ ናቸው።

**ሠ) ባዶ ቦታዎቹን ሙሉ**

1. ኤርትራ
2. ጭስ እና ቆሻሻ ዝቃጭ
3. ከ14 እስከ 18
4. ደርባን
5. ዲያሎ ቴሊ

# ዋቢ መጻሕፍት


- ቤንደር፤ ኤም.ኤል. እና ኤት.ል (አርታኦች) **የኢትዮጵያ ቋንቋ**፤ ለንደን፤ 1976
- ካርስተን፤ ጄ.ኤች ሀይል ኤት.አል **የዓለም ታሪክ** ነው። ላናርክ 1996
- ጌድስ፤ ጂ፤ ኤትአልስ **የዓለም ታሪክ** ነው ላርክ 1996
- ዌልስ፤ ኤች ጂ **አጭር የዓለም ታሪክ** 1976
- ትሬዋርታ፤ ሮቢንስን፤ ሐሞንድ፤ **የጂኦግራፊ ባሕሪያት**፤ ማክግሮ ሒል መጽሐፍ ኩባንያ 5ኛ እትም ዩ.ኤስ.ኤ. 1967
- ፓል ዋርድ እንግሊሽ **በሚለዋወጠው ዓለም ውስጥ ጂኦግራፊ ሕዝብ አየር ቦታ** ብሔራዊ የመማሪያ መጽሐፍ ኩባንያ ቺካጎ ዩ.ኤስ.ኤ 1975
- ዴቪድ ዋግ **ሠፊው ዓለም** ቶማስ ኔልሰን እና ልጆቹ ተከታታይ ኃላፊነቱ የተወሰነ ሆንግ ኮንግ 1994
- ዴቪድ ዋግ **ጂኢግራፊ የተዋሐደ አቀራረብ** ቶማስ ኔልሰን እና ልጆቹ ተከታታይ ኃላፊነቱ የተወሰነ ሆንግ ኮንግ 1990
- ደብሊዩ ግሬሰድል **አጠቃላይ ጂኦግራፊ ለኢትዬጵያ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች** በትምህርት ሚኒስቴር የሥርዐተ ትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል አዲስ አበባ ኢትዮጵያ 1965
- **የ11ኛ ክፍል የጂኦግራፊ መማሪያ መጽሐፍ** ሜጋ አታሚ ድርጅት አዲስ አበባ 2001
- ጂ.ሲ ላስት **የኢትዮጵያ ጂኦግራፊ ለከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች** ዲ.ሲ ኤም. ዲ ትምህርት ሚኒስቴር አዲስ አበባ
- **ማስተር መጽሐፍ የቡድን ሥራ ለ9ኛ እና 10ኛ** ኩራዝ ዓለም አቀፍ አታሚ ድርጅት አዲስ አበባ 2002
- **የሕብረተሰብ ትምህርት መማሪያ መጽሐፍ ለ8ኛ** በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርት ቢሮ አዲስ አበባ 2006
- **ለሁለተኛ ደረጃ ጂኦግራፊ አዲስ መምሪያ 9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች** አስቴር ነጋ አታሚ ድርጅት አዲስ አበባ 2000
- መኩሪያ ፈለቀ ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ጠቃሚ ጂኦግራፊ አዲስ አበባ 1997